# ኆኅተ ሃይማኖት

ከ

ብርሃኑ ጐበና

መስከረም 1986 ዓ. ም.
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያ ዕትም መስከረም 1986 ዓ.ም.
ሁለተኛ ዕትም ሐምሌ 1987 ዓ.ም.
ሦስተኛ ዕትም ጥቅምት 1995 ዓ.ም.

## መታሰቢያነትዋ

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ሥርዓትና ትውፊት መጠበቅና መስፋፋት ጥረት ለሚያደርጉ ክርስቲያኖች ሁሉ ትሁንልኝ ።

## ምስጋና

ይህችን መንፈሳዊ መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ በሐሳብና በማቴሪያል የረዱኝን መምህር ገ/ሚካኤል ድፈር የሰዋሰው ብርሃን ቅ/ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ም/ዲን እንዲሁም ረቂቁን በማረም የተባበሩኝን ዲ.ጌታቸው ደጀኔ በተጨማሪም ረቂቁን ታይፕ በማድረግ የተባበሩኝን እህቶችና ይህ መጽሐፍ ታትሞ እስኪወጣ ድረስ ልባዊ ትብብራችውን ላደረጉልኝ ለንግድ ማተሚያ ድርጅት ሠራተኞች በሙሉ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን በአንባብያን ስም አቀርባለሁ።

## ምስጋና ፤

ይህችን መንፈሳዊ መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ በሐሳብና በማቴሪያል የረዱኝን መምህር ገ/ሚካኤል ድፈር የሰዋሰው ብርሃን ቅ/ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ም/ዲን እንዲሁም ረቂቁን በማረም የተባበሩኝን ዲ. ጌታቸው ደጀኔ በተጨማሪም ረቂቁን ታይፕ በማድረግ የተባበሩኝን እህቶችና ይህ መጽሐፍ ታትሞ እስኪወጣ ድረስ ልባዊ ትብብራቸውን ላደረጉልኝ ለአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ሠራተኞች በሙሉ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን በአንባብያን ስም አቀርባለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ


መቅድም - - - - - - - - - - - - - - - - 7

ማስገንዘቢያ - - - - - - - - - - - - - - 9

ምዕራፍ ፩ መንፈስ ቅዱስ - - - - - - - - - - 15

1.1 በመንፈስ ቅዱስ ላይ ክህደት ያስተማሩ - - 16

1.2 መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሠረጸ ነው - - 20

1.3 መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እስትንፋስ ነው - - - 25

1.4 የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክነት - - - 27

1.5 የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ - - - - - - - - 29

1.5.1 የልሳን ስጦታ - - - - - - - - 30

1.5.2 በልሳን መጸለይ - - - - - - - 34

1.5.3 የመፈወስ ስጦታ - - - - - - - 35

1.5.4 ትንቢት የመናገር ተሰጥኦ - - - - 37

1.5.5 ህልም - - - - - - - - - - 47

1.5.6 መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተያየት - - - 52

1.6 የመንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰል ምሥጢር - 55

1.7 መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል የወረደበት ምክንያት - - - - - - - - - - - 57

1.8 ማጠቃለያ - - - - - - - - - - 58




www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፪. ቅዱሳን መላእክት - - - - - - - - - - - 59
2.1 የመላእክት ተፈጥሮ - - - - - - - - - 59
2.2 መላእክት ምን ቀን ተፈጠሩ - - - - - - - 60
2.3 የመላእክት ባሕርይ - - - - - - - - - 61
2.4 የመላእክት አገልግሎት ፤ (ተራዳኢነታቸው) - 63
2.5 መላእክት ሊሰገድላቸውና ሊከበሩ ይገባቸዋል - 71
2.6 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልአክ (ሚካኤል) ነው? - - - - - - - - - - - 77
2.7 ማጠቃለያ - - - - - - - - - - - - - 81
ምዕራፍ ፫ ተዝካርና ፍትሐት - - - - - - - - - - 82
ምዕራፍ ፬ ስለምንኖርባት ምድር ማለፍና ስለመንግሥተ ሰማይ - - - - - - - - - - - - 93
ምዕራፍ ፭. መጭው አውሬ - - - - - - - - - - 102
5.1 እሱ ማን ነው - - - - - - - - - 103
5.2 ራእዩ የታየበት ቦታ - - - - - - - - - 105
5.3 ትውልዱና አቋሙ - - - - - - - - - 108
5.4 ዐሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች የተባሉት ምንድር ናቸው? - - - - - - - - - - 109
5.5 ምክንያቱ ምን ይሆን? - - - - - - -113
5.6 የ666 ምሥጢራዊ ፍቺ - - - - - - - 120
5.7 በመጨረሻስ - - - - - - - - - - - 123
ምዕራፍ ፮. ተጠራጣሪዎች የሚያቀርቡአቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው - - - - - - - - - - - 125



# መ ቅ ድ ም

ቸርነቱ እንደ ባሕር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት ሁልቆ መሣፍርት የሌለው የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምሥጋና ይግባውና ለሙሉ ጤንነቱ ደህና ነኝ ። መቼም በአሁን ዘመን ከሚነፍሰው የኑፋቄ ነፋስ ተጠብቆ ጤና መሆንን የመሰለ የለምና አንዳንዶች ቀደም ጤነኛ የነበሩ ባጭር ጊዜ የክህደትና የኑፋቄ ተስቦ ተጋብቶባቸው ቀድመው ያመልኩትንና የወደዱትን ጌታ በመካድ በሽታ ታመው በፍልስፍና አልጋ ላይ ተኝተዋልና ። ያውጣን ነው ወገኖች ። አይጣል ኮ ነው ገንዘብን ያህል ክፉ ባላጋራ በላያችን ነግሦ! አድነን ጠብቀን ። ከማለት ምን ሊባል ይችላል ።

እና ወገኖቼ በዓምደ ሃይማኖት መጽሐፍ የትውውቁ መንገድ የተከፈተ ስለሆነ ዛሬ ከትውውቅ ጉራ ወጥተን ወደ መጠያየቅ አንባ የዘለቅን ይመስለኛል ። አንዳንድ ወገኖች በጽሑፍም ሆነ በግንባር ብዙ አስተያየት ሰጥተውኛል ። ለምሥጋናውም ሆነ ለገቢው ሒስ እግዚአብሔር ይስጥልኝ በዚህች ሁለተኛ መጽሐፌ በመጀመሪያው መጽሐፌ የተሰጠኝን ሒስ ለማሻሻል ሞክሬያለሁ መቼም ሰው በአንድ ጊዜ እንከን የማይወጣለት እንደማይሆን የታወቀ ነው ። ኧረ እንዲያው እልፍ ዘመን ቢኖር እንከን አይታጣበትም ። በሥራው እንከን የማይገኝበት ንጹሐ ባህርይ አምላክ ብቻ ነው ።

ዓላማዬ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ መንጭቶ ከሐዋርያት ልቡና ውስጥ የተቀዳውን ንጹህ ማየ ሕይወት ሳትደፈርስ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ልቡና ውስጥም እንዲንቆረቆር ማድረግ ነው ። ስለዚህ ይኸን ንጹህ ውሀ ለማደፍረስ የተነሱ አደፍራሾችን መጽሐፍ ቅዱስ አጥብቆ ስለሚያወግዝ እኔም ሕብረቴን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አድርጌ እርሱ የሚቃወማቸውን ተቃውሜያለሁ እቃወማለሁም «ጸባችሁ ሥጋን ከለበሰ ጋር አይደለም» እንደተባለው ሁሉ የእኔም ጸብ ከሥጋ ለባሹ ወገኔ ጋር ሳይሆን የኑፋቄን ትምህርት በሰዎች ልቡና ከዘራው ከጥንት ጠላት ከዲያብሎስ ጋር ነው ። ስለዚህ አንዳንድ የዲያብሎስ ማኅደር ሆነው የሚያገለግሉ ሰዎች አመለካከት በሚነቀፍበት ጊዜ ሰዎ



www.ethiopianorthodox.org

ቹን ራሳቸውን መንቀፍ አለመሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል ። ጌታችን «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኲላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠበቁ» ማቴ ፯. ቊ. ፲፭ ። ሲል ሰብአዊነታቸውን ገሮ ተኲላ ብሎ መሳደቡ ሳይሆን ተኲላዊ ጠባያቸውን መንቀፉ ነው ። እንዲሁም «የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ» ማቴ ፯. ቊ. ፮ ሲል በቁሙ ውሾችን ማንሣቱ ሣይሆን ሰው ሆነው ተፈጥረው ሳለ የውሻ አይነት ግብር ለሚያንጸባርቁ ሰዎች ነው ። መጥምቀ መለኮት ዮሐንስም ፈሪሳውያንን ሲገሥጽ «እናንት የእፉኝት ልጆች» ማቴ. ፫. ቊ. ፯ ። ብሏቸዋል ። ጌታም ሄሮድስን ቀበሮ ብሎታል ሉቃ ፲፫. ቊ. ፴፪ ።

አንዳንድ ሰዎች ለተግሣጽ የተጻፉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አነጋገሮች መጠቀስ እንደ ሌለባቸው በምትኩ ዲፕሎማሲያዊ አነጋገር መተካት እንዳለበት አስተያየት ይሰጣሉ ። ዳሩ ግን ጌታንና ቅዱሳንን አነጋገራቸው ያልታረመ ነው ብሎ እንደመሳደብና ከጌታም በላይ ትሁት ሆኖ ለመታየት የተደረገ ከንቱ የዓለም ነገር ስለሆነ ክርስቶሳውያን የተባልነው ልንቀበለው ያስቸግረናል ። ምንን ምን ካላሉት እንደሚባለው ሁሉ መናፍቅንም መናፍቅ ካላሉት ሐቀኛ ትክክለኛ ካሉት ሥህተቱ በምን ይታወቃል ። ጌታ ራሱ ሲያስተምር ከሐሰተኞች ትምህርት ተጠበቁ አለ እንጂ በዲፕሎማሲያዊ አነጋገር አልተጠቀመም የወደደ ቢኖር ይምጣ የጠላም ይመለስ ነው ። ትምህርቱ ግልጽ ነው ።

ስለዚህ እኔም መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ቃል እንጂ የጊዜውን የማባበያ ቃል አልተጠቀምኩም ። ስለሆነም በጽሑፉ ውስጥ መናፍቅ የሚል ቃል ካገኛችሁ ተጠራጣሪ ትንሽ እውነት ይዞ ብዙውን እውነት ሽምጥጥ አድርጎ የሚክድ ማለት ነወ ና ከስድብ አትቈጠሩት ። ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ያለ ነውና ። ገላ ፩ ቊ ፳፩ ።

ብርሃኑ ጐበና ።



# ማ ስ ገ ን ዘ ቢ ያ

የእግዚአብሔር ምርጥ ዕቃ የተሰኘው ሐዋርያው ጳውሎስ ለታመነው ደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በላከው ክታቡ አበክሮ ያስገነዘበው ዓቢይ ቁም ነገር ነበር ። ደግሞም ለጢሞቴዎስ ብቻ አይደለም በእምነት ጳውሎስን ለሚመስሉት ክርስቶሳውያን ሁሉ እንጂ ።

«በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ አንተ ግን ለዚህ ዓለም ከሚመቹና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ» ፩ኛ ጢሞ ፬. ቊ. ፩—፫ ።

ፍጻሜ ዓለም እየተቃረበ ባለበት በአሁኑ ወቅት ጳውሎስ ቀደም ብሎ እንደገለጸው ግብዝነት የተሞላበት የሐሰት ትምህርት ክርስቲያናዊ ካባ ተላብሶ በዓለም ላይ ነግሦ ይታያል ። የኃይማኖት ሰዎች ነን የሚሉ ብዙ ሰዎች እንኳን ከላይ እንደተጠቀሰው በውሸተኞች ግብዝነት የሚሰጠውን ላዩ የክርስቶስ የሚመስል ውስጣዊ ዓላማው ግን የአጋንንት የሆነን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖታቸውን እየካዱ ነው ።

የሃይማኖታችን ራስ የሆነው መድኃኒዓለም ክርስቶስ «በውኑ የሰው ልጅ ለፍርድ ሲመጣ ከሰው ልጆች እምነትን ያገኝ ይሆንን» ሉቃ ፲፰ ፥ ፰ ብሎ መናገሩ ሰዎች በመጨረሻው ዘመን ክርስቶስ በደሙ ከመሠረታት ሃይማኖት ወጥተው በራሳቸው ፍልስፍና በፈጠሩት እንደሚያምኑ ሲገልጽ ነው ።

«እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» ፩ኛ ቆሮ ፲. ቊ. ፲፪ በርግጥ ነው ያለነው ፈታኝ በሆነ ዘመን ላይ ነን ብዙዎች ቀድሞ በሁለት እግራችን ቆመናል እያሉ ሲፎክሩ ዛሬ ግን የዓለም ጭቃ አዳልጦአቸው በኑፋቄ ማጥ ገብተው የሚዳክሩ እንደዝናብ ጠብታ ለመቁጠር ያዳግታሉ ። ትናንት የሐዋርያትን አርማ ይዞ



www.ethiopianorthodox.org

«አንድ ክርስቶስ አንዲት ሃይማኖት» ሲል የነበረው ዛሬ ግን ከዓለም ጋር ተመሳስሎ ለመኖር ሐዋርያት ያልሰበኩትን ሌላ ክርስቶስን ከሚሰብኩ ጋር ተደምሮ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ መዶሻ ይዞ የተነሣ ጥቂት አይደለም ።

የክርስቶሳውያን መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ እየታመነ በተለያዩ ዘመናት እንደ ቀድሞዎቹ የታየል ልጆች ስማቸውን በዚህች ኃላፊ ዓለም ላይ ለማስጠራት የፍልስፍና ግንብ ገንብተው ከላይ ግን እውነተኛ ሐዋርያ ለመምሰል የክርስቶስን ስም አንግበው ክርስቲያኑ ወገን ከወንጌል ጋር ሆድና ጀርባ እንዲሆን ያደረጉ ሰዎችን በመከተል ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና ሕግ ፍጹም ርቋል ።

ዛሬ የክርስትናውን ዓለም ብንቃኝ በወንጌል ላይ የተሰበከው ክርስቶስ አንድ ክርስቶስ ተከታዮቹም እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ የሆኑ በአንድ ቤተክርስቲያን ጥላ ሥር የተጠለሉ አንድ ክርስቶስን የሚያስተምሩ ሆነው ሳለ ዛሬ ግን ራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን ብለው የጠሩ ብዙ ክፍሎች የተለያየ ክርስቶስን ሲሰብኩ ይሰማሉ ።

አካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ በመወለዱ በኃጢአት የረከሰውን አዳምን ከወደቀበት የኃጢአት ማጥ ለማውጣት መሆኑ በወንጌል ላይ የተዘገበ አሌ የማይባል ዝልቅ ነገር ነው ። በዚህች ምድር ላይ ሠላሣ ሦስት ዓመት ያደረገው ጉዞም በፈቃዱ ወዶ ያደረገው እንጂ ማንም አስገድዶት አይደለም ። ወዶ ፈቅዶ የሰዎች ልጆችን በደል እርሱ ተሸክሞ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ታዛዥ ሁኑአል ። አምላካችን ምን ያህል ወዶናል ። ይገርማል ይደንቃል በእውነት ለዚህ ፍቅሩ አንክሮ ይገባል ። መላእክትን እንዳይሞቱ አድርጎ የፈጠረ ጌታ እርሱ ግን የእጁ ሥራ የሆነውን አዳምን ከወደቀበት ለማንሣት ከፈጠራቸው ከመላእክት በትሕትና አንሶ ሞትን ቀመሰ ። ዕብ. ፪. ቍ. ፱ ።

መሞት የማይገባው አምላክ ሞተ ። መዋረድ የማይገባው አምላክ እኛን ከወርደት መንጥቆ ለማውጣት ተዋረደ ። ከገነት የተሰደደውን አዳም ወደ ገነት ለመመለስ መድኅን ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር በሕጻንነቱ ወደ ግብጽ በረሐ ተሰደደ ። በዙፋኑ ዙሪያ ከበው ከመለኮታዊ ፊቱ



የሚወጣውን ብርሃን ማየት ስለማይቻላቸው በስድስቱ ክንፋቸው ኪሩቤል የተባሉት መላእክት ፊታቸውን የሚሸፍኑለት ልዑል ባሕርይ አምላክ እጸ በለስን በመብላቱ ጸጋው ተገፎ የነበረው አዳምን የቀደመ ጸጋውን ለማላበስ እርሱ ስለ ሁላችን እርቃኑን በመስቀል ላይ እንደ ብራና ተወጠረ ይኸን ሁሉ የፍቅር ሥራ የሠራው ጌታ ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ትመሰክራለች ። ታስተምራለች ።

በአንጻሩ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን በአግባቡ ያልተረዱ አጸራረ ክርስቶስ «ጌታ ወዶ ፈቅዶ ያደረገውን የትህትና» ሥራ ሁሉ ከግንዛቤ ሳይከቱ ሳይወድ በግዱ እንደተንገላታ እንደሞተ አድርገው በመውሰድ ከባሕርይ አባቱ ከአብ በመለኮታዊ ሥልጣን ለይተው ፍጡር በማለት» ፍጡር ክርስቶስን» የሚሰብኩ ዳሩ ግን የልባስ ስማቸው ክርስቲያን የተባሉ አሉ ።

በሌላ አንጻር ደግሞ ከባሕርይ አባቱ ከአብ አሳንሰው ዛሬ በአብ ቀኝ ተቀምጦ ለእኛ ይለምናል በመለኮቱ ከአብ ጋር አንድ ቢሆንም በሥጋው ግን ከአብ ያንሳልና በማለት «አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» ዮሐ. ወን. ፩. ቍ. ፲፬ ። ተብሎ አንድ ብቻ መሆኑ የተመሰከረለትን ክርስቶስን ሁለት ከፍለው ሁለት አድርገው አንዱ አምላክ ነው አንዱ ለማኝ ነው በማለት በማይከፈለው ጌታ ላይ መከፈልን የፈጠሩ አሉ ግን ክርስቲያን ተብለው ነው የሚጠሩት አንድ አካል አንድ እግዚአብሔር ብለው የተነሱ ሰበልዩሳውያንም አሉ ። እነዚህም ክርስቲያኖች ነው የሚባሉት ።

ኧረ ስንቱን ጠቅሰን እንዘልቀዋለን ባጭሩ ጌታችን በመጨረሻው ዘመን እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢሏችሁ አትመኑ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና ፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትናድንቅ ያሳያሉ እነሆ አስቀድሜ ነገርኩአችሁ» ማቴ ፳፬. ቍ ፳፫—፳፮

አስቀድሞ እነዚህ ሁሉ ሐሰተኞች ክርስቶሳውያን እንደሚመጡ በፈጣሪያችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተነገረን ወልድ ዋህድ በምትል በተዋሕዶ ሃይማኖት የምናምን ክርስቲያኖች ማንም ሊያሳስተን አይገባም ዛሬ ባሕር ላይ እንደወደቀ ከብት የሚዋ



www.ethiopianorthodox.org

ልሉ ወገኖች ከጥርጥር ወደማረጋገጥ መሸጋገር ይጠበቅባቸዋል ። መቼም ዘመኑ የእታላዮች ዘመን መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው ስለሆነም የክርስቶስን ስም የጠራና መጽሐፍ ቅዱስን በእጁ ያነገበ ሁሉ ትክክለኛ ሐዋርያ አይምሰለን «ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለዉጣሉ ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ» ይሁዳ ፩. ቊ. ፬ ።

እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሐር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ» ይሁዳ ፩ ቊ ፳

ወደ ተቀደሰው ጉባኤ ሾልከው የገቡ አንዳንዶች «አንዲት ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት አንድ ጌታ» ኤፌ. ፬ ቊ ፭ የሚለውን መርሆ ይዘው የተነሱ እውነተኛ ክርስቶሳውያንን ለማሰናከል ይኸ የወግ አጥባቂዎች አባባል ነው ። እስከ መቼ ድረስ በወግ አጥባቂነት ገመድ ተተብትባችሁ ትኖራላችሁ ። «ከእኔ ሃይማኖት ውጭ ሌላው ትክክል አይደለም» የሚለው ራስን ማመጻደቅ ነው የሁሉም እምነት ያጸድቃል በሚል ፍልስፍናዊ አመለካከት ክርስቲያኑን ሲያውኩት ይታያሉ ። ዳሩ ግን ይኸ አባባል ለዓለም ሕግ የሚመች ቢሆንም ለሰማያዊው መንግሥት ግን በር ዘጊ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ያላመኑ ተስፋ እንደሌለው ሲገልጥ እውነት እውነት እላችኋለሁ እኔ የበጎች በር ነኝ ።..... በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል ።.....» ዮሐ ወን ፲ ቊ ፯ — ፲፩

«ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም በወልድ የሚታመን አብ ደግም አለው» ፩ኛ ዮሐ. መል ፪. ቊ. ፳፪

እንግዲህ ፍፁል ባሕርይ የሆነውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከአብ አሣንሰው እንደ ፍጡር ወይም ነቢይ እንዲሁም ለማኝ — (አማላጅ) አድርገው የሚያምኑ ሰዎች በዚህ እምነታቸው ሊድኑ አይችሉም የዳንነው በፍጡር ወይም በአማላጅ አይደለም ራሱ እግዚአብሔር አምላክ ሥጋን ተዋሕዶ በእውነት አዳነን እንጂ «የይሁዳን ቤት



አምራለሁ በአምላካቸውም በእግዚአብሔር አድናቸዋለሁ» ትንሆሴ ፩. ቊ. ፯ ።

«በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ። ...... ቃልም ሥጋ ሆነ» ዮሐ. ወን. ፩. ቊ. ፩ — ፲፬

ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስን ሁሉን ቻይ አምላክ ተማላጅ (ተለማኝ) ፣ ፈራጅ አዳኝ ብላ የምታምን ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ፍጡር ፣ አማላጅ ብለው ከሚያምኑ ጋር ምን አንድነት ሊኖራት ይችላል ። የእግዚአብሔር ቃል ይኸን በማስመልከት እንዲህ የሚል ሜን ያለ ትዕዛዝ ያስተላልፍልናል ። «ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን መስማማት አለው ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው የእግዚአብሔር ታቦት ከጣኦት ጋር ምን መጋጠም አለው ፪ኛ ቆሮ. ፮. ቊ. ፲፬ — ፲፮ ።

እንግዲህ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኛችሁ ወገኖች ዛሬ ብዙ ሰይጣን ያነሳሳቸው የወንጌል ሰባኪ የሚመስሉ መናፍቃን እንደ አሸን የፈሉበት ዘመን ነውና ልንጠነቀቅ ይገባናል ። እነዚህ ሰዎች በወንጌል ላይ የፍልስፍና ደባል አኑረው ምስቅልቅሉ በወጣ ሕይወት ውስጥ ያሉ ሆነው የሌላውንም ሕይወት ለማመሰቃቀል የተነሱ ናቸው ።

በየዘመኑ የማትታደሰውን በክርስቶስ ደም የተዋጀችውን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ በላይ ሆነው ለማደስ ሲንጠራሩ ይኖራሉ ነገር ግን «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘለዓለም ያው ነው ። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ» ዕብ ፲፫. ቊ. ፰ ። እንደተባለው ክርስቶሳውያን ዘመን ያፈራው የኑፋቄ ትምህርት በልቦናችን ማሳ ላይ ተዘርቶ እንዳይበቅል ተግቶ መጸለይ ያስፈልጋል ።

«ኖኅተ ሃይማኖት» (የሃይማኖት በር) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሰዎች ሁሉ የክርስቶስን ማንነት ካላወቁ በስተቀር በሩን አላገኙትም ማለት ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስ ያለና የነበረ ፣ ሁሉን የሚችል ፣ ስለ ሰዎች ልጆች ሲል በሥጋው መከራን የተቀበለና የሞተ ሞትን ድል አድርጐ በሦስተኛው ቀን በገዛ ሥልጣኑ የተነሣ ኋላም ዓለምን ለማ



www.ethiopianorthodox.org

ሳለፍና በዓለም ላይ ለመፍረድ የሚመጣ እውነተኛ አምላክ ነው ። ፩ኛ ዮሐ. መል ፭. ቍ. ፳ ራእይ ፩. ቍ. ፰ ።

ይህ አምላክ በስሙ ለምናምን እውነተኛ አማኞቹ እንዲህ ይለናል «በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር እንዲሁ ለብ ስላለህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው» ራእይ ፫. ቍ. ፲፭ — ፲፮ ።

ሁሉም እምነት ያጸድቃል በሚል ሰፊ መንገድ የምትጓዙ ወገኖች ከዛሬ ጀምራችሁ ጠባብዋን መንገድ ምረጡ የመረጣችሁት መንገድ በእርግጥ ለጊዜው ጭንቅ የሌለበት መስሎ ቢታያችሁ ለወደፊት ግን የሚያደርሳችሁ ስሩ ወደ ማይታወቅ የስቃይ ገደል ነው ። «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው»

ስለዚህ Universalist (ዩኒቨርሳሊስት) አቋም ያላችሁ ዛሬ ውኑ አቋማችሁን ልታስተካክሉ ይገባል ። እውነተኛ ድኅነት የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ በሚለው ሁሉ ስንመራና ስንጓዝ እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለአመለካከታችን የሚጠቅመውን በመውሰድ ሌላውን በመተው አይደለም ከሕግ አንዲቱን የሚንቅና የሚያስተምር ቢኖር እርሱ በሁሉም በደለኛ ይባላል የሚለውን ቃል ልናስብ ይገባናል ።

ጌታ ያከበራቸውን ማክበርና መውደድ በጸሎታቸውም ተጠቃሚ መሆን የጌታ ፍጹም ልጆች መሆናችንን ያሳያል እንጂ ከክርስቶስ አምልኮት መውጣትን አይደለም ።

እንግዲህ ከላይ ያለው ሐተታ የታተተበት ምክንያት አለው ። አንዳንድ ሰዎች ያልሆነ አቋም ይዘው ስላስተዋልኩ ነው ። በተለያየ ዶግማ የተለያዩ እምነቶች በዚሁ በእምነት ልዩነታቸው እንዳሉ ሁሉም የጽድቅን መንገድ የያዙ ናቸው የሚል እምነት ያላቸው ብዙ ሰዎች ስለገጠሙኝ ነው ።

እኛ ግን መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነውና ጌታችን ኢየሱስ በደሙ የመሠረታት አንዲት ሃይማኖት ብቻ እንዳለችና ሰው ሁሉ በዚህች ሃይማኖት ጥላ ሥር ተጠልሎ ለመንግሥተ ሰማይ እንደሚበቃ እናምናለን እምነታችንም በእውነተኛዋ ወንጌል ላይ የተመሠከረ ነው ኤፌ ፬ ፡ ፭ ።



# ምዕራፍ አንድ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን ፡

## መንፈስ ቅዱስ (ፓራክሊቶስ)

ከበዓለ ጰንጠቆስጤ ጀምሮ ቤተክርስቲያንን የሚመራው ከቅድስት ሥላሴ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ነው ። ጌታ በስልጣኑ በሀይሉ ሞትን ድል አድርጐ በተነሣ በሃምሳኛው ቀን ጰንጠቈስጤ በጽርእ «ፔንዲኮንዳ» ትርጉሙ ሃምሣ ማለት ነው (1) ቤተ ክርስቲያንን ለማጽናትና ለማጽናናት መንፈስ ቅዱስ እመቤታችን ባለችበት በሐዋርያት ጉባኤ ተገኘ ። ከዚህም የምንረዳው ነገር ቢኖር መንፈስ ቅዱስ የእመቤታችን የቅዱሳት ድንግል ማርያም አማላጅነት በሚታመንበት ጉባኤ ላይ ብቻ እንደሚገኝ ነው ።

መንፈስ ቅዱስ «ጰራቅሊጦስ» በጽርእ «ፓራክሊቶስ» ። ናዛዚ ፡ መጽንዒ መስተፍሥሒ ማለት ነው ። (2) በአማርኛ አረጋጊ አጽናኝ ፡ አስደሳች እንደማለት ነው ። ያዘኑትን ያረጋጋል ፡ ያስደስታል የደከሙትን ያበረታል ። ሰማእታትን ወደ ደም መነኮሳትን ወደ ገዳም ምዕመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ በውስጥ ይቀሰቅሳል ። በቅዱስ መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያን ምሥጢራትን በመንፈስ ቅዱስ ትቀድሳለች በምሥጢራት አማካኝነት የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ለምእመናን ትናኛለች የክርስቲያኖችን እምነት በቤተ ክርስቲያን የሚጠብቅና የሚያስፋፋ መንፈስ ቅዱስ ነው ። በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ክርስቶስን የባህርይ አምላክ ነው ብሎ የሚያምን የለምና ፩ኛ ቆሮ ፲፪ ፡ ፫ ።

---

(1) የቤ/ክ ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ 99
(2) ኪዳኑ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 907



www.ethiopianorthodox.org

## በመንፈስ ቅዱስ ላይ ክህደት ያስተማሩ

1ኛ. <u>መቅዶንዮስ ፡—</u> ከሐዲው መቅዶንዮስ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ነበር ። እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ373 ዓ. ም. እንደ አውሮፓውያን በ381 ዓ. ም. መንፈስ ቅዱስን ከአብና ከወልድ ለይቶ ፍጡር ነው ብሎ ተነሣ ። ይኸን ክህደቱን ቤተ ክርስቲያን ተቃወመች አንድ መቶ ሃምሣ የሚሆኑ ኤጲስ ቆጶሳት ከመላው ዓለም ተሰባስበው በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ተደረገ ። በጉባኤውም ላይ ከሐዲው መቅዶንዮስ የኑፋቄ ትምህርቱን አቀረበ በመቅዶንዮስ እምነት መንፈስ ቅዱስ «ገዘርው ሀይል» ፍጡር ነው ። እንደ አብና እንደ ወልድ በዘባነ ኪሩብ ላይ ተቀምጦ የሚሠለስ የሚቀደስ የባህርይ አምላክ አይደለም ። ነገር ግን ይህ ትምህርት ፍጹም ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣና የክርስትናን እምነት የሚያናጋ ስለሆነ ጉባኤው እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሆኖ የመቅዶንዮስን የኑፋቄ ትምህርት አውግዟል ። (3)

## የቁስጥንጥንያ አንቀጸ ሃይማኖት

1. በጌታ በአዳኝ ከአብ በሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን እንሰግድለት እናመስግነው
2. በሁሉ ባለች በሐዋርያት ጉባኤ ባንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን
3. ለኃጢአት ማስተሰሪያ ባንዲት ጥምቀት እናምናለን
4. የሙታን ትንሣኤን ተስፋ እናደርጋለን ። (4)

መቶ ሃምሣ ሊቃውንት መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሠረጸ መሆኑን አረጋግጠው ይህንንም ለተከታዩ ክርስቲያን ሁሉ ይተላለፍ ዘንድ በቁስጥንጥንያው አንቀጸ ሃይማኖት ካሰፈሩ በኋላ ሰይጣን የቀሰቀሰው

(3) ሚስጥረ ሥላሴ ገጽ 132
(4) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ 130



ሉክዮስ የሚባል መናፍቅ በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሳይሆን ከወልድም የሚወጣ ነው በማለት በኢየሩሳሌም አውራጃ ሲያስተምር ቅዱስ ጎርጎርዮስ ኢየሩሳሌም ለመሳለም ሲመጣ ይህን የክህደት ትምህርት ሉክዮስ ሲያስተምር ስላደመጠው ይህን የክህደት ትምህርት ማስተማሩን እንዲያቆም ገሠጸው ። እሱ ግን እንደውም በሌላውም ክፍል ይኼን መርዙን ልርጭ ብሎ ወደ ሮም ተሻግሮ ክህደቱን በሕዝቡ ላይ ነዛ ። ሕዝቡም ያለምንም ማንገራገር ትምህርቱን እንደተቀበሉለት ባየ ጊዜ የፈረንሳይ ንጉሥ ወደ ሆነው ወደ ታላቁ ካርሎስ ዘንድ ሄዶ ጉባኤ ይደረግልኝ ብሎ ንጉሱን ለመነ አዲሱን ክህደቱን ሊያስመርቅ ። ንጉሡ ግን ሳይቀበለው ቀረ ። እንዳውም ስለሁኔታው ገልጾ ለሮሜ ሊቀጳጳስ ሶስተኛ ልዮን ላከለት ሊቀጳጳሱም የሉክዮስ ትምህርት አዲስ ክህደት መሆኑን ለምስክርነት እንዲሆነው ሶስቱን ዓበይተ ጉባኤ ጉባኤ ንቂያ ፣ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ ፣ ጉባኤ ኤፌሶን የወሰኑትን የሃይማኖት መመሪያ በሁለት ሳንቃ (ጣውላ) ላይ በላቲንና በዮናኒ ቋንቋ አስጽፎ በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ደጅ ላይ ሰቀላቸው ገቢና ወጪው እንዲያስተውላቸውና ከአዲስ የክህደት ትምህርት እንዲጠበቅ (5)

ነገር ግን ሶስተኛው ልዮን አዲሱ ክህደት በ451 ዓ. ም. በተፈጠረው ክህደት ላይ ተጨማሪ እንዳይሆን ብሎ የወሰደው ጥንቃቄ አልሰመረም በፖፕ ቤኔዲክቶስ ዕብሬት ዘመን ማለትም በ1ሺህ አስራ አራት ዓ. ም. የሉክዮስ የክህደት ትምህርት መላዋን ሮም አጥለቅልቆ በካቶሊክ እምነት ውስጥ ትክክለኛ ዶግማ ሆኖ ተቆጠረ ዛሬ ከካቶሊክ እምነት በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተገንጥሎ የወጣው የሉተር ተከታዮችም የሉክዮስን ክህደት ትክክለኛ ትምህርት አድርገው በመውሰድ መንፈስ ቅዱስን ከአብና ከወልድ የሠረጸ ነው ሲሉ ይሰማሉ ።

በ1870 ዓ. ም. የተቋቋመው የይሖዋ ምሥክሮች የተባለው ድርጅት ደግሞ ስለመንፈስ ቅዱስ ለየት ያለ ትምህርት ያስተምራል ። እንደ «ዋችታዎር ሶሳይቲ» እምነት መንፈስ ቅዱስ መለኮትነትም

(5) ሚስጥረ ሥላሴ ገጽ 133—137



www.ethiopianorthodox.org

ሆነ አካል የለወም ። እምነታቸውን እንዲህ ይገልጹታል « ይሖዋ ፍጥረቱን ያከናወነው ሰዎች በሚጠቁሙባቸው መሣሪያዎች ሳይሆን በማይታይ ፈጣን ኃይሉ ይኸወም በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው ። ሕምላክ በምድር ላሉ ሰዎች ያለውን ፈቃዱንና ዓላማውን እንድናውቅ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን ያስጻፈው በዚሁ መንፈስ ቅዱስ በኩል ነው» (6)

አርዮሳውያን ለማለት የፈለጉት መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፈጣን ፍጡር ኃይል እንጂ ፈጣሪ አይደለም ። ለየት ያለ ፍጡር ሆኖ የሚወርድ የሚወጣ የሚሄድ የሚመጣ ተላላኪ አድርገው ነው የሚወስዱት «ዮሐንስ መጥምቅ በውሃ ያጠምቅ እንደነበረ ሁሉ ኢየሱስም በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ዮሐንስ ራሱ ተናግሯል ። ውሃ አካል እንዳልሆነ መንፈስ ቅዱስም አካል አይደለም» (7) በማለት ያለምንም ማፈር ያስተምራሉ ። የሚገርመው ይህን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለውን ትምህርታቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳገኙት አድርገው ለማቅረብ መሞከራቸው ነው ። ለዚህም በዋቢነት የሚጠቀሰው «የአዲስቱ ዓለም የእንግሊዘኛ ትርጉም» ነው ። በ፪ኛ ጴጥ ፫ ፥ ፲፮ ላይ እንደተጠቀሰው «በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደ ሚያጣምሙ እነዚህን (ቅዱስት መጻሕፍትን) ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ» የይሖዋ ምስክሮችም የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ አባባል በራሳቸው አባባልና ትርጉም በመውሰድ ተርጉመውት ይገኛሉ ።

ለዚሁም ማስረጃ የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ያላቸውን ጥላቻና ክህደት ለመግለጽ «በአዲስቱ ዓለም ትርጉም» ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ስም ያለአግባቡ መጻፉ ነው ። በእንግሊዝኛው የማንኛውም ሰው ስም ሲጻፍ በትልቁ የእንግሊዝኛ ፊደል እንደሚጀምር የእንግሊዝኛውን የሰዋሰው ህግ የሚያወቅ ሰው ሁሉ የሚያስተውለው ነው ። አርዮሳውያን ግን መንፈስ ቅዱስን ፍጡርና ዝርው ኃይል ለማለት ስለፈለጉ ብቻ የመንፈስ ቅዱስን ስም በትንሹ የእንግሊዘኛ ፊደል ጀምረውት ጽፈውታል (HOLY SPIRIΓ) ይህም «በአዲስቱ

---

(6) ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራ እውነት ገጽ 5, Let God be true . 108
(7) ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራ እውነት ገጽ 24



ዓለም ትርጉም» በማቴ. ፳፰ ፥ ፲፱ ፪ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፲፬ ዮሐንስ ፲፬፥ ፳፮ የሐዋ ሥራ ፰፥ ፳፱ እንዲሁም በ፩ኛ ቆሮ ፲፪ ፥ ፫ እና በሌሎችም መንፈስ ቅዱስን በሚያነሳበት ቦታ ሁሉ (HOLY SPIRIT) ተብሎ መጻፍ ያለበትን (holy spirit ብለውታል ።

በተጨማሪም አካል የሌለው በይሖዋ ውስጥ የተከማቸ ብትን ሃይል ነው የሚለው እምነታቸውን በሌላው ሰው አእምሮ ውስጥ ለመቅረጽ የእንግሊዘኛውን የሰዋሰው ሕግ አሁንም ተጠቅመዋል ። ይኸወም (WHOM) በሚለው ቃል ምትክ (WHICH) የሚለውን በመተካት የቃላት ጨዋታ በመጽሐፉ ላይ ተጫውተዋል ። ለምሳሌ በዮሐንስ ወንጌል ፲፬ ፥ ፳፮ ሮሜ ፰ ፥ ፲፮ ኤፌሶን ፬ ፥ ፴ ። የቃሉን አገባብ እንዴት እንደተጠቀሙበት ለአብነት ያህል በዮሐንስ ፲፬ ፥ ፳፮ ላይ የተጠቀሰውን እንመልከት «the holy spirit which the Father will send in my name»

በዘመናዊ የእንግሊዘኛ ሰዋሰው ሕግ WHICH የሚለው ቃል የሚገባው ሰብአዊነት በእንግሊዘኛው (PERSONALITY) ለሌላቸው ነገሮች ነው ።«WHO» ግን (PERSONALITY) ላላቸው ይገባል ። እንግዲህ እነርሱ (WHICH ) በሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስን መግለጻቸው አካል የሌለው ዝርው ሃይል ነው የሚለው እምነታቸውን እንዲያንጸባርቅላቸው ሽተው ነው ።

በሌሎች የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱሳት ውስጥ ይህ አይነቱ ከአግባብ የወጣ ሁኔታ ባይኖርም አርዮሳውያን ግን ለእዚህ ትርጉማቸው ማስተባበያ አድርገው የሚያቀርቡት የመጀመሪያውን የእንግሊዘኛ ትርጉም የሆነውን የኪንግ ጀምስ ቨርሽንን ነው ። እንደ አርዮሳውያን አገላለጽ «በአዲስቱ ዓለም ላይ የታየው» የሰዋሰው ሕግ ማለትም «WHICH» የሚለው ቃል ለመንፈስ ቅዱስ መግለጫነት መዋሉ በኪንግ ጀምስ ትርጉምም ላይ የሚታይ እውነታ ነው ይላሉ ።

በመሠረቱ የኪንግ ጀምስ ቨርሽን የተተረጎመው በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደመሆኑ የእንግሊዘኛው የሰዋሰው ሕግም ለየት ያለ ነበር ከአሁኑ ዘመን ። ስለዚህ በዛን ወቅት WHICH የሚለው RELATIVE PRONOUN ለሰው መግለጫነት ይውል ነበር ። በዚህም የተነሣ ለመንፈስ ቅዱስም ተጠቅሞበታል ። አጠቃቀሙ ግን መንፈስ ቅዱስ አካል የሌለው (IMPERSONAL POWER)መሆኑን ለመግለጽ አይደለም ። ደግሞም የተጠቀመው ለመንፈስ ቅዱስ ብቻ



www.ethiopianorthodox.org

ሳይሆን ለአብም ለወልድም ጭምር ነው ። ይህንንም በማስረጃነት ማስተማሙን ይቻላል ። ጌታ በማቴ ፮ ፡ ፱ እና በሉቃ ፲፩ ፡ ፪ ላይ ስት ጸልዩ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ ያለውን የኪንግ ጀምስ ቮርሽን እንዲህ ጽፎታል « OUR FATHER WHICH ART IN HEAVEN » ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በተተረጎሙት መጽሐፍ ቅዱሶች ላይ WHICH የሚለው WHO በሚለው ተተክቶ እናገኘዋለን ምክ ንያቱም በዘመናዊው የእንግሊዘኛ ሰዋሰው ሕግ WHICH እኔ ባይ ለሆነ አካል ስለ ማይገባ ነው ። (8)

መቅዶናሳውያን ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስን ባይመሩበ ትም ለምስክርነት ይሆንባቸው ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት ሲገልጽ «የእውነት መንፈስ ወደ እውነት ይመራችኋል ሁሉን ያስተምራችኋል» ዮሐ. ወንጌል ፲፮ ፡ ፲፪ / ፲፫ ብሏል ። ለመሆኑ ዝርው ኃይል ሁሉን ነገር ሊያስተምር ይችላል? የሚሰማውን ሁሉ ይነ ግራችኋል ብሎ ጌታችን ኢየሱስ የተናገረለት እኔ ባይ ላልሆነ ዝርው ሃይል ይሆን?

## መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሠረጸ ነው

የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሥረጽ ነው ። ከማን ነው የሠረጸ? ቢሉ ከአብ ። ከአብ ወጣ ሲባልም አብን አህሎ መስሎ ተገኘ ማለት ነው ። ያለመቀዳደም ከአንድ የሻማ ብርሃን ሌላ ብርሃን እንደሚገኝ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ አብን አህሎ አብን መስሎ ከአብ ወጣ (ተገኘ) (ምሳሌው በሻማው ብርሃን እንጂ በሻማው ላይ አለመመ ሰሉን ልብ ይበሉ)

መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ለመሠረጹ ምን ማስረጃ አለህ? ቢሉ እንደሚከተለው ይጠቀሳል ።

<u>የዮሐንስ ወንጌል ፲፭ ፡ ፳፮</u> «ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላ ችሁ ጰራቅሊጦስ ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል»

---

(8) Jehovah's Witnesses PP (26-29)



ጌታችን እንደመሠከረው መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሚወጣ እንጂ ከወልድም የሚወጣ አይደለም ። ከወልድ የሚሠረጽማ ቢሆን ኖሮ ከእኔም የሚወጣው ብሎ በተናገረ ነበር ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሚወጣ ስለሆነ ከአብ የሚወጣ ብሎ አረጋገጠ ልን ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በማይታበል ቃሉ የመንፈስ ቅዱስን ከአብ ብቻ መውጣት እየተናገረ ተቃዋሚዎች ግን ከወልድም የሚሠርጽ ነው የሚለውን ስህተታዊ ትምህርታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ለማስደገፍ ያልሆነ ጥቅስ ሲጠቅሱ ይታያሉ ። ከእነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹን ቀጥለን እንመልከት

— <u>ገላትያ ፬ ፡ ፮</u> «ልጆች እንደመሆናችሁ መጠን እግዚአብሔር የልጅን መንፈስ በልባችሁ አሳደረ»

የልጅን መንፈስ ማለቱ ከልጅ (ከወልድ) የሚወጣ ማለቱ ነው ይላሉ ። ዳሩ ግን የልጅ መንፈስ የሚለው አባባል የመንፈስ ቅዱስን ከወልድ መሥረጽ የሚናገር ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የአብ ብቻ ሳይ ሆን የኢየሱስ ክርስቶስም ሕይወት መሆኑን ሊገልጽ ፈልጎ ነው «የልጁ ሕይወት የሚኾን መንፈስ ቅዱስን በልቡናችሁ አሳድ ሮታል» (9)

መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ ሕይወታቸው መሆኑን እነርሱም የሚ ክዱት አይደለም ። ስለሆነም ብርሃነ ዓለም ጳውሎስም የመንፈስ ቅዱ ስን ሕይወትነት ሊገልጽ ብሎ እንጂ የመንፈስ ቅዱስን ከወልድ መሥ ረጽ ሊያስተምር አይደለም ። ይህማ ከሆነ የጌታን ቃል ማስተባበሉ ነውና ምኑን ክርስቶስን መሰለው? ዮሐ ፡ ወንጌል ፲፭ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ፡ ፳፮ ፡

መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ እስትንፋስ መሆኑን ካመናችሁ ታዲያ እንዴት ከወልድ አይወጣም ትላላችሁ? ሊሉ ይችሉ ይሆናል ። እንዲህማ ከተባለ ወልድ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው ። ከእርሱ ሌላ መናገሪያ ቃል የላቸውም ። ስለዚህ ወልድ የሁለቱም ቃል ነውና ከአብ ብቻ ተወለደ ብሎ መናገሩ ስህተት አይሆንም? የመንፈስ

---

(9) የጳውሎስ ንባቡ ከነትርጓሜው ገጽ 373



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስም ቃል ነውና ከመንፈስ ቅዱስም ተወለደ ማለት ይገባናል ማለታቸው እንደሆነ አስተውለውታል? እንዲህ አይነት እምነት ደግሞ እስከ አሁን አልተፈጠረምና እነርሱ ሊፈጥሩ በዝግጅት ላይ እንዳሉ ይጠቁምባቸዋል እንላለን ።

— ዮሐንስ ወንጌል ፲፮ ፡ ፯ «እኔ ካልሔድኩ ጰራቅሊጦስ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ከሔድኩ ግን እርሱን እሰድላችኋለሁ» ይህን ጥቅስ በመጥቀስ መንፈስ ቅዱስን ወልድ እሰድላችኋለሁ ማለቱ የሚያሰርጸው ስለሆነ ነው እንጂ የማያሰርጸውማ ቢሆን እንዴት ብሎ እሰድላችኋለሁ ሊል ቻለ? ይላሉ ።

እዚህ ላይ ጌታ መንፈስ ቅዱስን እሰድላችኋለሁ ማለቱ አካሉን ሳይሆን ጸጋውን ነው ። ይህንንም ጌታ ሲገልጽ «እነሆ እኔ የአባቴን ተስፋ ለእናንተ እልካለሁ» ሉቃ ፳፬ ፡ ፵፱ ብሏል ። የአባቴን ተስፋ ማለቱ የመንፈስ ቅዱስን ልዩ ልዩ ስጦታ ማለት ነው ። አይደለም አካሉን ነው እንጂ የላከላቸው ካሉ ግን እንግዲያው ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን የመንፈስ ቅዱስ አካል ወርዶ ስላደረባቸው የጸጋ አማልክት መሆናቸው ቀርቶ የባሕርይ አማልክት ሆኑ ማለት ይሆናል ይህ ደግሞ ልዩ ወደር የማይገኝለት ክህደት ነው ።

ወልድ መንፈስ ቅዱስን እልካለሁ ካለ ከወዴት አምጥቶ ይልከዋል ከራሱ ካለወጣው በስተቀር የሚል አመለካከት ካላቸው እንደዚሁም ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ጋር ሆኖ ወልድን እንደላከው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሠፍሯል «አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል» ትንቢተ ኢሳያስ ፵፰ ፡ ፲፮ ተላኪው ወልድ ለመሆኑ ከላይ ከፍ ብሎ ተጠቅሷል «እኔ ከጥንት ጀምሮ በስውር አልተናገርሁም ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ» ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በቅድምና ያለ የነበረ መሆኑን ሲገልጥ ነው ። እንግዲህ መንፈስ ቅዱስም ወልድን እንደላከ ስለተነገረ ከየት አምጥቶ ላከው ካልወለደው በስተቀር? የሚል አደናጋሪ ጥያቄ የሚያስከትልባቸው መሆኑን አላስተዋሉት ይሆን? የወልድን ከአብ ብቻ መወለድ ክደው ከመንፈስ ቅዱስም ተወልዷል የሚሉ ከሆነ ከመሠረታዊ የክርስትና እምነት መውጣታቸው ነው ። አብ መሠረት ነው ወልድን ይወልዳል መንፈስ ቅዱስን ያሰርጻል ። መንፈስ ቅዱስ ቢሠርጽ እንጂ አይወልድም አይወለድም ። ወልድም ቢወለድ እንጂ አይወልድም አያሠርጽም አይሠርጽም ። እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው የሥላሴ መሠረት አንድ ነው እርሱም አብ ነው ። ተብሎ ፡ቅዱሳን አበው እንደተነገረ ።



«ከአብ በሠረፀ በወልድ በተገለጠ በተመሰገነ ከአብ ከወልድ ጋር ለሚሰገድለት በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን» መንፈስ ቅዱስ መባሉ ከአብ ስለሠረፀ ነው ለአብ ለወልድ እስትንፋሳቸው ስለሆነ ነው ...... መንፈስ ቅዱስ ዓለም ሁሉ ሳይፈጠር ከአብ ተገኝቶ ፡ዘሠራዊነት ይኖራል ። ከአብ ሠረፀ እንጂ እንደ ወልድ አልተወለደም» (10)

«መንፈስ ቅዱስ ከሌላ ባሕርይ ከሌላ አካል አልተገኘም የወልድ መገኛ ከሚሆን ከአብ አካል ከአብ ባሕርይ ነው እንጂ በጊዜው ሁሉ ቀዳማዊ የሚሆን መንፈስ ቅዱስ ከአብ ተገኘ ከእርሱም ተገኝቶ ታወቀ ...... በቅድምና የነበረ መንፈስ ቅዱስ ዘመን ሳይቀድመው ከአብ ተገኘ» (11)

— ዮሐንስ ወንጌል ፲፮ ፡ ፲፬ «...... እርሱ እኔን ይገልጻል ከእኔ ገንዘብ አድርጎ ይነግራችኋልና»

ይህን ጠቅሰው መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ይሠርጻል ይላሉ ። ከእኔ ገንዘብ አድርጎ ይነግራችኋልና የሚለውን ወስደው ከሆነ መንፈስ ቅዱስን ከወልድም ይወጣል ያሉት እጅግ ተሳስተዋል ። የቃሉን ትክክለኛ ትርጉም እንደሚከተለው ተገልጾአል «አካላዊ ቃልም ጰራቅሊጦስን እሰድላችኋለሁ ቃልነትንም ከእኔ ገንዘብ አድርጎ ይነግራችኋል ማለቱ በዚህ በመለኮት አንድነት ያለውን አንድነት ያስተምረናል» (12)

በእኔ ቃልነት ይነግራችኋል ማለትና ከእኔ ይሰርጻል የሚለው አባባል እጅግ የሰማይና የምድር ያህል ርቀት አለው ።

ቤተክርስቲያናችን ስለ ቅድስት ሥላሴ ጥርት ያለና የነጠረ ትምህርት አላት ። በዚህ ትምህርትዋ ላይ የሥላሴን የባሕርይ አንድነት ከግብር ሦስትነትና ከአካላት ሦስትነት ጋር ቀላቅላ አትናገርም ።

---

(10) ሃይማኖተ አበው — ዘመቃርስ ገጽ 435 — 436
(11) ሃይማኖት አበው — ዘኪራኮስ ገጽ 397—398
(12) ሃይማኖተ አበው — ዘካርያስ ገጽ 493



www.ethiopianorthodox.org

በምስጢረ ሥላሴ ትምህርት ላይ የሥላሴ ሥራ በሁለት ተከፍሎ ይነገራል ።

አንደኛው የአካላት ሥራ ነው መውለድ ፡ መወለድ መሥረጽ ተብሎ ይታወቃል ። በእዚህ የአንድ አካል ሥራ ከአንድ አካል አይተላለፍም ። አብ አብ ብቻ ይባላል ። ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይባልም ። ወልድና መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ከእዚህ አልፈን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መሆን ይችላል ። ወልድም አብ መንፈስ ቅዱስ መሆን ይችላል ወልድም አብ መንፈስ ቅዱስ መሆን ይችላል መንፈስ ቅዱስም አብ ወልድ መባል ይችላል ከተባለ ሥላሴ ሦስት አካል መሆኑ ቀርቶ ዘጠኝ አካል ሊሆን ነው ። ይህ ሁሉ እንዳይሆን የግብር ሦስትነት ማለት የአብ ግብሩ መውለድ ማስረጽ የወልድ ግብረ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መስረጽ መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅ ነው ። (13) እንግዲህ መንፈስ ቅዱስን ከአብ ብቻ ሳይሆን ከወልድም ይሠርጻል ካሉ ከላይ የተጠቀሰውን ዘጠኝ አካላት መፍጠራቸውነው ምክንያቱም አብ አብ ብቻ ሆኖ አይቀርም ወልድ ይሆናል ወልድም ወልድ ብቻ ሆኖ አይቀርም አብ ይሆናል ራሱን በራሱ ይወልዳል መንፈስ ቅዱስም አብ ወልድ ይሆናል ራሱን በራሱ ያሰርጻል እንግዲህ ከተቀደሰው ከሐዋርያት እምነት ወጥተን በሥላሴ ባሕርይ መጫወታችን መሆኑን አንዘንጋ ።

ሁለተኛው የሥላሴ ሥራ አብ የሚሰራውን ወልድ ወልድ የሚሠራውን መንፈስ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን አብና ወልድ የሚሠሩት ሥራ ነው ። ይኸውም መፍጠር ፡ መግደል ፡ መሥጠት ፡ መንሣት መጠበቅ ማሳለፍ ይህን የመሳሰሉት ። ለእዚህም ማስረጃ ጌታ የተናገረውን መጥቀስ እንችላለን ። «የእኔ የሆነ ሁሉ ያንተ ነው የአንተ የሆነም የኔ ነው በእነሱ ተመስገንኩ» ዮሐ ወን. ፲፯ ፡ ፲ ካለ በኋላም «...... ቅዱስ አባት ሆይ የሰጠኸኝን በስምህ ጠብቃቸው በእኛ እንደ እኛ ይሆኑ ዘንድ እንዲሁም «የምነግራችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ግን ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል ከራሱ አንቅቶ አይናገርምና የሰማውን ይናገራል እንጂ የሚመጣውንም ይነግራችኋል» ዮሐንስ ወን

---

(13) ምስጢረ ሥላሴ 144—146



፲፮ ፡ ፲፪—፲፫ ። ከዚህ የምንረዳው መንፈስ ቅዱስ ከርሱ ብቻ አውጥቶ እንደማይናገር ከአብ ከወልድ በህላውና የሰማውን ማስተማሩን ነው ። ስለዚህ ከእኔ ይወስዳል ሲል የህልውና አንድነታቸውን ሲገልጽልን ነው እንጂ ከእርሱ የሚሠርጽ መሆኑን አይደለም ።

## መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እስትንፋስ ነው

መንፈስ ቅዱስ ዝርው ኃይል አይደለም ። እንደ አብና እንደ ወልድ ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ያለው ነው ። እኔ ማለት የሚችል ነው ። መንፈስ ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለተጠራ አካል የለውም የሚለው አባባል ከደካማ አስተሳሰብ የመነጨ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» ዮሐ. ወን ፬ ፡ ፳፬ ። ማለቱ አካል የለውም ማለቱ እንዳልሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስንም መንፈስ ብሎ መጥራቱ አካል የሌለው ለማለት አይደለም ። እግዚአብሔር አካል ያለው ሲሆን ነገር ግን እንደ ፍጡራን ውሱን አይደለም ። እግዚአብሔር በዓለምና ከዓለም ውጭ ያለ የሌለበት ቦታ የሌለ ምሉዕ ስፉህ ነው ። ለዚህም የልበ አምላክ የዳዊትን አባባል ብቻ መጥቀሱ በቂ ነው ። «ሰማየ ሰማያት ብወጣ አንተ በዚያ አለህ ወደ ባህር ብጠልቅ አንተ በዚያ አለህ የሌለህበት ቦታ የለም» እግዚአብሔር የሚከፋፈልና የሚበታተን አካል ያለው አይደለም ነገር ግን በፍጹም መለኮቱ እሱው ራሱ በኹሉም ቦታ ይገኛል ።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እስትንፋስ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ያስረዳናል ።

— አሪት ዘፍ ፲፰ ፡ ፩ ። — በሰው አምሳል ከተገለጡት ከሦስቱ አካላት አንዱ መንፈስ ቅዱስ ነው

— ማቴዎስ ፫ ፡ ፲፮ ። ......የእግዚአብሔር መንፈስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አየ»

የእግዚአብሔር መንፈስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ለመሆኑ የሚያጠራጥር ነገር አይኖርም ። እንግዲህ በርግብ አምሳል መውረዱ ዝርው ኃይል ሳይሆን አካላዊ መሆኑን ሲያስገነዝበን ነው ። ብትን ሃይል ቢሆን ኖሮማ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ባልተቀመጠ ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

— <u>ዮሐንስ ወንጌል ፲፬</u> ፣ ፲፮ እና ፳፮ «እኔም አብን እለምነዋለሁ ጰራቅሊጦስንም ሌላውን አካል ይልክላችሁአል ለዘላለም ከእናንተ ጋር ይኖር ዘንድ »

በአዳዲስ እትሞች ላይ ጰራቅሊጦስ የሚለው <u>ሌላ አጽናኝ</u> በሚለው ተተክቷል ሌላውን አካል የሚለው እርሱም በሚለው ተተክቷል ። ይህም ቢሆን የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት የሚያስተባብል አይደለም ።

<u>ሌላ አጽናኝ</u> (ጰራቅሊጦስ) ሲል ፍጽም ገጽ ፍጹም መልክዕ ያለው ልዩ አካል መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን ሌላ ሲል ከአብና ከወልድ የተለየ ሦስተኛ አካል ማለቱ ነው ። እርሱም የሚለው አባ ባልም ከአብና ከወልድ በተለየ አካል ያለ ልዩ በአካላት ሦስት ከሆኑት አንዱ እኔ ባይ አካል መኖሩን የሚገልጽ ነው ። «ነገር ግን አብ በስሜ የሚልክላችሁ የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስ እርሱ ሁሉን ያስተምራችሁአል እኔ የነገርኩአችሁንም ሁሉ ያሳስባችሁአል» ከዚህ የምንረዳው መንፈስ ቅዱስ የእውነት አስተማሪና መሪ እንደሆነ ነው እንግዲህ ብትን ኃይል ሁሉን ማስተማር ይችላል? ማሳሰብስ ይቻለዋል? መናገርስ ይቻለዋል? በእዚሁ በዮሐንስ ወንጌል በም ፲፮ ፣ ፲፫ «......ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» ተብሎ እንደተገለጸው መንገድ ማሳየት፡ መምራት ይቻለዋል? እርሱ ተብሎስ ብትን ለሆነ ኃይል ይነገራል? በፍጹም ። አካል የሌለው እስትንፋስ ወይም መንፈስ እርሱ ተብሎ አይጠራም ። ወደ እውነትም አይመራም መናገርም አይችልም መንፈስ ቅዱስ ግን አካላዊ እስትንፋስ ስለሆነ ከላይ የተጠቀሰው ሁሉ ሲነገርለት ተችሎዋል ።

— <u>ትንቢተ ኢሳያስ ፵፰ ፣ ፲፮</u> «አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል» በዘህ ላይ እግዚአብሔር ብሎ አብን መንፈስ ብሎ መንፈስ ቅዱስን ማመልከቱ ነው እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በአብ ውስጥ የተከማቸ ብትን ኃይል ነው ከተባለ ወልድን እንዴት ሊልክ ቻለ? መላክስ ይቻለዋል? ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው ያለው እንጂ መቼ መንፈስ ቅዱስ አለ እንዳይባል ። እግዚአብሔር ብሎ እና በሚለው ቃል በማያያዝ ሌላ አካል እንዳለም ገለጸ እንጂ የእግዚአብሔር መንፈስ ብሎ አንድ አካል ብቻ አድርጎ አላቀረበም ። ልከውኛል የሚለው ቃል የሚያመለከተው ሁለትነትን እንጂ አንድነትን አይደለም ።



«ከአብ በሠረጸ ከአብ ከወልድ ጋር አንድ በሚሆን እንደ አብ እንደ ወልድ ፍጹም አካል ባለው በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን ። እንዲሁም በአካሉ በገጹ ጸንቶ ያለ ነው» (14) በማለት ቅዱሳን አበው መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርገው ያስረዳሉ ።

## የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክነት

«መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር የነበረ ያለ የሚኖርም ነው እርሱ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው» ፣ (15) የቀደሙት አበው መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሰው ይመሰክራሉ ።

— <u>ኢዮብ ፳፮ ፣ ፲፫</u> «በመንፈሱ ሰማያት ውበትን አገኙ......»

የእግዚአብሔር መንፈሱ ተብሎ የሚጠራው መንፈስ ቅዱስ ነው ። በመንፈስ ቅዱስ ሰማያት ውበትን እንዳገኙ እንደተፈጠሩ ኢዮብ መሰከረ ።

— <u>መዝ ፴፪ ፣ ፮</u> «በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ» የእግዚአብሔር እስትንፋስ መንፈስ ቅዱስ ነው ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ፍጥረታትን የፈጠረ ያጸና እንደሆነ ዳዊት መሠከረ <u>ዘኍልቅ ፮፣ ፳፬ ፣ ፳፮</u> «እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም ፣ እግዚአብሔር የፊቱን ብርሃን ይግለጥልህ ይራራልህም ፣ እግዚአብሔር በምህረት ዐይን ይመልከትህ ሰላሙንም ይስጥህ»

ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር ማለቱ ያለምክንያት አይደለም ። አብ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስን መጥራቱ ነው እንግዲህ ሦስተኛው «እግዚአብሔር በምህረቱ አይን ይመልከትህ ሰላሙን ይስጥህ » የሚለው ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከሆነ መሐሪ ሰላምን የሚያድል የባሕርይ አምላክ እንደሆነ መግለጹ ነው ።

— <u>መዝሙር ፻፲፯ (፻፲፰) ፣ ፲፭ እና ፲፮»</u> የእግዚአብሔር ቀኝ ሃይልን አደረገች የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገች የእግዚአብሔር ቀኝ ሃይልን አደረገች»

---

(14) ሃይማኖት አበው — ዘካርያስ ገጽ 491
(15) ሃይማኖተ አበው — ዘኪራኮስ ገጽ 398



www.ethiopianorthodox.org

ይህን ቃል ስናነብ ተገርመን ይሆናል ። ወይም የሕትመት ስህ
ተት ነው ብለን ጠርጥረንም ይሆናል ። ዳሩ ግን የሕትመት ስህተት
ሳይሆን ሆን ተብሎ ከመጀመሪያው የተጻፈ ነው ዳዊት ተመሳሳይ
ቃልን ማስፈሩ ለምክንያት ነው ። በተለይ በመጀመሪያውና በመጨ
ረሻው ላይ ምንም አይነት የቃል ልዩነት የለም መሐከለኛው ላይ
ያለው ግን ከፍ ከፍ አደረገችኝ ብሎ እናገኘዋለን ። ተራውን ጠብቀን
የመጀመሪያውን ለአብ መካከለኛውን ለወልድ ሦስተኛውን ለመን
ፈስ ቅዱስ ሰጥተን እንናገራለን ለምን ሦስቱም አንድ አይነት ዓረፍተ
ነገር አልያዙም የሚል ጥያቄ በአእምሮአችሁ ሊቀረጽ ይችል ይሆ
ናል የመሐከለኛው ለየት ባለ ቃል መገለጹ አሁንም ምስጢር አለው
ከሦስቱ አካል በተለየ አካሉ በቃልነቱ ከዊን ከቅድስት ድንግል ማር
ያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ አዳምን ከተዋረደበት ከወ
ደቀበት የኃጢአት የመርገም ማጥ ያወጣውና ወደ ቀድሞ ክብሩ
የመለሰው ተዋርዶ የነበረው ባሕርይውን ከፍ ከፍ ያደረገው እርሱ
ስለሆነ ይህን ለማመልከት ነው ። እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ እግዚ
አብሔር ተብሎ መጠራቱን ልብ በሉ ።

— 2ኛ ቆሮ ፲፫ ፣ ፲፬ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፣ የእግዚ
አብሔርም ፍቅር ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ፣ ከሁላችሁም ጋር ይሁን
አሜን»

መንፈስ ቅዱስ በመለኮት በህልውና ከአብና ከወልድ ጋር አንድ
ስለሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ኅብረት እንዲሰጠን በኃይሉ እንዲያበረታን
ጸለየልን ። ስሙ የሚባርክ የሚቀድስ መሆኑን አስረዳን ።

— ማቴ. ፳፰ ፣ ፲፱ «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ»
በመንፈስ ቅዱስም ስም መጠመቅ እንዳለብን ጌታ ራሱ አስረዳን
የባሕርይ አምላክ ባይሆን ኖሮ በስሙ ለመጠመቅ ባልተገደድን
ነበር ።

— 1ኛቆሮ. ፪ ፣ ፲—፲፪ «መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን
ጥልቅ ባሕርዩን ይገልጣልና»

ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ ሲያስረዳ
«ባንድ ሰው ልብ ያለውን የሚያውቅ ማነው? ተዋሕዳው ያለች
ነፍስ ብታውቅ እንጂ ሌላውማ ሰው እንዴት ሊያውቅ ይችላል ።



እንዲሁም ሁሉ በእግዚአብሔር ህልውና ካለ ከመንፈስ ቅዱስ በቀር
የእግዚአብሔርን ምስጢር የሚያውቅ ማንም የለም ብሎ መንፈስ
ቅዱስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ አረጋግጦልናል ። የአበውንም
ምስክርነት ብንሻ «ዳግመኛም መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር
እኩል ትክክል እንደሆነ ከአብ ከወልድ መለኮታዊ ባህርይ ልዩ እን
ዳይደለ እናምናለን ልዩ ነው ማለት አይገባም» (16)

«መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ነው አስቀድመን እንደተና
ገርን መገኘቱ ከአብ ነው እንጂ ከሌላ አይደለም» (17)

## የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ

መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ወረደ ሲባል አንዳንዶቹ የመን
ፈስ ቅዱስ አካሉ የወረደባቸው ይመስላቸዋል ይህ ግን የተሳሳተ አመ
ለካከት ነው ። በመንፈስ ቅዱስ አካልና ስጦታ መካከል ያለውን
ልዩነት ጠንቅቀን ማወቅ ከስህተት ላይ ከመውደቅ ያድነናል ።

የመንፈስ ቅዱስ አካሉ ሳይሆን የሚሰጠው ጸጋው ነው መጽሐፍ
ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በተለያየ አገላለጥ ይገልጸዋል ። አንድ
ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሌላ ጊዜ መንፈስ እያለ ይጠራዋል ። ለአብነት
ያህል ብንጠቅስ ዮሐንስ ወን ፫ ፣ ፴፬ «እግዚአብሔር መንፈሱን
ሰፍሮ አይሰጥምና ......» መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና ሲል የእግዚ
አብሔር መንፈስ እንደማይሠፈር ጸጋውም ልክ ወሰን የሌለው
መሆኑን መግለጽ ነው ።

ሐዋ ሥራ ፲፱ ፣ ፪ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?» አላቸው
የመንፈስ ቅዱስን አካል ማለቱ ሳይሆን ጸጋውን ማለቱ ነው ሐዋ ሥራ
፲ ፣ ፵፬ «ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ» አሁንም
አካሉ ማለት አይደለም ስጦታውን ለማለት ነው ። የዚህን አባባል
ትርጉም በዚህ ምዕራፍ በቁጥር ፵፭ ላይ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል
«......በአሕዛብ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለፈሰሰ ተገረሙ» ይላል ።

---

(16) ሃይማኖተ አበው — ዘካርያስ ገጽ 491
(17) ሃይማኖተ አበው — ዘኪራኮስ ገጽ 398



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ አንድ ጊዜ መንፈስ ሌላ ጊዜ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እያለ ይጠረዋል ። እንዲህ ካልሆነ ግን ማለትም የመንፈስ ቅዱስ አካሉ ነው የሚሰጠው የሚወርደው ከተባለ የእግዚአብሔርን ምሉዕነት ስፋህነት አለማወቅ መሆኑን ያሳያል ። እንዲሁም እግዚአብሔር ፍጡር ይመስል መመጣት መውረድ የለበትም ።

የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ይዘረዝረዋል «የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ ፣ የምክር የኃይል መንፈስ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ......» ትን ኢሳ ፲፩ ፥ ፲፪ ።

ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ ደግሞ «የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው (አካሉ አንድ ሲሆን ስጦታው የበዛ ነው ማለቱ ነው) ለእያንዳንዱ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ስጦታው ልዩ ልዩ ነውና ለሁሉም ጌታ እየረዳ እንደ ዕድሉ ይሰጠዋል ለየአንዳንዱ እንደሚገባውና እንደሚጠቅመው በግልጥ ይሰጠዋል የጥበብ ቃል የሚሰጠው አለው በመንፈስ ቅዱስም የዕውቀት ቃልን የሚሰጠው አለው በመንፈስ ቅዱስ ሃይማኖትን የሚሰጠው አለው ድውይ የመፈውስ ሥልጣንም የሚሰጠው አለው የእርዳታና የኃይል ሥራን የሚሰጠው አለው ትንቢት መናገርን የሚሰጠው አለው በመንፈስ ቅዱስ ትርጓሜ ማወቅን የሚሰጠው አለው የየአገሩን ቋንቋ እንዲያውቅ ትርጓሜን የሚሰጠው አለው ። በዚህ ሁሉ ሁሉንም የሚረዳቸው መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው ነገር ግን ለሁሉም እንደወደደ ያድላቸዋል» ፩ኛ ቆሮ ፲፪ ፥ ፬—፲፩

የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል የሚለውን ዘንግተው አንዳንዶች የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ መጫወቻ ሲያደርጉት ይታያሉ ።

## የልሳን ስጦታ

የልሳን ትርጉም ፣ የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ የልሳንን ትርጉም እንዲህ ይፈታዋል ።

ልሳን ፣ በቁሙ ምላስ አንደበት የአፍ ውስጥ ሕዋስ የመብል የነገር መማሪያ (ያዕ ፫ ፥ ፭—፮ መዝ ፭ ፥ ፲፩)



በዕርሱ መማሪያነት የሚነገር ቃልና ቋንቋም ከርሱ ስም ነስቶ ልሳን ይባላል (18)

ዳሩ ግን በአንዳንድ ክፍሎች ዘንድ የልሳን ትርጉም በአግባቡ የታወቀ አይመስልም ። በልሳን መናገርንም የማይታወቅ ልዩ የሆነ ተሰምቶ የማያውቅ ቋንቋ አድርገው ይወስዱታል ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የተለያዩ አገሮች መግባቢያ ቋንቋ መሆኑን ይነግረናል ። ማርቆስ ፲፮ ፥ ፲፯ «በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ» ማለቱ በዓለም ላይ ባልነበረ ልዩ በሆነ ቋንቋ ይናገራሉ ማለቱ ሳይሆን እነሱ ያወቁት ባልነበር የሌሎች ዜጎች ቋንቋ በሆነ በተለያዩ ሀገሮች ቋንቋ ይናገራሉ ማለት ነው ። ይኸውም ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ነው ።

ለሐዋርያት ልሳን ተገለጠላቸው ሲባል በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ክፍሎች ዘንድ እንደሚስተዋለው ዓይነት አልነበረም ። ሐዋርያት የተናገሩት ሰው የማይሰማውን የመላእክት ቋንቋ አይደለም ወይም የሌላ ፍጡር ቋንቋ ፤ የልሳን ስጦታ የተሰጣቸው ዓለምን ዞረው ያስተምሩ ዘንድ ስለሆነ በዓለም ላይ ይነገር የነበረው የሀገሮች ሁሉ ቋንቋ የተገለጸላቸው ወንጌልን በእያንዳንዱ ቋንቋ እንዲያስተምሩ ነው ። ደግሞም ሰማእያኑ (ሰሚዎቹ) የሚረዱት የሚያውቁት ቋንቋ እንደነበረም በሐዋ ሥራ ፪ ፥ ፮ — ፲፩ ያለውን ብቻ ማየቱ በቂ ነው ። «......ሁሉም ቢያገራቸው ቋንቋ ሲናገሩ ሰምተዋቸዋልና ደንገጡ አደነቁ እንዲህም አሉ እነዚህ ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን እንግዲህ በየሀገራችን ቋንቋ ሲናገሩ እንዴት እንሰማቸዋለን......»

በየሀገራችን ቋንቋ ሲናገሩ እንዴት እንሰማቸዋለን! የሚለው አባባል የሚያስገነዝበን ቢኖር ሐዋርያት በወቅቱ የተገለጸላቸውና የተናገሩት ሰሚዎቹ ያውቁት ይናገሩት የነበረው ቋንቋ መሆኑን ነው እንጂ እንደ አሁኖቹ ልሳን ተሰጠን ባዮች ሰውነታቸው እየተንዘፈዘፈ እጃቸውና እግራቸው እየራደ መላ ሰውነታቸው እንደ እስክስታ ወራጅ ሆኖ በዛር ዓይነት ቋንቋ አልነበረም ሲናገሩ የነበሩት ።

ታዛቢዎቹ እራሳቸው ማለትም ሰሚዎቹ የራሳቸው ቋንቋ መሆኑን የመሰከሩለት ነው ። «..... እነሆ የእግዚአብሔርን ጌትነት በየሀገራችን

---

(18) ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት



www.ethiopianorthodox.org

ቋንቋ ሲናገሩ እንሰማቸዋለን» ሐዋ. ፪ ፥ ፲፩።የዘመናችን ልሳን ተናጋሪዎች ግን የሚቀባጥሩት ልሳን ተብየው ከሰሚዎቹ አልፎ የቋንቋ ሊቃውንትን ሁሉ ሳይቀር ፈትኗል እንኳን በአሁኑ ዘመን ሊነገር ቀርቶ በመሠረቱ በዓለም ውስጥ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ይነገርበት እንደነበር ሁሉ አጠራጣሪ ሆኑአል ። እንግዲህ እንዲህ አይነቱን አደናጋሪ ነገር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ልንለው እንችላለን? በሁሉም ሊቃውንት ዘንድ እንደሚታወቀው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አከራካሪ አወዛጋቢ አጠራጣሪ አፍራሽም አይደለም ። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬው ጳውሎስ እንደጻፈው»...... ፍቅር ደስታ ሰላም ትዕግሥት ምጽዋት ቸርነት ሃይማኖት ገርነት ንጽሕና ነው ገላ ፭ ፥ ፳፪ ።

የቤተክርስቲያን ብርሃን ተብሎ የሚጠራው ጳውሎስ ዳግመኛ ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲገልጽ «እንዲሁ እናንተም በመንፈስ ቅዱስ ለሚሆን ነገር ተፎካከሩ ትበዙም ዘንድ ቤተክርስቲያን የሚታነጽ በትን ግብር (ሥራ) ሹ (ፈልጉ)» ፩ኛ ቆሮ. ፲፬ ፥ ፲፪ ።

እንግዲህ የአሁኑ ዘመን የልሳን ስጦታ ጳውሎስ እንዳለው ቤተ ክርስቲያን የምትታነጽበት ነው? የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽና ለጥቅም እንደሆነ ተጠቅሷል የቤተክርስቲያን መታነጽ ሲባል ምን ማለት ነው?

ቤተክርስቲያን ከሚለው ቃል ትርጉም እንነሣ ቤተክርስቲያን የሚለው የግእዝ ቃል በዘይቤም በምስጢርም ሦስት ዓይነት አወጣጥ አለው (19)

፩ኛ. እግዚአብሔር የሚቀደስበት የሚመሰገንበት አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት ልዩ ቦታ ። ቤተክርስቲያን ይባላል ።

የክርስቲያኖች መኖሪያ ማለት ነው ፩ኛ ጢሞ. ፫ ፥ ፲፬ — ፲፮ ።

፪ኛ/ በክርስቶስ ደም የተዋጀ በአርባና በሰማንያ ቀን ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማህጸነ ዮርዳኖስ (በጥምቀት) የተወለደ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ይባላል ፩ኛ ቆሮ. ፫ ፥ ፲፮ ።

(19) የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ 10



፫ኛ/ የክርስቲያኖች አንድነት ማኅበር ስብሰባ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይጠራል ፩ኛ ጴጥ. ፭ ፥ ፲፫ ፩ኛ ቆሮ ፲፬ ፥ ፴፭ ።

የቤተ ክርስቲያን ፍቺ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን መታነጽ ሲባል እንግዲህ የእያንዳንዱ ምእመን በሃይማኖት በምግባር በትሩፋት የሚበለጽግበት ማለት ነው ።

በአንድ የቤተክርስቲያን ጉባኤ ላይ አንድ ሰው ብድግ ብሎ ሰሚዎቹ በማያውቁት ማንም ሰው ሊረዳለት በማይችለው በእርሱ እምነት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ ለመሞላቴ ምስክር ነው ብሎ ቢቀባጥር ይሄ ጉባኤ ያገኘው ትምህርት የታነጸበት ነገር አለ ወይ? እንደውም በጥርጥር ማእበል ሰውን ከመክተት በስተቀር የሚያንጸው ምንም ነገር የለም ።

ሰውነቱ? ወባ እንደያዘው ሰው መድረክ ላይ ወጥቶ ቢንዘፈዘፍ ጭንቅላቱን እየናጠ የዛር ይሁን የቃልቻ ውሉ በማይታወቅ ቋንቋ ቢለፈልፍ ይኸን ሰው እብድ እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተቃኘ ነው ለማለት አያስደፍርም ።

እንኳን በዓለም ውስጥ የሌለን ቋንቋ ቀርቶ በሌላ አገር ቋንቋ እንኳ ተናጋሪዎቹና ሰሚዎቹ በሌሉበት መናገሩ አስፈላጊ አይደለም ጳውሎስ ይህን ሲነቅፍ «በቋንቋ የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው የሚናገር አይደለም የሚናገረውን የሚሰማው የለምና በልቡና የተሰወረውን ይናገራል እንጅ የሚተረጉም ግን ለሰው ይናገራል እንዲበረታ ደስ እንዲለውና እንዲረጋጋ በቋንቋ የሚናገር ራሱን ያንጻል የሚተረጉም ግን የክርስቲያንን ማህበር ያንጻል ።...... ሳይተረጉም በቋንቋ ከሚናገር ይልቅ የሚተረጉም እጅግ ይበልጣልና ቢተረጉም ግን ሕዝቡን ያንጻል ።...... በማታውቁት ቋንቋ ባነጋግራችሁ የምጠቅማችሁ ጥቅም ምንድነው ገልጬ ካልነገርኩአችሁ የጥበብ ነገርንም ቢሆን የትርጉሙ ስልትንም ቢሆን የማስተማር ሥራንም ቢሆን በዓለም ውስጥም ነፍስ የሌለው ድምጽ የሚሰጥ እንደመሰንቆ እንደ እንዚራ ያለ መሣሪያ አለ በስልቱ ካልመቱአቸውና ካልተናገሩ መሰንቆውስ እንዚራውስ የሚለውን ማን ያውቃል ። መለከት የሚነፋም በታወቀው ስልት ካልነፉ ለሰልፍ ማን ይዘጋጃል ።

እናንተም በቋንቋ ብትናገሩ ይህንንም ገልጣችሁ ባትተረጉሙ የምትሉትን የምትናገሩትን ማን ያውቃል ከነፋስ ጋር እንደምትነጋ



www.ethiopianorthodox.org

ገሩ ትሆናላችሁ ። በዓለም ብዙ አሕዛብ አሉ ቋንቋቸውም አነጋገራቸውም እየራሳቸው ነው ሁሉም በአገሩ ቋንቋ ይናገራል ። የነገሩን ትርጓሜ ኃይለ ቃሉንም ካለወቅሁ እኔ ለሚያነጋግረኝ እንደ ዲዳ እሆን በታለሁ የሚያነጋግረኝ እሱም አእምሮውን ያጣ ይመስለኛል» ፩ኛ ቆሮ. ፲፬ ፥ ፮—፲፮ ።

እንግዲህ ብዙ ቋንቋ የመናገር ስጦታ የተሰጠው ጳውሎስ እንኳን «ከሁላችሁ ይልቅ እኔ በቋንቋ እና ገራለሁና (ሰባ ሁለት ቋንቋ ተገልጾለታል) በዚህም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን አምስት ቃላትን ልናገር በልቤ እሻለሁ ለሌሎችም አስ ተምር ዘንድ በቋንቋ ከሚነገር ብዙ ቃል ይበልጣልና ።» ፩ኛ ቆሮ. ፲፬ ፥ ፲ ፥ ፳ ።

ስለዚህ በማያንጽ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተብሎ ከሚቀባጠር ልሳን ይልቅ የሚያንጸውን አምስቱ አዕማደ ምስጢራትን መማር ማስተማር ይጠቅማል ። በመሠረቱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መወሰን ባንችልም በአሁኑ ጊዜ ግን የልሳን መገለጽ ቤተክርስቲያንን በምን አይነት መልኩ እንደሚጠቅም ግልጽ አይደለም በርግጥ ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አስፈላጊነቱ ግልጽ ነው ምክንያቱም ወንጌልን በመላው ዓለም ያሰራጩ ዘንድ ሰዎችን ወደ ክርስትና እምነት ይመልሱ ዘንድ ነበር ። አሁን ግን ወንጌል በተለያዩ ቋንቋዎች እየተሰበከች ነው ። እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው የሚያስተምረው መምህር አለው ። ስለዚህ የቋንቋ ትልቅና ትንሽ ስለሌለ ሰዎች በሚሰሙት ቋንቋ ብቻ ሊማሩ ይገባቸዋል እንጂ ሊሰሙት የሚችሉትን ቋንቋ ትቶ ሊረዱት በማይችሉት ቋንቋ መለፍለፍ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው እብደት ነው ።

## በልሳን መጸለይ

የልሳን ጸሎት የሚባል ነገር በአንዳንድ እምነቶች ዘንድ አለ እነዚህ ሰዎች ትርጉሙ በማይታወቅ ቋንቋ ካለፈለፉ ሰውነታቸው እንደ ባለዛሮች ካልተርገፈገፈ ጸሎት ያልጸለዩ የሚመስላቸውና ይህ ጸጋ ያልተሰጣቸውም ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ እንደሆኑ ይናገራሉ ። እንግዲህ ነገሩን አርቀን ብናስተውለው የቋንቋ አምልኮት እንዳለበት እንረዳለን እግዚአብሔር በማናቸውም ቋንቋ ብናመሰግነው ብንለምነው ቁም ነገሩ የልብ ንጽህና እንጂ የቋንቋ መለ



ዋወጥ አይደለም ። በልሳን አልጸለያችሁምና ብሎ ልመናችንን የማይቀበል አምላክ አይደለም ። እንደውም በልሳን እንጸልያለን የሚሉት ሰዎች ለእነርሱ ይመስላቸዋል እንጂ ከትክክለኛው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የወጡ ናቸው ። ይህን ስል ግን በተለያየ ቋንቋ መጸለይ ተገቢ አይደለም ማለቴ አለመሆኑ ይታወቅልኝ ። ዋናው ዓላማዬ ከሥርዓት ወጥተው የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በሚያስነውሩ ሰዎች ላይ የሐዋርያው ቃሌን ለማስማት ነው ።

ቋንቋ የሰውን እምነት ትንሽና ትልቅነት የሚለካ አይደለም ። በልሳን መጸለይ አለብህ የሚለው አባባል «ሌላው ቀርቶ እንኳን በሰዎች ቋንቋ ቀርቶ በመላእክት ቋንቋ እንኳን መናገር ብችል ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ ነኝ» ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፩ የሚለውን አለማስተዋል ነው ።

## የመፈወስ ስጦታ

ፈውስ ማለት ከበሽታ መዳን ጤናን ማግኘት ነው (19) ህሙማንን መፈወስ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ያለ ነው ። ማርያምና ንዕማን ከለምጽ ተፈወሱ (ዘኁልቅ ፲፪ ፥ ፩—፲፭ ፪ኛ ነገሥ ፭ ፥ ፩—፲፬ ኤልያስ የስራፕታሴት ልጅ (፩ኛ ነገሥ ፲፯—፲፯—፳፬) ኤልሳዕም የሱነምን ሴት ልጅ ከሞት እንዳስነሱ ተዘግቧል (፪ኛ ነገሥ ፬ ፥ ፲፰—፴፯)

ክርስቶስ ብዙ ሰዎችን እንደ ፈወሰ በወንጌል ተጽፏል ። አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም ድውያንን እንዲፈወሱ ሥልጣንን ሰጥቷአቸዋል ። (ማቴ ፲ ፥ ፩)

በዘመናችንም በየጸበሉ ብዙ ፈውስ ይደረጋል ከ1947 ዓ. ም. እስከ 1983 ዓ. ም. መጨረሻ ድረስ በወንጪ አውራጃ ወሊሶ ግዮን ከተማ በብጹእ አቡነ ዲዮስቆሮስ (መምህር ወልደ ትንሣኤ ግዛው) እጅ ተጠምቀው በእግዚአብሔር ቸርነት 5,720,293 ሕሙማን ፈውስን አግኝተዋል ከእነዚህም ውስጥ 2,853 ሽባ የነበሩ 1,179 አንደበታቸው ተዘግቶ የነበረ 318 ዓይነ ስውር የነበሩ 11,496 እብደው የነበሩ 2,932 ጆሩአቸው ደንቁሮ የነበር 5,576 አፋቸው ተጣሞ የነበረ እንደዚሁም በሌላ ደዌ ተለክፈው የነበሩ ብዙዎች ፈውስን አግኝተዋል ። አሁንም ቢሆን በአማናዊት ቤተክርስቲያን የፈውስ ስጦታ አለ ።



www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን ሕሙማንን መፈወስ የእውነተኛ ሃይማኖት መግለጫ ሊሆን አይችልም ። ምክንያቱም የተሳሳተ እምነት ያላቸው ሰዎች ህሙማንን ሲፈውሱ ይታያልና ።

ተአምር ከእግዚአብሔር ብቻ የሚመጣ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜም ሰይጣን ሰዎችን ለማዘናጋትና ከእውነተኛው እምነት ለማውጣት ልዩ ልዩ ተአምራትን በወዳጆቹ ላይ አድሮ ይፈጽማልና «የሚተነኩሉ የክርስቶስን ሐዋርያት የሚመስሉ ዐመጽን የሚያደርጉ ዋሾዎች አሉና ። ይህም አያስደንቅም እሱ ራሱ ሰይጣን እንደ ብርሃን መልአክ ይመስላልና ። ይህም ታላቅ ነገር አይደለም የሰይጣን መልእክተኞቹም የጽድቅ መላእክትን ቢመስሉ ፍጻሜያቸው ግን እንደ ሥራቸው ነው» ፪ኛ ቆሮ. ፲፩ ፥ ፲፫—፲፭ ።

እንግዲህ የክርስትና እምነታችን የተመሠረተችው በተአምር ላይ አይደለም በወንጌል ላይ እንጂ ህገ ወንጌል ተስፋ ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲባል ግን በቤተክርስቲያን አማናዊ ተአምር አይደረግም ማለት አይደለም ግን መሠረት ሆኖ ሊመለክበት አይገባም ምናልባት ሰይጣናዊ ተአምርም ሊሆን ይችላልና ። ሰይጣንና ተከታዮቹም ተአምራትን ያደርጋሉ ዘጸአት ፯ ፥ ፲፩—፲፫ ። እና ፳፬ ማቴዎስ ፳፬ ፥ ፳፬ ፪ኛ ተሰሎ. ፪ ፥ ፱

በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስመሰግነው ታምር ማድረግ ሳይሆን ልብን ንጹህ አድርጎ በሃይማኖት መጽናት ነው በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚል ተጽፏል «እነዚህ አበው መልእክተኞችም ደስ ብሎአቸው ተመለሱና አቤቱ አጋንንትም እኮ በስምህ ተገዙልን አሉት ። እሱ እንዲህ አላቸው ...... አጋንንት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ ስማችሁ በሰማያት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ እንጂ» ሉቃ ፲ ፥ ፲፯—፳ ።

ዮሐንስ ተብሎ የሚጠራው ሐዋርያ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ «ነቢያትን የሚያሳብሉ ብዙዎች ወደ ዓለም ሞጥተዋልና» ፩ኛ ዮሐን መል. ፬ ፥ ፩ ። ብሎ ከሐስተኞች ነብያት እንድንጠበቅ አስቀድሞ አስጠንቅቆናል ።

ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ በተለያየ መልኩ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው እየተባለ የሚካሄደው ፈውስ ታአምር ሌላም ድንቅ የሚመስል



ነገር ሁሉ በአንክሮ ሊጤን ይገባዋል እንጂ ከእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር እንደዚህ ዓይነት እጹብ ድንቅ ሥራ ሊሠራ አይችልም በሚል የየዋህነት አስተሳሰብ የጸላየ ሰናይ ሰለባ እንዳንሆን ።

በክርስቶስ ስም አጋንንትን ማውጣት ታላላቅ ተአምራትን ማድረግ አያጸድቅም «በዚያች ቀን ብዙዎች አቤቱ አቤቱ በስምህ ትንቢት ተናገርን በስምህ አጋንንትን አወጥተን በስምህ ብዙ ተአምራትን አድርገን አልነበረምን ይሉኛል ያን ጊዜም ፈጽሞ አላውቃችሁም ዐመጽን የምታደርጉ ሁላችሁ ከእኔ ራቁ እላቸዋለሁ» ማቴ ፯ ፡ ፳፪—፳፫ ።

ከዚህ አባባል እንደምንረዳው ድንቅ ተአምራትን ማድረግ የዛን ሰው ትክክለኛነትና ብቃት የሚገልጽ እንዳልሆነ ነው።እኛን ለማዳን አካላዊ ቃል ንጽሕት ቅድስት ከምትሆን ከድንግል ማርያም መወለዱን ስለ እኛ ሲል መሰቀሉን መሞቱን ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱን ኋላም ለፍርድ መምጣቱን ከማመንና ከመመስከርም የበለጠ ተአምር የለም ።

ተአምር አልተደረገልንም"ና የያዝነው እምነት ስህተት ነው ማለት ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው ። ምክንያቱም እምነታችን ከመነሻው በተአምር ላይ ብቻ የተመሠረተች አይደለችምና ።

## ትንቢት የመናገር ተሰጥኦ

የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት የትንቢትን ትርጉም እንዲህ ሲል ይፈታዋል ።

ትንቢት— በቁሙ ራእይ ንግር ገና ወደ ፊት የሚመጣ ነገር አስቀድሞ የሚታይና የሚገለጥ ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ (20)

መጽሐፍ ቅዱስም ስለትንቢትና ነብያት እንዲህ ይላል «በብዙ አነጋገር በብዙ ክፍል እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ተናገረ በነቢያቱ ከጥንት ጀምሮ» ዕብ ፩ ፥ ፩

---

(20) ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 620



www.ethiopianorthodox.org

ነገሮች ሲተነበዩ መሠረታዊ ሁኔታቸው እንጂ በጋዜጣ እንደሚጻፉ ፣ ድርጊቶች አይደሉም ። ስለዚህ ትንቢት ከመፈጸሙ በፊት እንዴት እንደሚሆን አይታወቅም ከተፈጸመ በኋላ ግን ድርጊቱ የትንቢቱ ፍጻሜ መሆኑን የእግዚአበሔር ሰዎች ያስተውላሉ (21)

መጻያትን መናገር የተናጋሪዎችን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መሞላት ያሳያል ። የሚለው እምነትና አስተሳሰብ ሁል ጊዜ ትክክል ነው ብሎ መቀበል የዋህነት ነው ። አባባሌን በተረዳ ነገር ለመግለጽ የሚከተሉትን ሰዎች ታሪክ ላቅርብ ።

## ኖስትራዳመስ

ኖስትራዳመስ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በዲሴምበር 14,1503 ዓ. ም. የተወለደ የፈረንሳይ ይሁዳዊ ነው ። ወላጆቹ ቀድሞ የይሁዲ እምነት ተከታዮች ነበሩ ዳሩ ግን ኖስትራዳመስ የዘጠኝ ዓመት ልጅ እያለ ወደ ካቶሊክ እምነት ተቀየሩ ።

በ1522 ዓ. ም. ምንቶፔለር በተባለው ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የአራት ዓመት የህክምና ትምህርቱን ጨርሶ በባችለር ዲግሪ ተመርቋል ። ከተወሰኑ ዓመታት በኋላም ተመልሶ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በመግባት የዶክትሬት ዲግሪውን ተቀብሏል ። (22)

ኖስትራዳመስ ከዛሬ አራት መቶ ዓመት ቀደም ብሎ የነበረ ሰው ቢሆንም ዳሩ ግን እስከ 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዘልቆ በዓለማችን ላይ የሚፈጠሩትን ዓበይት ክስተቶች በትንቢት መስታወት ያሳየ አስትሮሎጀር ነው ። የኖስትራዳመስ ንግርቶች ከ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ያዝነው ምዕተዓመት ድረስ በትክክለኝነታቸው የብዙዎች ሊቃውንትን እማኝነት ያገኙ ሲሆኑ በመላው ዓለም ላይም ተናኝተው የብዙውን ሰው የልብ ትርታ ቀስቅሰዋል ። በተለይ በመካከለኛው ምሥራቅ ተለኩሶ የነበረው የአሜሪካ መራሹ ጦርና የኢራቅ ሁኔታ በኖስትራዳመስ ንግርት ውስጥ ከተጠቀሱት አንዱ ስለነበር የዘመናችን ኰሜንታተሮች የራሳቸውንም የወሬ ቅመም ጨማምረው በቪዲዮ ፊልሞች ቀርጸው ወሬውን በመላው ዓለም ነዝተውት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው ። (The Man Who saw tomorrow) የሚለው ፊልም በዋቢነት ይጠቀሳል ።

(21) የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገጽ 116
(22) The Prophecies of Nostradamus pp (5-7)



ኖስትራዳመስ እስከ ዓለም ፍጻሜ ያለውን የዓለም ጉዞ እንዴት ሊያይ ቻለ? የሚለው መጠይቅ መሠረታዊና አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን ። ኖስትራዳመስ ንግርቶችን ሊጽፍ የቻለው መለኮታዊው ኃይል ገልጾለት ሳይሆን ከእርሱ በፊት የነበሩትን ማለትም የአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኔዎፕ ላቶኒስት የአስማት ስልት ተጠቅሞ መሆኑን ራሱ ገልጾታል ። «ለሊት ላይ ነው ። ሁሉም ነገር ጸጥ ረጭ ያለበት ። ኖስትራዳመስ በጥናት ክፍሉ በሃይማኖት አባቶች የተከለከሉ ምሥጢራዊ የሆኑ (የተለያዩ የመናፍስት መጥሪያ መጻሕፍት ሊሆኑ ይችላሉ) ለብቻው ሆኖ ያነባል ። እነዚህ መጻሕፍት የኖስትራዳመስ ንግርቶች ምንጭ ናቸው ። ኖስትራዳመስ የጥንት አፖሎኒያን የሚጠቀሙበትን የመናፍስት መጥሪያ ዘዴ እሱም ተጠቅሞበታል ። ኖስትራዳመስ ሊደረግ የሚገባውን ሁሉ አድርጎ እንደ ጨረሰ ተመስጦ መጣበት አይቶትና ሰምቶት በማያውቀው ክስተት ታጠረ ፍርሐት ዙሪያውን ከበበው ቀስ በቀስ ከእንግዳው ክስተት ጋር ሲላመድ ፍርሐቱ እየለቀቀው መጣ ። ንግርቶቹን በወረቀት ላይ ማስፈር ጀመረ (23)

ከኖስትራዳመስ ትንቢያዎች አንዱ በ1789 ዓ. ም. የተፈጸመው የፈረንሳይ አብዮት ነበር ። ስለዚህ ወቅት ኖስትራዳመስ ተንብዮ እንደነበር በኮሜንታተሮቹ ተገልጿል ። እንዲሁም በ1804 ዓ. ም. እራሱን የፈረንሳይ ንጉስ ብሎ ስለሰየመው ናፖሊዮን ሲተነብይ «በዓለም ውስጥ አንድ ንጉሥ ይነግሣል በዘመኑም ሰላም አይኖርም የግዛት ዘመኑም አጭር ነው በዚህ ዘመን የጳጳሱ መርከብ ይጠፋል ። ...» (24)

በንግርቱ መሠረት በጄነራል ሚዮሊስ የተመራው የፈረንሳይ ጦር በ1809 ሮምን ተቆጣጠረ ። በዚያን ጊዜ የሮሙ ጳጳስም የናፖሊዮን እስረኛ ሆኖ በ1814 ዓ. ም. የናፖሊዮን ዘመነ ንግሥና ሲያከትም የጳጳሱም ነጻነት አብሮ ታወጀ ።

በንግርቱ ውስጥ የንጉሱ የንግሥና ዘመን አጭር እንደሆነ ተጠቁሞ ነበር ናፖሊዮንም የፈረንሳይ ንጉስ የሆነው ለአሥር ዓመት ብቻ ነበር ።

(23) The Prophecis of Nostradainus pp (20-21)
(24) The " " " (22)



www.ethiopianorthodox.org

ኖስትራዳመስ ስለ ሂትለር በተነበየው ላይ ስሙን ሳይቀር ጠቅሶ ነበር ። (25)

አሜሪካን በሂሮሺማንና ናጋሳኪ ላይ በ1945 ዓ. ም. የጣለችው አውቶሚክ ቦንብ አስቀድሞ በኖስትራዳመስ የትንቢት መስተዋት የታየ ነበር ። ይህንንም ሲተነብይ «በመርከቦች ወደብ አቅራቢያ ባሉት ሁለት ከተሞች ላይ አሰቃቂ የሆነ ሁኔታ ይፈጠራል ። እንደዚህ ዓይነት አሰቃቂ ድርጊት ከዚህ ቀደም ያልታየ ነው።ርሐብ፣ ፈጣን ተላላፊ በሽታ እንዲሁም የሕዝብ እልቂት ይሆናል ። ጩኸት ይበረከታል ሁሉን ወደሚችል አምላክ» (26)

ሁለቱ ከተሞች ማለትም ናጋሳኪና ሂሮሺማ በባህር የተከበቡ ከተሞች እንደሆኑ ይነገራል ። በሁለቱም ከተሞች ላይ ከዛን ጊዜ በፊት በመሬት ላይ ያልታየ እልቂትና በጨረር ምክንያት የሚዛመት በሽታ በከተሞቹ ውስጥ በሚኖሩት ሰዎች ላይ የደረሰ ነው ። ሁለት መቅሰፍቶች በሁለት ከተሞች ላይ ይወርዳል የተባለውም በሁለቱ ከተሞች ላይ አሜሪካን የጣለችው የአውቶሚክ ቦንብ ነው ።

ኖስትራዳመስ ያልዳበሰው ያልነካው ያልተነበየው የለም ስለ ጥገናዊ ለውጥ ፣ ስለ ባሕረ ሰላጤው ፍጥጫ ፣ ስለ አያቶላ ሆሚኒ ፣ ስለ ጆን. ኤፍ. ኬኔዲ መገደል ፣ ስለ ኮሚዩኒዝም ስለ ቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ባጭሩ ከ16ኛው ሙቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሚፈጸሙ ድርጊቶች በኖስትራዳመስ አስቀድመው ታይተዋል ።

☆ ☆ ☆

በፈረንሳይ አገር ካኦርሊንስ መሥፍን አሽከሮች አንዱ 1699 ዓ. ም. አንዲት ልጅ ወለደ ። ልጅቱ ስምንት ዓመት ሲሆናት በውሃ ውስጥ እያየች ትንቢት መናገር ጀመረች ይህ ነገር በአሽከሮችና በቤቱ ሠራተኞች ዘንድ ወሬው ስለተስፋፋ መሥፍኑ ልጅቱን 1707 ዓ. ም. ከእሱ ዘንድ እንድትቀርብ አድርጎ «ልጄ ሁሉ ነገር የሚታይሽ ከሆነ ታላቁ የፈረንሳይ ንጉሠ ነገሥት ሉዊስ 14ኛ ሲሞቱ ስነሥርዓቱ የሚፈጸመው እንዴት ነው? ከእሳቸው በኋላስ በዙፋናቸው ላይ የሚቀመጠው ማነው ? አላት ።

---

(25.) The Prophecies of Nostradamus P. 90
(26.)The prophecies of Nostradamus p. 81



ልጅቱ በብርጭቆ ተሞልቶ ከተሰጣት ውሃ ውስጥ እየተመለከተች እያንዳንዱን ሁኔታ እየዘረዘረች ትናገር ጀመር ሬሳው የት እንደሚተኛ አጃቢዎቹ ምን እንደሚለብሱ መልካቸው ሁሉ ምን እንደሚመስል ዘርዝራ ተናገረች ። ልዑሉ «ሌላስ የሚታይሽ ነገር የለም» አላት «የቡርጎኒ ልዑልና ልዕልት ይታዩኛል የቤሪ ልዑልም ይታዩኛል ግን በቀብሩ ቦታና ጊዜ የሉም» አለች ። ይኸው የልጅቷ ንግግርት በወረቀት ተጽፎ ለትዝብት ያህል ለትልቅ ሰዎች ተሰጠ ።

በ1638 ዓ. ም. የተወለዱት ግርማዊ ሉዊስ 14ኛ በ1715 ዓ. ም. ልጅቱ በተነባች በስምንት ዓመት ሲሞቱ የተናገረችው ሁሉ በትክክል ደረሰ በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ አይታዩኝም ያለቻቸው ልዑሎች ሁሉ ከንጉሡ በፊት ሞቱ *

የልጅቱ ትንቢያ ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጣት ወይስ የውሃ ጥንቆላ?

☆ ☆ ☆

በ1452 ዓ. ም. ተወልደው በ1516 ዓ. ም. የሞቱት ንጉሥ ፌርዲናንድ 5ኛ ጠንቋዮች የምትሞተው ማድሪጋል በሚባል ቦታ ነው ብለዋቸው ነበር ። እኝህ ንጉሥ የእስፓኝ ንግሥት ኮሎምቦስ አሜሪካን ሲፈልግ በገንዘብ የረዱት ንግሥት ባል ነበሩ ታዲያ እኝህ ንጉሥ ጠንቋዮች በነገሩአቸው ንግርት አምነው የሚስታቸውን የትውልድ ቦታ የሆነችውን ማድሪጋልን ጎብኝተው አያውቁም ። አንድ ጊዜ በጉዞ ላይ እንዳሉ ታመሙና ተከታዮቻቸው በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ አስተኙዋቸው ጥቂት ሻል ሲላቸው ንጉሡ «የዚች መንደር ስም ማን ይባላል?» ብለው ጠየቁ ሰዎቹም «ትንሿ ማድሪጋል ትባላለች» ብለው ነገሩዋቸው ንጉሡም ይህን ስም ሲሰሙ ደንግጠው በድንጋጤ ወዲያው ሞቱ (27)

እንግዲህ ጠንቋዮቹ ይህን ተናግረው ተፈጸመና በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተሞሉ ናቸው ሊባሉ ነው?

☆ ☆ ☆

የቷቤት ገዥ የነበሩት ደላይ ላማ በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ እንዳሉ እሥረኛ ሆነው እንዲቀመጡ ቻይናውያን ፈረዱባቸው ። ዳላይ

---

* 1ኛ አስደናቂ ታሪኮች ገጽ 18 — 19
(27) አምስተኛ አስደናቾ ታሪኮች ገጽ 10



www.ethiopianorthodox.org

ላማ በዚያው በቤተመንግሥታቸው ውስጥ በእሥረኝነት እንደተቀመጡ «መጋቢት 17 ቀን 1959 ዓ. ም. ከሰዐት በኋላ ከእሥር ቤት እንወጣለን» ብለው ትንቢት ተናገሩ የቻይና ቀይ ጦር በቤተ መንግሥቱ ዙርያ የባውዛ መብራት እንዲበራ አድርገው በታላቅ ጥንቃቄ ለሊትና ቀን ሲጠብቁ ልክ ላማው በተናገሩት ቀን በነፋስ ኃይል ከበድ አሸዋ ተነስቶ የአካባቢውን ሰማይ ስለ ሸፈነው ዳላይ ላማ ከታሠሩበት ቤተ መንግሥታቸው ከ80 ሰዎች ጋር ወጥተው ሔዱ (28)

ስለ ቲቤቱ ገዥ ምን መናገር የምንችለው ነገር አለ? ትንቢት ስለተናገሩና ትንቢቱ ስለሰመረላቸው ፍጹም ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኙ ሊባሉ ይችላሉ?

## ነቢያተ ሐሰት

መጺያትን ተናግረው በለስ የቀናቸው ቢኖሩም በአንጻሩ ደግሞ ቅሌታቸውን ተሸክመው የቀሩም በጣት የሚቆጠሩ አይደሉም ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እንደነዚህ ያሉት ነቢያት ነን ባዮች እንዲህ ይላል «አለምሁ አለምሁ (ህልም አየሁ ፣ ራእይ ታየን) እያሉ በስሜ ሐሰትን የሚናገሩትን የነቢያትን ነገር ሰምቻለሁ ትንቢትን በሐሰት በሚናገሩ የልባቸውንም ሽንገላ በሚናገሩ በነቢያት ልብ ይህ የሚሆነው እስከ መቼ ነው... እነሆ ከምላሳቸው ትንቢትን አውጥተው እርሱ ይላል በሚሉ ነብያት ላይ ነኝ ይላል እግዚአብሔር ሐሰትን በሚያልሙ በሚናገሩም በሐሰታቸውና በድፍረታቸው ሕዝቤን በሚያስቱ በነቢያት ላይ ነኝ ይላል ። እግዚአብሔር እኔም አልላክኋቸውም አላዘዝኋቸውም ለእነዚህም ሕዝብ በማናቸውም አይረቡአቸውም ይላል እግዚአብሔር» ኤር ፳፫ ፣ ፳፫—፴፩ ።

እስቲ ከእነዚህ የሐሰት ነቢያት መካከል አንዳንዶቹን ለአብነት እናውሳቸው ።

(28) እምስተኛ አስደናቂ ታሪኮች ገጽ 50



## ሞንታንየስ

በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፍርግያ የተወለደው ሞንታንየስ የሞንታኒዝም እምነት መስራች ነው ። ቤተሰቦቹ ምንም እንኳ አረማውያን ቢሆኑም እሱ ግን የክርስትናን እምነት ተቀብሎ ካህን እስከ መሆን ደርሶ ነበር ። የኋላ ኋላ ግን በምትሐታዊ ተመስጦ ወደቀ ራእይ አያለሁ ትንቢት እናገራለሁ አለ ከተከታዮቹ መካከልም ማክሲሚልና ፕርስኪል የተባሉትን ሴቶች መርጦ ተከታዮቹ አደረገ ። እነርሱም እንደ እርሱ ሀብተ ትንቢት ተሰጥቶናል የሚሉ ነበሩ ።

ለሞንታንየስ ትምህርት ማእከሉ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና በዚህ ዓለምም የሚመሠረተው የሺህ ዓመት መንግሥት ነበር ። የአሁኖቹ የይሖዋ ምሥክሮች «የአምላክ መንግሥት በምድር ላይ ይመሰረታል» የሚለውን እምነታቸውን የወሰዱት ከሞንታኒየስ ሳይሆን አይቀርም ።

ሞንታንየስ እልቀተ ዓለም መቃረቡን የክርስቶስ ዳግም ምጽዓትም በዚህ ቀን ይሆናል በማለት ተከታዮቹን ሥራ አስፈትቶ ሁሉም የአምላክን መምጣትና የሺ ዘመኑን የአምላክ አገዛዝ ተስፋ በማድረግ እጆቻቸውን አጣምረው ተቀምጠው እንደነበር ይነገራል ።

ሞንታኒስትስ በብዙ ነገር ከሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የራቁ ናቸው በህጋቸው ውስጥ ወሰን የሌለው ጾም—ትኅርምት ያዛሉ ። ከሁሉም ምግቦች ይከለከላሉ ከደረቅ ምግቦች በስተቀር ። ጋብቻም የተወገዘ ነው ። ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት የሠሩ ሰዎች እስከ ዕለተ ሞታቸው በንስሐ መቆየት አለባቸው ። እምነታቸው በትንቢት ላይ የተመሠረተ ነው ። (29)

## ዊሊያም ሚለር

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በፌብሯሪ 15,1782 ዓ. ም. ፒትስፊልድ በተባለችው መንደር የተወለደው ዊሊያም ሚለር የአድቬንቲስትን እምነት በዘመናዊ መልኩ ያደራጀ ሰው ነው ።

(29) Short History of the Christian Church P. 46,
The Oxford Dictionary of the Christian Church P. 919



www.ethiopianorthodox.org

ሚለር በአሜሪካን ዩናይትድ ስቴትስ ቁጥሩ እጅግ በርካታ ለሆነ ሕዝብ ከ1838 ዓ. ም. ጀምሮ «በ1843 እና 1844 ዓ. ም. መካከል የምንኖርባት ዓለም ፍጻሜ ይሆናል» በማለት ያስተምር ጀመረ ። ይህን ትንቢት እንዲተነብይ ያደፋፈረው ጉዳይ ምን ነበር? የሚል ጥያቄ ለሚያነሳ ሁሉ መልሱ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ፰ ቁጥር ፴፬ ላይ የተጠቀሰው የ2300 ቀን የመቅደሱ መንጻት ትንቢት ነው ።

በዚህ ላይ ተመሥርቶ ሚለር የዓለምን ፍጻሜ ተነባ ፤ የሚለርን ትርጉምና አመለካከት አጠር ባለ ሁኔታ ለግንዛቤ ይሆናችሁ ዘንድ ልግለጽላችሁ ።

በዘህ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሰው 2300 ቀናት በዓመት ሲወሰዱ 2300 ዓመታት ይሆናሉ ። 2300 ዓመት ሲፈጸም መቅደሱ ይነጻል ለሚለው መነሻ አድርጐ የወሰደው በዚሁ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ፱ ቍ. ፳፬ እና ፳፭ ያለው ቃል ነበር። «በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባኤ ተቆጥሮአል ። ስለዚህ እወቅ አስተውልም ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትዕዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሲህ ድረስ ሰባት ሱባኤና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል» ።

ሰባ ሱባዔ ወደ ቀን ሲለወጥ 490 ቀናት ይሆናል ። ይኸ ደግሞ አንዱ ቀን ወደ ዓመት ሲለወጥ 490 ዓመት ይሆናል ። 490 ዓመቱ በሚለር ትርጉም ከክርስቶስ ልደት በፊት የኢየሩሳሌም መጠገን ትዕዛዝ የወጣው 457 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው ። እስከ ክርስቶስ ልደት 457 ዓመት ይቆጠራል ። ከክርስቶስ መወለድ እስከ ክርስቶስ ሞት 33 ዓመት (34 ዓመት) አለ ። 453 ዓመት ላይ 390 ዓመት ስንደምር 490 ዓመት እናገኛለን ። እንግዲህ የሰባው ሳምንት (የ490 ዓመት) መጀመሪያ ያ ቀን በ457 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን ማብቂያው ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ34 ዓ. ም. ነው ። ከዚህ በመነሳት የ2300 ዓመቱን መጨረሻ ማግኘት አስቸጋሪ አይደለም ። ከላይ የተጠቀሰው 490 ዓመት ከ2300 ዓመት ላይ ስለተነሳ ቀሪው 1910 ዓመት ይሆናል ። ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ34 ዓ. ም. ጀምሮ 1840 ዓመት ስንቆጥር ዳንኤል በምዕራፍ ፰ በቁጥር ፲፬ ላይ የጠቀሰው 2300 ዓመታት በ1844 ዓ. ም. ላይ ይሆናል ። ሚለርም በዚህ ዓይነት የሂሳብ ስሌት በመጠቀም የክርስቶስን ምጽዓት ወስኖ የዓለም መጨረሻ በ1844 ዓ. ም. ይሆናል ብሎ ባለመጠራጠር ተነባ ዳሩ ግን ትንበያው ሳይዝለት ቀረ ።



«ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉ» ማቴ ፳፬ ፥ ፲፩ ያለውን ያላስተዋሉ እንደው እንደ ቦይ ውሃ በመሩዋቸው የሚሄዱ አያሌ ሰዎች የሚለርን ትንበያ በፍጹም ልባቸው አምነው በመቀበል የእምነቱ ተከታዮች ሆኑ ። ነገር ግን በጉጉት በፍርሀት ትጠበቅ የነበረችው ቀን ደረሰች ፤ ዓለም እንደብራና ተጠቅላ ልታልፍ ነው በማለት «በእልፍ አእላፋት ወትእልፊት መላእክት ታጅቦ ቀንደመለከት እያስነፋ ቢታላቅ ግርማ የሚመጣውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሁሉም በተስፋ ሲጠባበቁ» እሱ ግን በተባለው ቀን ሳይመጣ ቀረ ። ቀጣዩ ዓመትም ተጠበቀ ፤ አሁንም ሰማይና ምድር አላለፉም ። የጌታም የምጽአት ምልክት በሰማይ አልታይ አለ ። 1844 ዓ. ም. እንደዘበት አለፈች ። የሚለር ተከታዮች ወደህሊናቸው ተመልሰው በሚለር ላይ ማንጐራጐር ጀመሩ ። በዚህ የተነሳ ሌሎች (ዲኖምኔሽንስ) ተፈጠሩ ። (30)

## ቻርለስ ቴዚ ሩስል

የአሁንዋ የፒተስበርግ ክፍል በምትሆነው በፔንሲልቫንያ በፌብሯሪ 16, 1852 ዓ. ም. የተወለደው ሩስል ፤ የመጀመሪያው የዋችታዎር ሶሳይቲ (የይሖዋ ምሥክር) መስራችና ፕሬዝዳንት ነው ። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የሚሰጠው ትምህርት አንድ አይነት መሆንና አብዛኛዎቹም ከእውነት ያራቁ ናቸው በማለት የተነሣው ሩስል በአእምሮው ሚዛን እንደ ገለባ ቀለው ከተገኙት ትምህርቶች ውስጥ «ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ አስቀድሞ የታወቀና የተወሰነ ነው ሰው በኃይሉ ሊለውጠው የሚችል አንዳች ስንኳ ነገር የለም» የሚለውና «ዘላለማዊ ቅጣት አለ» የሚለው እምነት ነበር ።

ተቃውሞውን እሱን የመሰሉ ሰዎችን በማሰባሰብ ጀመረ ። «የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት» በሚል ሰበብ ብዙዎችን የእምነቱ ሰለባ አደረጋቸው ቀስ በቀስ ተከታዮቹ እየተበራከቱ መጡ እርሱም እምነቱን የሚያራምድባቸው መጻሕፍትን ጻፈ በ1881 ዓ. ም.

---

(30) Encyclopaedia Britannica, Volume 15, P. 497,
The Oxford Dictionary of the Christian Church P. 20
Universe in Conflict, ፑ ፻77



www.ethiopianorthodox.org

«ጽዮን ዋችታዎር ትራክት ሶሳይቲ» የሚለውን ድርጅት ከመሰሎቹ ጋር ሆኖ አቋቋመ ።

በ1879 ዓ. ም. ማርያ ፍራንሲስ የተባለችውን ሴት አገባ ። ጋብቻ ውን እግዚአብሔር ያልባረከው ስለነበር መጨረሻው አላማረም ትዳራቸው የሚያስቀና አልነበረም እንዳውም ንዝንዝና ጭቅጭቅ የሞላበት ነበር ለዚህም ሙንስኤ የሩስል እኩይ ምግባርና ባህርይ ነበር ። ባለቤቱ እንደምትለው «ሩስል ራሱን ወዳድ ተመጻዳቂ ከሁሉ በላይ ነኝ ባይ እንዲሁም ደግሞ ከሌሎች የእምነቱ ተከታዮች ከሆኑ ሴቶች ጋር የሚማገጥ ነው» (31) በዚህ ምክንያት የተነሣ በ1913 ዓ. ም. ከሚስቱ ጋር ተፋቷል ።

ከሩስል ቅሌቶች አንዱ «ታምረኛ ስንዴ» በማለት ከማንኛውም ተራ ስንዴ የተለየ አምስት እጅ እጥፍ ምርት የሚሰጥ ብሎ የእራሱን ገቢ ለማዳበር የተጠቀመው ዘዴ ነው ነገር ግን ታምረኛው ስንዴ እንደተባለው አምስት እጥፍ ምርት ሊሰጥ ቀርቶ ከተራው የስንዴ ዘር ያነሰ ምርት ነበር የተገኘበት ። (32)

የሩስል ቅሌት በዚህ ብቻ አያልቅም ። ሩስል ሀብተ ትንቢት አለኝ የሚልም ነበር ። ለዚሁም ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአትና ስለፍጻሜ ዓለም የተነባው ትንቢዖ ዓይነተኝ ምሥክር ነው «የክርስቶስ መምጫ ቀን በ1874 ዓ. ም. ሲሆን የዓለም ፍጻሜ ደግሞ በ1914 ይሆናል» (33) ብሎ ነበር ።

ዳሩ ግን ፍጻሜ ዓለም እሱ በወሰነው ቀን ሳይሆን ቀረ የክርስቶስ ምጽአት እንደዚሁ ሳይሆን ቀረ እዲያውም በ1916 የሩስል የራሱ ፍጻሜ ሆነና ሞተ ተከታዮቹ ግን ይኸን ቅሌታቸውን ተሸክሙው ዛሬም የማይሆን ምክንያት ሲደረድሩ ይሰማሉ ።

## የደቡብ ኮሪያውያን ፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ትንበያ

በሺዎች የሚቆጠሩ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሆኑ ደቡብ ኮሪያውያን ቤታቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በመተው በያዝነው

---

(31) Jehovah's Witnesses P. 13
(32) The Oxford Dictionary of the Christian Church P. 1189
Jehovah's Witnesses P. 12
(33) The Oxford Dictionary of the Christian Church P. 1189



ጥቅምት ወር ለሚጠበቁት ጌታ እየሱስ መምጣት እየተዘጋጁ መሆኑ ታውቋል ብሎ አንድ ወርሃዊ መጽሔት ከታማኙ የዜና ምንጮች ያገኘውን ዜና ለንባብ አብቅቶት ነበር ።

በዚህ ዜና ላይ እንደተዘገበው በብዙዎቹ የኮሪያ ነቢያት የተነገረውን ይህንን የክርስቶስ ዳግም መምጣትን ከሚጠባበቁት መካከል ወደ ሰማይ ለመምጠቅ ከብደታቸውእንዳ ያስቸግራቸው በማሰብ ብዙ እርጉዝ ሴቶች ማስወረዳቸው ተደርሶበታል ። በደቡብ ኮሪያ ምድር ከሚገኙት ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት መካከል በተመልካቾቹ ዘንድ ወደ ፷ሺ የሚገመቱ ተከታዮች አሏቸው የሚባሉትን እነርሱ ግን ፻ሺ አሉን የሚሉት እነዚህ የእምነት ተቋሞች ባራመዱት የክርስቶስ ምጽዓት ትንቢት የተነሳ ይመጣል ከተባለበት ቀን ማለትም እ. ኤ. አ. ከጥቅምት ፳፰ በኋላ ነገሩ ሳይፈጸም ቢቀር እንደ አንድ ጊዜው ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እንደታየው የጆንስታውን ተከታዮች ዓይነት ራስን የማጥፋት ከፍተኛ አደጋ ይደርሳል ብለው የኮሪያ ባለሥልጣናት የፈሩ ሲሆን ያገሪቱ ዋና ዓቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትም አስፈላጊውን ሕጋዊ ክስ ለመመስረት ምርመራ መጀመሩ ታውቋል ብሎ መጽሔቱ ዜናውን ቋጭቷል (34)

## ሕልም

በህልማችን የምናየው ነገር ሁሉ እውነተኛ ነው ብለን አምነን ልንቀበለው አይገባም ሕልም አንዳንድ ጊዜ ቅዠት ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ በእውን የሚፈጸመውን አስቀድሞ ያሳያል ። ፈላስፋው ጋሊኖስ ሕልምን አስመልክቶ ሲጽፍ «ሕልሞች እርስ በርሳቸው ከተቃላቀሉት ካራቱ ባሕርያት ከነፋስ ፣ ከመሬት ፣ ከውኃ ፣ ከእሳት ይወለዳሉ ።

<u>ደም</u> በሕዋሱ ውስጥ ሲጸና (ሲዘዋወር) ሰውዬው በሕልሙ ያማረ ቀያይ ነገርንና ደስ የሚያሰኘውን ዓይነት ያያል ደም ሲጐርፍ ሲፈስ እሳት ሲሞቅ አገሩ ዱሩ ገደሉ በእሳት ሲቃጠል መብራቶች ሲያንጸባርቁ መብራቶች ሲብለጨለጩ ይህንና ይህን የመሳሰሉትን

---

(34) ሩሕ መጽሄት ቅጽ 1 ቍጥር 6 መስከረም 1985 ዓ. ም. ገጽ 45



www.ethiopianorthodox.org

የደም ኅብር ዓይነቶች ሲያይ ያድራል ። (ደም እሳታዊ ጠባይና
ኅብር ነው)

ሳፍር በሕዋሳቶች ውስጥ በብርታት ሲንቀሳቀስ ሰውዬው ክንፍ
አውጥቶ እንደ ወፍ ሲበር ሲሮጥ ሲዞር ሲመላለስ መሬት ሲዞርበት
ይህንና ይህን የመ ሳሰለውን የነፋስ ዓይነት በማየት ሲባክን ያድራል ።
(ሳፍር ነፋሳዊ ጠባይ ነው)

በልቀም ሲጸና ወንዞችንና ባሕሮችን በረዶንና ዝናምን ሲያይ
ያድራል ከውኃ ውስጥ ገብቶ ሲዋኝ ሲራጭ ውኃ ሲጠጣ ነጫጭ ነገሮ
ችንና እነዚህን የመሳሰሉትን የውኃ ዓይነቶች ሲያይ ያድራል (በል
ቀም ማያዊ (የውሃ) ጠባይ ነው)

ሳውዳ ሲፀና ወይም ሲዘዋወር መቃብሮች ሲቆፈሩ ጓድጓዶች
ሲማሱ ሰወየው ሲያርስ ሲቆፍር ሰው ሞቶ ሰዎች ሲቀብሩት ሲያለ
ቅሱ ሲላቀሱ መሬት በጨለማ ተውጦ ጥቋቁር ዓይነቶችን እያየ በፍ
ርሃት በረዓድ ሲርበደበድ ሲንቀጠቀጥ ያድራል ። (ሳውዳ መሬታዊ
ጠባይ ወይም ኅብር ነው (አንጋረ ፈላስፉን ተመልከት)

ሰው በእነዚህ በአራት ጠባዮች መንቀሳቀስና መነዋወጽ ምክ
ንያት በሕልሙ ሲፈራ ሲደነግጥ ሲንቀጠቀጥ ያድራል የፍርሃት
ዓይነቶች ሦስት ናቸው እነሱም «ፍርሃት ፡ ድንጋጤ ፡ ረዓድ ይባላሉ ።
ሞኝ ሰው ሐሰተኛ ሕልምን በከንቱ ተስፋ ያደርጋል ሐሰተኛ ሕልም
ሰነፉን ሰው ያስደነግጠዋል ሕልምን የሚያምን ሰው ጥላን እንደ ሚጨ
ብጥና ነፋስን እንደሚከተል ነው ። ሕልም ከመሆን ወዳለመሆን
ይፋለሳል በየወገን በየወገኑም የየራሱን ያሳይሀል ። ከእሪያ በግ እንደ
ማይወለድ ሁሉ ከሐሰተኛ ሕልምም ቁም ነገር አይገኝም ።

እውነተኛ ሕልም በምን ይታውቃል? እውነተኛ ሕልም ከሆነ
ፈጥኖ ይደርሳል ከእግዚአብሔር ዘንድ ከታዘዘ አይቀርም ካልታዘዘ
ግን ቢሉ ቢጨነቁ አይደረግም ። ስለዚህ እውነተኛ መልዕክትን ሊያስ
ተላልፍ የፈለገ ሕልም ይደጋገማል መላልሶ ይታያል ለልብም ይረ
ደዋል ።

ሕልምን በሚመለከት የተፈጸመውን አንድ አስገራሚ ትረካ
ልተርክልዎት «ቦስተን ግሎብ» የተባለው የታወቀ ጋዜጣ በሚዘጋጅ



በት መሥሪያ ቤት ውስጥ ባይረን ሳም የሚባል የጋዜጣው ሪፖርተር
ሊነጋጋ ሲል የተረኛነት ተግባሩን ፈጸመና ቢሮው ውስጥ
በሚገኝ ማረፊያ ላይ ጋደም አለ ከእንቅልፉ ሲነቃ በድንጋጤ መንፈስ
ተሸብሯል ራሱን እየነቀነቀ በህልሙ ያየው መዓት ሁሉ በዕውን
ያልተፈጸመ በመሆኑ ፈጣሪን አመሰገነ ። ከእንቅልፉ ነቅቶ ቁጭ
እንዳለ እንኳን እነዚያ በህልሙ ያያቸው መሸሻ በማጣት ይጨነቁ የነ
በሩ ሰዎች የጣእር ድምጽ በጎሊናው ያስተጋባል ። የቋጥኞች ቅላጭ
በተራራዎች ጐንና ጐን በየእርሻው መሃል በየመንደሮቹ ውስጥና
በሰዎች ላይ ሲፈሱ ይታየዋል ። የሁሉም ምክንያት በአንዲት ደሴት
ላይ የተፈጠረ የእሳት ገሞራ ፍንዳታ ነበር ።

ጋዜጠኛው ባይረን ቢሮው ውስጥ ለብቻው ተቀምጦ ጭንቅላቱን
በእጆቹ ደግፎ በሀዘን ተመስጦ ከቆየ በኋላ ብዕሩን አንስቶ በህልሙ
ያየውን ሁኔታ በዝርዝር መጻፍ ጀመረ የጻፈው እንዲህ የሚል ነበር
«በጃቫ አቅራቢያ በምትገኘው ፓራላፔ እየተባለች የምትጠራ ደሴት
በድንገት በፈነዳ እሳተ ገሞራ ሳቢያ ደሴቲቱ ከምድረ ገጽ የጠፋች
ሲሆን ነዋሪዎቹም በእሳትና በባሕር መካከል ሆነው ሲቅበዘበዙ ቆይ
ተው በመጨረሻ እነርሱም ሆኑ መርከቦቻቸውና ጀልባዎቻቸው
ፈልቶ በሚንተከተከው ውኃ ውስጥ ሰምጠዋል» ጽሑፉን ሲጨርስ
«ብርቱ ጉዳይ» የሚሉ ቃላት ከግርጌው አስፈረበት ።

ጧት የተረኛነቱ ሰዓት ሲፈጸም ጋዜጠኛው ባይረን ወረቀቱን
ጠረጴዛው ላይ እንዳኖረው ዘንግቶ ወደ ቤቱ ይሄዳል የጋዜጣው ዋና
አዘጋጅ ለዕለቱ የሚሆኑ ወሬዎችን ከየሪፖርተሮች ጠረጴዛ ላይ ሲለ
ቃቅም ያንን የባይረንን ጉድ የሚያወራ ጽሁፍ ያገኘዋል ። ትልቅ ዜና
አገኘሁ በማለት በዕለቱ ጋዜጣ የመጀመሪያ ገጽ ላይ እንዲታተም ያደ
ርጋል ። ዜናው እጅግ ከፍተኛና ስሜትን የሳበ ከመሆኑ በላይ በሌሎች
ጋዜጦች ባለመስፈሩ «ቦስተን ግሎብን» ለማግኘት ሕዝቡ መራኮት
ይጀምራል ። ዕለቱ ነሐሴ 28,1883 ዓ. ም. ነበር ።

ይሁን እንጂ ዋል አደር ብሎ አንዳንድ ጋዜጦች ጥያቄ ማቅረብ
በመጀመራቸውና በይበልጥም በጃቫ ደሴት አቅራቢያ «ፓራላፔ»
የምትባል ደሴት በፍጹም አለመኖሯ በምሁራን በመገለጹ የቦስተን
ግሎብ ጋዜጣ አዘጋጅ ከያቅጣጫው በጥያቄ ተወጠረ አዘጋጁ ምላሽ
ለመስጠት በመቸገሩም ባይረንን አስጠርቶ ማብራሪያ ለመጠየቅ ይገ
ደዳል ። ሪፖርተሩም በፍርሃት እየተርበደበደ ወሬውን ያገኘው ከሕ



www.ethiopianorthodox.org

ልሙ እንጂ ከገሀዱ ዓለም አለመሆኑን ያስረዳል ። በዚህ የተነሣ ጋዜጠኛው ከሥራው ሲባረር የቦስተን ግሎብ ደግሞ ያንን የሕልም ወሬ ያሳንዳች ማረጋገጫ ተቻኩሎ በገጹቹ ላይ በማውጣቱ ሌሎቹን ጋዜጦችና ሕዝቡን በማሳሳቱ ከእትሞቹ በአንደኛው የመጀመሪያ ገጽ ላይ የይቅርታ ጥያቄ ያቀርባል ። የሚከበረውና የሚወደደው ጋዜጣ ዋሾ ተብሎ በተለይ በተቀናቃኞች ዘንድ መሳቂያና መዘባበቻ ሆነ ። ሺያጩም ክፉኛ አሽቆለቆለ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ በሕንድ ውቅያኖስ በምትገኝ ደሴት ላይ ከባድ የመሬት ነውጥ ስለመድረሱና ብዙ ግዙፍ መርከቦችም ስለመስጠማቸው የሚገልጥ አስደንጋጭ ዜና ደረሰ ። በጸጸት ራሱን ቀብሮ የተዋረደ ስሙን በማደስ ላይ ከነበረው ከቦስተን ግሎብ በስተቀር. ሁሉም ጋዜጦች ወሬውን እየተቀባበሉ ያራግቡት ጀመር ። በተከታታይ ከደረሱት ዜናዎችና ከአደጋው ሥፍራ በሕይወት ለማምለጥ ከቻሉ የዓይን ምሥክሮች ለመረዳት እንደተቻለው የነውጡ ምክንያት በሱዳን ሰርጥ ውስጥ በምትገኝ «ካራካቶአ» የምትባል ደሴት ላይ የደረሰ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ መሆኑና በጦሱም ካራካቶአ ከምድረ ገጽ መጥፋቷ ተረጋገጠ ፍንዳታው የደረሰበትና ደሴቲቱም የወደመችበት ዕለት ነሐሴ 28, 1883 ነበር ።ጋዜጠኛ ባይረን ሳም ተረኛ የነበረበት ሌሊት ህልሙንም ያየበት ንጋት ዋዜማ| መሆኑ ነው ።

ይህን ጊዜ ያደፈጠው «ቦስተን ግሎብ» አንሰራራ የባይረን ሳምን ፎቶና የአደጋውን ወሬ በመጀመሪያ ገጽ ላይ በማስፈር ጋዜጠኛው ከአደጋው ቦታ የግማሽ ዓለም ርቀት ባለው በቦስተን ከተማ ተቀምጦ የካርካቶአን ጥፋት ልክ በወቅቱ በህልሙ ማየቱን አስረዳ ባይረን ያሳሳተው ነገር ቢኖር የደሴቲቱን ስም ብቻ ነበር «ፓራላፔ» ማለቱ ።

ይሁንና ከብዙ ዓመታት በኋላ ይህም ስህተት አለመሆኑ ተረጋገጠ ። አንድ ቀን ከሆላንድ የታሪክ ማህበር የተላከ አሮጌ የዓለም ካርታ «ለቦስተን ግሎብ» ዋና አዘጋጅ ይደርሰዋል ። በካርታው ላይ ካራካቶአ የምትታወቀው ከሃምሳ ዓመት በፊት ትጠራበት በነበረው ስም ሆኖ ይታያል ። ስሙም «ፓራላፔ» ይባላል ።

የባይረን ሳም የህልም ትንቢት ፍጹምና የተሟላ ሆነ ። ሁኔታውም መላውን ዓለም አስገረመ» ብሎ በ1983 ዓ. ም. በልዩ እትም የታተመው ቡናችን መጽሔት ታሪኩን ይቋጫል ።



እንግዲህ እውነተኛ ሕልም ወደድንም ጠላንም ይፈጸማል መጽሐፍ ቅዱስም ይህን እውነታ ያስረዳል ናቡከደነፆር ያየው ሕልም በዳንኤል እንደተተረጎመ ፈርኦን ያየው ሕልም በዮሴፍ እንደተተረጎመ ኋላም ተፈጻሚነት እንዳገኘ በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረ ነው ። ነገር ግን የታየው ሕልም ሁሉ ቅዠትም ሊሆን ስለሚችል ረጋ ብሎ መመርመር ተገቢ ነው ።

ስለፈረንሣዊው አይሁድ ስለኖስትራዳሙስ በጠቀስኩት ላይ ኖስትራዳሙስ እስከ ፳፩ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተሻግሮ ብዙ ነገሮችን እንደተነበየ ገልጬ ነበር ። አብዛኛዎቹ የኖስትራዳሙስ ትንቢቶች ለብዙዎች ግልጽ አይደሉም ። ኮከብ ቆጣሪው ኖስትራደሙስ የተነበየው ትንቢት ግልጽ ሆኖልናል ያሉ የዘመናችን «መጽሐፍ ገላጮች» ሄዋትና ሉሪያ የተባሉት ሁለት አሜሪካውያን የኖስትራደሙስ ምሥጢር መፍትሔ ተገለጸልን ብለው አብስረዋል ። የምርመራ ውጤታቸውንም «ሶላር ኤድሽን» በሚል ጽፈው በፍራንሲስ ዲማንገ ጋዜጣ (16/10/92) ላይ አውጥተዋል ።

እነዚህ «መጻፍ ገላጮች» ሁለት ሺህ ከመምጣቱ በፊት ብዙ ተዓምር ይታያል ። ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ አስከፊ ፈተናና ብሩህ ተስፋ ይፈራረቃል ብለዋል ። ከእነዚህም ውስጥ ፤

በ1993 ካሊፎርኒያ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ይደርስባታል ። በቁሟም ትፈራርሳለች የተረፉት ሕዝቦችዋ በድንኳን ይኖራሉ የሆሊውድ ማዘጋጃ ቤቶች ይወድማሉ የሲኒማ ወዳጆችን በእጅጉ ያስከፉቸዋል ።

በ1993 የእንግሊዝ አልጋ ወራሽ ቻርልስ ይነግሳል ለሚበከለውና ለሚጠፋው ዓለም ከባቢ ልዩ ግብረ ኃይል ይቋቋማል እሱም ይመራዋል ። ከጥፋትም ያድናል የንጉሡ እድሜ ግን በጥቂት ዓመታት ተወስኗል ።

በ1994 ወቅቱ አእምሮ ከፍትና በሳል ለሆኑ ግድላት ይጀምራል የዘጋባቸውና ደናቁርትም ሲያልፍባቸው ቆመው ይመለከታሉ ኒልሰን ማንዴላ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ይሆናሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

በ1993 የሚጀምራት የኢኮኖሚ ቀውስ እስከ 1995 ጃፓንን አይለያትም ። በነዚሁ ዓመታት የዐረቦችና እስራኤላውያን ጠብ እየከረረ ይሄዳል ።

በ1995 የአሜሪካምድር በእሳት ትጠበሳለች ።

በ1996 ጎዋ ውስጥ በተሌስኮፕ ሲታዩና ሲያስደንቁ የኖሩት ጥቋቁር ጉድጓዶች ምሥጢር ይገለጣል ያኔ የሰው ልጅ የሰሎሞንን ጥበብ ይለብሳል ።

ከ1997 ዓ. ም. ጀምሮ የሰው ልጅ ከካንሰር በሽታ ተፈዋሽ ይሆናል ዘሙኑ ፈውስ ይመጣል ። የሥጋ መዳከም የአእምሮ መዛል በሰው ልጅ ጥበብ ይገታሉ ። ለእርጅና ፍጹም ተገዥነት ያበቃል» የማቱሳላ ዕድሜ ለብዙዎች ይደርሳል ።

በ1998 ለኒያ የሳይንስ ልብወለድ ወዳጆች ያልጠበቁት ይከሰትባቸዋል «መጣፍ ገላጮች» እንደሚሉት ከምድር ከተላከች መንኮራኩር ጋር በሚደርስ ግጭት «የሌላ ፍጥረታት መኖር ምልክቱ በቴሌቪዥን ዕውን ይሆናል ። (35)

እንግዲህ ይህንንም በአርምሞ መጠበቅ ነው ። ሊሆንም ይችላል ። ነገር ግን ሆኖ መገኘቱ የሰዎቹን በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የሚያስረዳ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተያየት

መጽሐፍ ቅዱስ ከላይ ስለተጠቀሱት ጉዳዮች ቀደም ብሎ ብዙ ተናግሯል አስቀድሞም አስጠንቅቋል ። ለምሳሌ ያህል እነዚህን ጥቅሶች እንመለከት ።

ዘሌዋውያን ፲፱ ፥ ፴፮ «አስማትም አታድርጉ ሞራ ገላጭም አትሁኑ» እንግዲህ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት አስማት አድራ

(35) ዕይታ ጋዜጣ ጥቅምት 9/1985



ጊዎችና ሞራ ገላጮች የተወገዙ ስለሆነ በእነርሱም የሚታመንና ነገራቸውን የሚያምን ሁሉ የተወገዘ ነው ።

ትን. ኤርሚያስ ፳፯ ፥ ፱ «እናንተ ግን ለባቢሎን ንጉሥ አትገዙም የሚሉአችሁን ነቢያቶቻችሁንና ምዋርተኞቻችሁን ሕልም አላሚዎቻችሁን እና ቃላተኞቻችሁን መተተኞቻችሁንም አትስሙ ከምድራችሁ እንዲያርቁአችሁ እኔም እንዳሳድዳችሁ እናንተም እንዳትጠፉ ሐሰተኛ ትንቢትን ይናገሩላችኋልና ።»

እግዚአብሔር እርሱ ከላካቸው ነቢያት ውጭ ሌሎች የሰይጣን መልእክተኞች የሆኑ የሐሰት ነቢያትንና ኮከብ ቆጣሪዎችን እንዳንከተል ያስጠነቅቀናል ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የሚመክረንና የሚያዘንን ትተን በምዋርተኛ በኮከብ ቆጣሪ ራእይ አየን እያሉ በሚያታልሉ ሰዎች ተመርተን ሕግና ሥርዓትን የምናፋልስ ቃለ እግዚአብሔርን የምንዘነጋ ከሆንን እንደም፡ጠፋ ያስታውቀናል ።

ትን—ኢሳይያስ ፰ ፥ ፲፱ «እነርሱም የሚጮኹትንና ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው የሚናገሩትን መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ጠይቁ ባሉአችሁ ጊዜ ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባወ ምን?»

ዛሬ መላ ዓለም እምነቱ በመጽሐፍ ገላጮች በመናፍስት ጠሪዎችና ጠንቋዮች ስለሆነ የሚያማክረው ሁሉ በእነርሱ ቃል እንዲመራ ነው ። ነገር ግን በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘ ሁሉ መመሪያው የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያሳስበን ስለሁሉም ነገር ሊጠይቅ የሚገባው የታመነበት አምላኩን ነው ። ስለወደፊት ሕይወቱም ሆነ ስለዓለም የወደፊት ሁኔታ ለማወቅ ሊጠይቅ የሚገባው መጽሐፍ ቅዱስን ነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈ የለም ሁሉም በየፈርጁ ተጽፎ ይገኛል ። ከተመሠረተበት ከወንጌል ወጥቶ በማንም ቅዠት ወይም ኮከብ ቆጣሪ ትንቢትና መመሪያ ሊመራ አይገባውም ቢመራም የመጽሐፍ ቅዱስ ጠላት የእግዚአብሔር ጸር ነው ። ለመሆኑ ያለንበት ዘሙን ምን እንደሆነና ለወደፊትስ ምን እንደሚመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ሳይገልጽ ቀርቱአል? በፍጹም ሁሉም ነገር አስቀድሞ በእግዚአብሔር ሰዎች ተነግሮ አልቁአል ። ሁሉም ነገር አስቀድሞ ታይቷል ። ሰይጣን ለወዳጆቹ ቅርብ ነውና በእግዚአብሔር ሰዎች የተነገረውን እርሱ አዲስ አድርጐ ቢያቀርብ አያስደንቅም ዓላማው ሰውን ለማሳሳት ነውና ። ነብዩ እግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ዘካርያስ እንዲህ ይላል «ተራፊም ከንቱነትን ተናግረዋልና ምዋርተኞችም ውሸትን አይተዋልና ሐላምንም የሚያዩ በሐሰት ተናግረዋል በከንቱም ያጽናናሉ እረኛም የላቸውምና እንደ በጎች ተቅበዝብዘዋል ተጨንቀውማል» ሕዝቅ ፲፥፪ እነሆ ዛሬ የሕዝቡ ሆኔታ እንደዚህ ነው ።

በወንጌል የትመሠረተ በጣት የሚቆጠር ነው ። አብዛኛው ሰው ግን ከወንጌል ይልቅ ምልክት የሚሻ ነው «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል» ማቴ. ፲፪ ፥ ፴፱ ። ብሎ ጌታችን እንደተናገረ ። ወንጌልን ከሚያስተምረው ምልክት የሚያሳየው ህልም አለምኩ የሚለው ራእይ ታየኝ እንዲህ ይሆናል የሚለውን ይሻል ነገር ግን ለክርስቲያን ከወንጌል የበለጠ መታመኛና ምልክት ባላስፈለገው ነበር ። ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት እንደሚመጡ የተመረጡትን እስከማሳት የሚደርሱ በምትሀት ተአምር የሚያደርጉ እንደሚሆኑ አስቀድሞ መንገሩን ሁሉም የዘነጋው ይመስላል ።

የሚሆነው ከመሆን አይቀርም ስለዚህ መጨነቁ መጠበቡ ምን ለማምጣት ነው ። ትንቢትን የሚሰሙኮ ይድናሉ አልተባለም ቃለ እግዚአብሔርን ሰምተው ተግባራዊ የሚያደርጉ እንጂ ። ደግሞስ ስለ ጌታ ምምጣት ስለ እልፈተ ዓለም ከፍጡር ወገን የሚያውቅ ይኖር ይሆን ጌታ ራሱ «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ከራሱ ከጌታ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ሌላ ፍጡር የሰማይ መላእክት ቢሆኑ አያውቁም» ማቴ. ፳፬ ፥ ፴፮ ተብሎ ተንግሮ ክርስቶስ በዚህ ቀን ሊመጣ ነው እያሉ ሐሰተኛ ነቢያቶች በተናገሩት ቃል ታምኖ የጌታን ቃል ረስቶ መጨነቅ መጠበብ ክርስቲያንነታችንን ያሳያል? «በውኑ የሰው ልጅ ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ከሰው ልጆች እምነት ያለው ሰው ያገኝ ይሆንን?» ሉቃ ፲፰፥፰ ። ብሎ የተናገረው ቃል አማናዊ መሆኑን ግልጽ እያደረገ ነው የዓለም ሕዝብ ለዚሁም ጥቅምት ፳፰ ፩ሺ ፱፻፺፫ ዓ. ም. እንደ ኢትዮጵያውያ አቆጣጠር ክርስቶስ ሊመጣ ነው ተብሎ በደቡብ ኮሪያ በሶቪየት ኅብረት በሎስአንጀለስ የታየው መሸበር አይነተኛ ምሥክር ነው ።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ትንቢት ማንም በራሱ አረዳድ ሊተረጉመው አልተፈቀደለትም ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስ እንዳስጠነቀቀው ግን በመጽሐፍ ያለ ትንቢት ሁሉ ትርጓሜው በላዩ እንደ ሌለ ይህን ብቻ አስቀድማችሁ ዕወቁ ። ትንቢት በሰው ፈቃድ በሰ



ውም ፍላጎት ከቶ አይሆንም ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ተናገሩ እንጂ ከእግዚአብሔር ተልከው ፪ኛ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፳—፳፩

እንደዚሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር ተልከው ሀብት ትንቢት ተሰጥቶአቸው አማናዊውን ትንቢት የተናገሩትን ነቢያት ለማስተባበል አንዳንድ ሐሳዊ መሲሆች ቅበግ ለምድ ለብሰው በሕዝብ ክርስቲያኑ መካከል በመኹለክለክ እገሌ ያለው ትንቢት በዚህ መልኩ ነው የሚፈጸመው እያሉ ነቢያትን ያሳብላሉ ይህንንም ቅዱስ ጴጥሮስ አስቀድሞ በተሰጠው ሀብት ትንቢት ተጠቅሞ ጽፎልናል «ግን በሕዝብ መካከል ሐሰተኞች ነቢያት አሉበት በመካከላችሁ በውስጣችሁ እንዳሉ ሐሰትን የሚያስተምሩ ለጉስቁልናም ክሕደትን የሚዘሩ በደመ የዋጃቸውን ፈጣሪያቸውን የሚክዱ ጥፋትንና ውደምሰስን በቶሎ የሚያመጡ» ፪ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፩ ።

ሌላው ቀርቶ የተናገሩት እንኳን በለስ ቀንቶአቸው ቢሆን በእነርሱ ልንመራ አይገባንም ክርስቲያን ምንግዜም መሪው ክርስቶስ ነው ። ክርስቶስም በወንጌል ነው የሚመራን ። ከወንጌል የወጣ እምነትና ትምህርት ምንጊዜም የተወገዘ ነው ። አለበለዚያ የሚናገሩት ከመሬት ጠብ አይልም በሚል ፈሊጥ የጠንቋዮች ካዳሚ የሐሰተኞች ነቢያት አጃቢ መሆን እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ነው የእግዚአብሔር ቃል ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ይላል «እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና ። ይህም ድንቅ አይደለም ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና እንግዲህ አገልጋዮች ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ አያስደንቁም» ፪ኛ፥ቆሮንቶስ ፲፩ ፥ ፲፪—፲፭ ።

## የመንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰል ምስጢር

ማቴዎስ ፫ ፥ ፲፩ «እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃችኋል»

እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ በእሳት ተመስሎ እናገኛለን ። ስለምን ?

ምክንያቱ (ምሥጢሩ) የሚከተለው ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

፩ኛ/ እሳት ምሉዕ ነው በየትም ቦታ ይገኛል ። የሌለበት ቦታ የለም ። መንፈስ ቅዱስም ምሉዕ ነው ። የማይገኝበት ስፍራ የለም ። እሳት በምልአት ሳለ ቡላድ (ክብሪት) ካልመቱ አይገለጽም ። መንፈስ ቅዱስም ቋንቋ ሲያናግር ፣ ምሥጢር ሲያስተረጉም ፣ ተአምር ሲያሰራ እንጂ አድሮ ሳለ አይታወቅምና ።

፪ኛ/ እሳት ከመነሻው ማለትም ክብሪት ጭረን ስንለኩስ በመጠን ነው ። አነስተኛ ኃይል ነው የሚኖረው ቀስ በቀስ ግን ገለባውን እንጨቱን እየጨማመርን ስናቀጣጥለው ግን ኃይሉ እየጨመረ እየሰፋ እየተስፋፋ ይሔዳል ። በዚህ መልኩ መንፈስ ቅዱስም መጀመሪያ በ፵ና በ፹ ቀን ከቤተክርስቲያን ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማሕጸን ዮርዳኖስ ስንወለድ በመጠን ይሰጠናል (ጸጋው ማለት ነው) ኋላ ግን በገድል በትሩፋት በመጠኑ የተሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እያደገ እየሰፋ በመጨረሻ ተራራ እስከ ማፍረስ ሙት እስከ ማስነሳት ይደረሳል ።

፫ኛ/ እሳት ጣዕምን መዓዛን ያመጣል ። ማለትም እሳት የነካው ምግብ ይጣፍጣል ። አብዛኞቹ የዕለት ምግቦች በእሳት የሚበስሉ የሚጣፍጡ ናቸው ። እንደዚሁም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ጣዕመ ጸጋን መዓዛ ጸጋን ያመጣል ። ሕይወታችን ሊጣፍጥ መንፈሳችን ሊረካ የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ሲጐበኝ ብቻ ነው ።

፬ኛ/ እሳት በአግባቡ ፣ በመጠኑ ቢሞቁት ሰውነትን ያፍታታል ሙቀትም ይሰጣል ። ባጠቃላይ ሕይወት ይሆናል እንዲሁም ለብዙ ጥቅም ይውላል ። ዳሩ ግን ያለ አግባብ ከመጠን አልፎ የሞቁት እንደሆነ በሰውነትም ሆነ በሌላ ንብረት ላይ ጉዳት ያስከትላል ። እንደዚህም ሁሉ መንፈስ ቅዱስም በአግባቡ በወንጌል በቅዱሳት መጻሕፍት ቅዱሳን አበው ባስተማሩት ላይ ተመስርተው ቢመረምሩት ሕይወትን ይሰጣል ጸጋን ያጐናጽፋል ። ነገር ግን ከተጻፈው ወጥተው በአጉል ፍልስፍና በትዕቢት ተወጥረው ልመርምርህ ቢሉት መቅሰፍትን ያመጣል ። በገሃነመ እሳትም ይቀጣልና ።

፭ኛ/ እሳት ገለባም ይሁን እንጨት እርጥብ ይሁን ደረቅ ያቀረቡለትን ሁሉ ሳይመርጥ ያቃጥላል ። መንፈስ ቅዱስም በንጹህ ልቡና ሆኖ ለሚለምነው ሁሉ ሕጻን አዋቂ ድሀ ሀብታም ሳይል የጸለዩትን ጸሎት ያቀረቡትን መሥዋዕት ይቀበላልና ።



፮ኛ/ እሳት ውኃ ፣ ገደል ካልከለከለው በስተቀር ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋል ። መንፈስ ቅዱስም ቸርነቱ ካልከለከለው በስተቀር ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋልና ።

፯ኛ/ እሳት ጥቅጥቅ ብሎ የነበረውን ዱር በልቶ ገላጣ ያደርገዋል ። መንፈስ ቅዱስም የተሰወረውን ምሥጢር ይገልጻልና ።

፰ኛ/ እሳት የበላው መሬት ለእህል ለተክል ተስማሚ ነው ጥሩ ምርት ይገኝበታል ። እንደዚሁም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰውነት ለገድል ለትሩፋት ይመቻልና ። ሰይፍ ስለቱን ፈርቶ ከሃይማኖት ከምግባር ፍንክች አይልም ። በጦም ፣ በጸሎት ፣ በስግደት ተወስኖ ይኖራል እንጂ ።

፱ኛ/ እሳት ከአንዱ የሻማ መብራት ላይ ሃምሳ ስድሳ ሻማ ቢያበሩለት ተከፍሎ አይኖርበትም (የሻማው መብራት አይጐድልም) (ከመጠኑም አይቀንስም ። መንፈስ ቅዱስም ተከፍሎ ወይም የጸጋ መጉደል (መቀነስ) ሳይኖርበት እስከ ምጽአት ድረስ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ተስፋውን ለሚጠባበቁ ሁሉ ሲሰጥ ይኖራል ።

፲ኛ/ ሸክላ ሠሪ ሥራዋን ሠርታ ስትጨርስ ነቅ (ስህተት) ያገኘችበት እንደሆነ እንደገና መልሳ ከስክሳ በውሀ ለውሳ በእሳት ታድሰዋለች ። እንደዚሁም ሁሉ ንጹህ ሆኖ የተፈጠረ ሰው በኃጢአት ከእግዚአብሔር ሕግ ቢወጣ በንስሀ ሳሙና ታጥቦ በመንፈስ ቅዱስ ታድሶ አዲስ ሰው ይሆናል ።

<u>በማቴዎስ ፫ ፣ ፲፮ ላይ መንፈስ ቅዱስ በርግብ</u>
<u>አምሳል የወረደበት ምክንያት ፤</u>

ጌታችን በዮሐንስ እጅ በተጠመቀበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ ክንፉን አሰይፎ በርግብ አምሳል ወርዶአል ። እዚህ ላይ በርግብ አምሳል መውረዱ ምሥጢሩ ምንድን ነው?

፩ኛ/ ርግብ በተፈጥሮዋ ቂም በቀልን የማትይዝ የዋህ ናት ኃዳጊት በቀል ናት ። መንፈስ ቅዱስም በባሕርይው ቂም በቀልን የማይዝ ንስሀ ከገቡ የቀድሞ ኃጢአትን የማይቆጥር (በቀልን የማይዝ) ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

፪ኛ/ ርግብ በኖህ ጊዜ የውኃውን መጉደል አይታ እንድትመጣ በላካት ጊዜ እንደ ቁራ በዛው ሳትቀር የተላከችበትን መልእክት ለላኪዋ ስታመጣ የወይራቅጠል በአፍዋ ይዛ መጥታ ነበር ።

ይህም የጥፋት ውኃ ጉድሎዋል ማለትዋ ነበር ። እንደዚሁም ሁሉ መንፈስ ቅዱስም የኃጢአት ባህር ጐደለ ከእንግዲህ ወዲህ በእግረ አጋንንት መጠቅጠቅ ቀረ ሲል መላው የአዳም ዘር በክርስ ቶስ ሞት ነጻ ሊወጣ መሆኑን (ተስፋ መስቀልን) ሊያ በስር በርግብ አምሳል ታየ ።

፫ኛ/ ርግብ ክንፍዋን ቢመቷት ዕንቁላሏን ቢሰብሩት ጐጆዋን ካላፈረሱባት በስተቀር ቦታዋን አትለቅም ። መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት ቢሠሩ ፈጽመው ካልካዱት በስተቀር ከሰው ሕይወት አይለይምና ።

## ማጠቃለያ ፤

— መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር የሚሠለስ የሚቀደስ የባሕ ርይ አምላክ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ እኔ ያለ በአካል ልዩ የሆነ ጰራቅሊጦስን ይሰድላችሁ ዘንድ እኔ አባቴን እለምነዋለሁ ብሎ በተናገረበት በወንጌል ለእኛ ገልጦልናል መንፈስ ቅዱስን አካላዊ ነው ብለን እናምናለን ። ዮሐንስ ወንጌል ፲፬ ፥ ፲፮ እና ፳፮

— ከአብ በሠረጸ በወልድ በተገለጠ በተመሰገነ ከአብ ከወልድ ጋር በሚሰገድለት በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ። የሠረጸውም ከአብ ብቻ ነው ዮሐንስ ወንጌል ፲፭ ፥ ፳፮

— የመንፈስ ቅዱስ አካሉ አንድ ሲሆን ጸጋው (ስጦታው) ግን ወሰን የለውም ። መንፈስ ቅዱስ ወረደ ፥ አደረ ፥ ተሰጠ ሲል ጸጋውን እንጂ አካሉን አይደለም ሐዋርያት ሥራ ፲ ፥ ፵፭

— መንፈስ ቅዱስን እንደ መቅዶንዮስ ፍጡር የሚል የተረገመ የተወገዘ ነው ። ኃጢአቱም አይሰረይለትም ። ማቴዎስ ፲፪ ፥ ፴፪



# ምዕራፍ ሁለት

## ቅዱሳን መላእክት

ቅዱስ ማለት በቁሙ የተቀደሰ ክቡር ምስጉን ልዩ ምርጥ ንጹህ ጽሩይ ማለት ነው (36) ቅዱሳን የሚለው ቃል ደግሞ የቅዱስ ዘር ሲሆን የእግዚአብሔር ገንዘብ የሆኑ ሁሉ የሚጠሩበት ስም ነው ።

መላእክት ስንል ደግሞ መልእክተኛ አገልጋይ ማለት ነው (37)

ከላይ ትርጉማቸውን የሰጠነውን ሁለቱን ቃላት ስናገ ጣጥም ቅዱሳን መላእክት የሚል ዓረፍተ ነገር እናገኛለን ። የተቀ ደሱ መልእክተኞች የተመሰገኑ መልእክተኞች ንጹህ ምርጥ መልእክ ተኞች ማለት ነው ። እንግዲህ ቅዱሳን መላእክት እንዳሉ ሁሉ እርኩ ሳን መላእክትም አሉ ። እነርሱም ቀድሞ ቅዱሳን ሆነው የተፈጠሩ ኋላ ግን በሥራቸው ውዱቃን የሆኑ ሠራዊተ አጋንንት ናቸው ።

የቅዱሳን መላእክት ከተማቸው ኢዮር ፥ ራማ ፥ ኤረር ፥ ተብሎ ይጠራል ። ከሰባቱ ሰማያት ውስጥ ናቸው ። ዲያብሎስና ሠራዊቱ ግን በእንጦርጦስ ገደል በባርባሮስ ጽልመት ተወርውረዋል ። ራዕይ ፲፪ ፥ ፱ ።

## የመላእክት ተፈጥሮ

በመላእክት ተፈጥሮ ላይ የተለያዩ ሐሳቦች በሊቃውንቱ ዘንድ ይሰነዘራሉ አንዳንዶቹ የመላእክት ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ ነው ። ለዚሁም ማስረጃ የብርሃነ ዓለም ጳውሎስ የዕብራውያን መልእክት ፩ ፥ ፯ ነው ብለው ያቀርባሉ በዚህ መልእክት ላይ «መላእክቱን ነፋ ሳት የሚላኩትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው» የሚለውን ዓረፍተ ነገር በ[illegible] ሰድ ነው ። ሌሎቹ ሊቃውንት ደግሞ ሲተረጉሙ ይኸ

(36) ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት
(37) የመ. ቅ መዝገበ ቃላት ገጽ 16



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሁለት

## ቅዱሳን መላእክት

ቅዱስ ማለት በቁሙ የተቀደሰ ክቡር ምስጉን ልዩ ምርጥ ንጹህ ጽሩይ ማለት ነው (36) ቅዱሳን የሚለው ቃል ደግሞ የቅዱስ ዘር ሲሆን የእግዚአብሔር ገንዘብ የሆኑ ሁሉ የሚጠሩበት ስም ነው ።

መላእክት ስንል ደግሞ መልእክተኛ አገልጋይ ማለት ነው (37)

ከላይ ትርጉማቸውን የሰጠነውን ሁለቱን ቃላት ስናገጣጥም ቅዱሳን መላእክት የሚል ዓረፍተ ነገር እናገኛለን ። የተቀደሱ መልእክተኞች የተመሰገኑ መልእክተኞች ንጹህ ምርጥ መልእክተኞች ማለት ነው ። እንግዲህ ቅዱሳን መላእክት እንዳሉ ሁሉ እርኩሳን መላእክትም አሉ ። እነርሱም ቀድሞ ቅዱሳን ሆነው የተፈጠሩ ኋላ ግን በሥራቸው ውዱቃን የሆኑ ሠራዊተ አጋንንት ናቸው ።

የቅዱሳን መላእክት ከተማቸው ኢዮር ፥ ራማ ፥ ኤረር ፥ ተብሎ ይጠራል ። ከሰባቱ ሰማያት ውስጥ ናቸው ። ዲያብሎስና ሠራዊቱ ግን በእንጦርጦስ ገደል በባርባሮስ ጽልመት ተወርውረዋል ። ራዕይ ፲፪ ፥ ፱ ።

## የመላእክት ተፈጥሮ

በመላእክት ተፈጥሮ ላይ የተለያዩ ሐሳቦች በሊቃውንቱ ዘንድ ይሰነዘራሉ አንዳንዶቹ የመላእክት ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ ነው ። ለዚሁም ማስረጃ የብርሃነ ዓለም ጳውሎስ የዕብራውያን መልእክት ፩ ፥ ፯ ነው ብለው ያቀርባሉ በዚህ መልእክት ላይ «መላእክቱን ነፋሳት የሚላኩትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው» የሚለውን ዓረፍተ ነገር በ[illegible] ሲድ ነው ። ሌሎቹ ሊቃውንት ደግሞ ሲተረጉሙ ይኸ

(36) ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት
(37) የመ. ቅ መዝገበ ቃላት ገጽ 16



www.ethiopianorthodox.org

የሚያመለክተው መላእክት በእሳት በነፋስ መመሰላቸውን እንጂ ተፈጥሮአቸው ከእሳት ከነፋስ መሆኑን አይደለም ይሉና በእሳት በነፋስ የተመሰሉበትን ሲተነትኑ ነፋስ ፈጣን ነው መላእክትም ፈጣኖች ናቸው ። ነፋስ ረቂቅ ነው መላእክትም ረቂቃን ናቸው ። እሳት ብሩህ ነው መላእክትም ብሩሃን አእምሮ ናቸው ። እሳት ነፋስ ፈጻምያን ፈቃድ ናቸው መላእክትም ፈጻምያን ፈቃድ ናቸውና ። ስለዚህ ነው በእሳት በነፋስ የመሰላቸው ይላሉ ። ታዲያ ከምን ተፈጠሩ ሲባሉ አክሲማሮስ የተባለ ሊቅ እንዳስረዳው የመላእክት ተፈጥሮ «እምኅበ አልቦ» ወይም ከአምላካዊ ብርሃን ነው ። «የመላእክት ተፈጥሮ ከአምላካዊ ብርሃን ነው ከነፋስ ከእሳትስ ተፈጥረው ቢሆኑ አንደኛ ሙቀተው በፈርሱ በበሰበሱ ነበር ።» በኋል ብለው ይናገራሉ ። (38)

## መላእክት ምን ቀን ተፈጠሩ

መላእክት በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ እንደተፈጠሩ ይነገራል ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጉልህ በዚህ ቀን ተፈጠሩ ብሎ ባይናገርም ዳሩ ግን በዕለተ እሑድ መፈጠራቸውን በአንዳንድ ቦታ ሳይጠቁም አላለፈም ።

ሳዊሮስ ዘእስሙናይን የተባለ የቤተክርስቲያን ሊቅ መላእክት የተፈጠሩ ለይኩን ብርሃን (ብርሃን ይሁን) ባለ ጊዜ ሥጋ የሌላቸው ረቂቃን አድርጎ እሑድ በመጀመሪያው ሰዓት ከብርሃን ነው የፈጠራቸው ብሏል ።

ቅዱስ ዳዊትም «መላእክት ሁሉ አመስግኑት ጸሐይና ጨረቃ ከዋክብት ብርሃን ሁሉ አመስግኑት እርሱ ብሎአልና ሁኑም እርሱም አዝዞአልና ተፈጠሩም » መዝ ፻፵፰ ፡ ፪—፭ ብሎ መላእክት በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ መፈጠራቸውን ገልጿአል ። ቀሌምንጦስም «በመጀመሪያው ቀን እሑድ ሰማይንና መላእክትን ሁሉ ፈጠርኩዋቸው ይህንም ለሙሴ አልነገርኩም» ይላል (39)

---

(38) የቅዱስ ጳውሎስ መጽ ንባቡ ከነትርጓሜው ገጽ 612, መርሐጽ ድቅ ባህለ ሐይማኖት ገጽ 35

(37) መርሐ ጽድቅ ባሕለ ሃይማኖት ገጽ 34



## የመላእክት ባህርይ

መላእክት በፍጥረታቸው ረቂቃን መናፍስት ስለሆኑ ሥጋና አጥንት የላቸውም አያገቡም አይጋቡም ፤ አይበሉም አይጠጡም ። ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስረዳው እውነት ነው ማቴ ፳፪ ፡ ፴። ሉቃ ፳፬ ፡ ፴፱ ።

መጽሐፍ ቅዱስን እንዳሻቸው የሚተረጉሙ አንዳንዶች ግን ዘፍ ፮ ፡ ፪ ያለውን በመጥቀስ መላእክት ያገባሉ ይጋባሉ እያሉ ያስተምራሉ ። በዚህ ቦታ «የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች አገቡ» ማለቱ መላእክት የሰውን ሴት ልጆች አገቡ በፍትወት ረከሱ ማለት አይደለም ።

በእርግጥም መላእክት በመጽ ኢዮብ ፩ ፡ ፮ ላይ እንደተጠቀሰው «የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ ። ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሚለው አነጋገር ሁል ጊዜ ለረቂቃን መላእክት ብቻ የሚነገር አይደለም ። በዘፍ ፮ ፡ ፪መላእክት (የእግዚአብሔር ልጆች) የተባሉት ረቂቃን መላእክት ሳይሆኑ ሰዎች ናቸው ። ሥጋና አጥንት ያላቸው ሰዎች እንጂ በቁሙ መላእክት አይደሉም ። በደብር ቅዱስ ከሴት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው ይኖሩ የነበሩ ደቂቃ ሴት ናቸው ። ስለምን (የእግዚአብሔር ልጆች) አላቸው ቢባል ስለ ሁለት ነገር ነው ።

፩ኛ/ ስለአለቅነታቸው

፪ኛ/ ስለንጽሕናቸውና ስለቅድስናቸው ነው ።

፩ኛ/ <u>ስለአለቅነታቸው</u> ፡— ለተባለው መልአክ የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አለቃ ማለት ነው መላእክት አለቆች ይሆናል ። መጽሐፍ ቅዱስም በዚህ መንፈስ ቃሉን ተጠቅሞበት እናገኛለን ።

ዮሐንስ ራዕይ ፪ ፡ ፩,፰,፲፪ ። ፫ ፡ ፩, ፯,፲፬ በእነዚህ ቦታዎች «ወደ ቤተክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ » ማለቱ ለነሚካኤል ፤ ለነገብርኤል ማለቱ ሳይሆን ለቤተክርስቲያናቱ አለቆች ማለቱ ነው ። የዚህ ደብር አለቃ እንደሚባለው ማለት



www.ethiopianorthodox.org

ነው ። ደቂቃ ሴትም መላእክት መባላቸው አለቆች ስለሆኑ ነው ።

## ፭ኛ/ ምክንያት ስለንጽሕናቸውና ስለ ቅድስናቸው ፤

ሰዎች ሰብአዊ ባህርይ ብቻ አይደለም ያላቸው ማንኛውም ሰው የእንስሳት ባህርይ፥ የመላእክት ባህርይ፥እንዲሁም ሰዋዊ ባህርይ ይታይበታል ። ግዜ ሳይወስን የሚበላ የሚጠጣ ። እንዲሁም ከሥርዓት ውጭ ሥርዓት እንደሌላቸው እንደ እንስሳት የሚኖር ከሆነ እንስሳዊ ጸባይ አይሎበታል ይባላል ። ከእህል ከውሃ ርቆ ንጽህ ጠብቆ በጾም በትኅርምት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲኖር መልአካዊ ጸባይ ተላብሷል ይባላል ። ጾም በመልአካዊ ሥርዓት ውስጥ መግባት ነው ። ግዜ ወስኖ መብላት መጠጣት በሕጉ በትእዛዙ መኖር ሰብአዊ ጸባይ ነው ። እንግዲህ በደብረ ቅዱስ ይኖሩ የነበሩ ደቂቀ ሴት ከሴት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው በጾም በጸሎት ገዳም ገድመው ከቃየል ልጆች ተለይተው ይኖሩ ስለነበር የእግዚአብሔር ልጆች (መላእክት) ተብለው ይጠሩ ነበር ። በአንጻሩ ደግሞ የቃየል ልጆች የራሳቸውን ስም ለማስጠራት ብቻ የሚጥሩ ሥጋዊ ጸባይ ያየለባቸው ስለነበር የሰው ልጆች ተባሉ ። እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉ ደቂቀ ሴት አንድ ቀን የቃየልን ልጆች አይተው በመልካቸው ማማር ተማርከው በፍትወት መነደፋቸውን በዝሙት መውደቃቸውን ሙሴ ሲጽፍ የእግዚአብሔር ልጆች ከሰው ልጆች ጋር በፍትወት ረከሱ ብሎ ጻፈ ። ሄኖክ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት ደቂቀ ሴት መሆናቸውን ገልጾ ጽፏል መጽ. ሄኖክ ፮ ፥ ፩—፫ (40)

ደግሞም ዛሬም ንጽሕናቸውን ቅዱስናቸውን የጠበቁ ካሉ እንደ ደቂቀ ሴት የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው እንደሚጠሩ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስገነዝበን ነው ። «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ» ፩ኛ የዮሐንስ መልእክት ፫ ፥ ፩ ።

---

(40) ኩኩሐ ሃይማኖት ገጽ 76-79



ከእግዚአብሔር በጥምቀት የተወለደ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ። ነገር ግን መላእክት ነን ማለት አይደለም ። ስለዚህ ሙሴ ጌታ ያለውን «መላእክት አያገቡም አይጋቡም» ብሎ የተናገረውን አስተባብሎ አገቡ ማለቱ አይደለም ። ፍትወት ሥጋ በለበሰው ላይ እንጂ በረቂቃን መላእክት ባህርይ የለም ።

# የመላእክት አገልግሎት

መላእክት እግዚአብሔርና ሰውን ያገለግላሉ ። እግዚአብሔርን ያለ እረፍት ያመሰግኑታል በመንበሩ ዙሪያ ሆነው ያለማቋረጥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች እያሉ ያመሰግናሉ ። ኢሳ ፮ ፥ ፩—፫ ራዕይ ፭ ፥ ፭—፲፬ የመላእክት ምግባቸው መጠጣቸው ስብሐተ እግዚአብሔር ነው ። እግዚአብሔርን ከማመስገናቸውም በተጨማሪ ወደ ላካቸው ሥፍራ በፍጥነት ይሔዳሉ ።

መላእክት ሰውን የሚያገለግሉት በተራዳኢነታቸው በአማላጅነታቸው ነው ። ከፈጣሪ አማልደው ምህረትን ያሰጣሉ ። ይኸም የመላእክት አገልግሎት በአንድ መንገድ ብቻ ሳይሆን በሁለት መንገድ ነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትን ይዘው እንደሚመጡ ሁሉ የሰዎችን ልጆች ልመናም ወደ እግዚአብሔር ይዘው ይወጣሉ ።

## ስለ ተራዳኢነታቸው

መዝ ፺/፺፩ ፥ ፲፩ «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቅህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል ።

ከእዚህ አባባል እንደምንረዳው መላእክት በእግዚአብሔር የታመነን ሰው ሁሉ በሚሄድበት መንገድ ሁሉ አብረው በመሄድ ችግር እንዳይገጥመው በስውር እንደሚጠብቁት ነው ።

ኦሪት ዘፍጥ ፵፰ ፥ ፲፮ «አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እርሱ እግዚአብሔር ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን



www.ethiopianorthodox.org

የመገበኝ እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነ ዚህን ብላቴኖች ይባርክ»

ያዕቆብ የተራዳውን መልአክ ስም ጠርቶ ምናሴንና ኤፍሬምን እንዲባርክ ጠይቋል ። ስለዚህ ዛሬ እኛስ ያዕቆብን አብነት አድር ገን ሊቀመልአክት ቅዱስ ሚካኤል እንዲሁም ቅዱስ ገብርኤልንና ሌሎችን መላእክት በወርቅ መስቀላችሁ ባርኩን እርዱን ብንል ከመ ጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሚያሰኝ ምኑ ነው?

— ትንቢተ ዳንኤል ፫ ፡ ፳፩—፳፫ ሦስቱን ሕጻናት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተራድቷአቸዋል ።

— ዳንኤል ፮ ፡ ፳፪ «አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ» ዛሬም መላእክት እንደተራበ አንበሳ አፉን ከፍቶ ሊውጠን የሚያጋሣውን ሰይጣንን ቅዱሣን መላእክት አፉን እንዲዘጉልን ብንጠራቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያሰኛል ?

— መዝሙር ፴፫(፴፬) ፡ ፯ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ፡ ያድናቸውማል»

ከዚህ እንደምንረዳው መላእክት በሚያከብራቸው በሚወዳቸው በአማላጅነታቸው በሚተማመን ሰው (ጉባኤ) መካከል በመገኘት ከማ ንኛቸውም መጥፎ ነገር ያድኑ አቸውማል ። ክብርን ለሚገባው ክብርን መስጠት እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል ። ስለሆነም የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ብቻ ሲሰፍርና ሲያድናቸው በማይፈሩት (በማያከብሩት ሰዎች ዘንድ ግን እንደ ማይገኝ ዳዊት ያስገነዝባል ።

— ኦሪት ዘጸ ፳፫ ፡ ፳ «በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ ። በፊቱ ተጠንቀቁ ቃሉንም አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢ አት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት»

ይቅር አይልምና አታስመርሩት ማለቱ መላእክት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ሥልጣን እንዳላቸው ማመልከቱ እንደሆነ ግልጽ ነው ።



ልናስመርራቸው አይገባም ። ብናሳዝናቸው ግን ይቅር አይሉንም ለዚ ህም አብነት የሚሆነን የካዘርያስ ታሪክ ነው

ዘካርያስ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን ቃል ባለመስማቱ በመ ጠራጠሩ ቅዱስ ገብርኤል ዲዳ እንዳደረገው በሉቃ ፩ ፡ ፳ ላይ የሰፈረ ነው ። አመጣጡ ለብስራት ነበር ዳሩ ግን ዘካርያስ ስላስቆጣው ነበር ያልመጣበትን ፍርድ የፈረደበት እንግዲህ መላእክት ከእግዚአብሔር መላክ ብቻ እንጂ ሌላ ማድረግ አይችሉም ከተባለ ቅዱስ ገብርኤል የተላከው ለብሥራት ነበር ታዲያ ያልተላከበትን ዲዳ ማድረግ ለምን ሲፈጽም እግዚአብሔር አልተቆጣውም?

ትንቢተ ዳንኤል ፲ ፡ ፲፫ «የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ እነሆም ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት»

በመላእክት ተራዳኢነት ማመን በሌላ አምላክ ማመን ማለት አይደለም ። ለዚህም ዳንኤል ራሱ ምሥክር ይሆናል የፋርስ መን ግሥት አለቃ (ሰይጣን) በተቋቋመው ጊዜ የታላቁን መልአክት የቅ ዱስ ሚካኤልን ረዳትነት ሽቷል ። ቅዱስ ሚካኤል ሊረዳው መመ ጣቱን ጠቅሷል እንግዲህ ዳንኤልን የመሰለ የእግዚአብሔር ሰው የመ ልአኩን እርዳታ ሲሻ እኛ ግን በራሳችን ጸሎት ብቻ ተጠብቀን እን ኖራለን ብንልና የመላእክትን ተራዳኢነት ብንንቅ ከእግዚአብሔር ጸጋ በአፉ (ውጭ) እንደሆንን ልንረዳው ይገባናል ። የትዕቢት መን ፈስ ያደረብን መሆኑንም መግለጻችን ነው ።

መላእክት ከጥንቱ የተፈጠሩት ሰውን ሊረዱ ሊራዱም ጭምር ነው ። ስለዚህ በመላእክት አማላጅነት መታመኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ። ዳንኤል በም ፲፪ ፡ ፩ «ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል» በማለት መላእክት በአማላጅነታቸው ለሚ ተማመኑ ለእግዚአብሔር ልጆች በተራዳኢነት እንደሚቆሙላቸው ገልጹአል ።

መላእክት ስለ ሰው ልጆች መጸለይ (ማማለድ) እንደሚችሉ ነብየ እግዚአብሔር ዘካርያስ ገልጾአል «......የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ አቤቱ የሠራዊቱ ጌታ ሆይ እነዚህን ሰባ ዓመት የተቆጣ ሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከመቼ



www.ethiopianorthodox.org

ነው? አለ... እግዚአብሔርም መልሶ ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ በመልካምና በሚያጽናና ቃል ተናገረው ። ስለዚህም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ እንዲህ አለኝ ስበክ እንዲህም በል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ።... ወደ ኢየሩሳሌም በምሕረት ተመልሻለሁ» ትን ዛካ ፩ ፥ ፲፪—፲፮ ።

እንግዲህ መልአኩ «ሰባ ዓመት ሙሉ የተቆጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው?» የሚለው ጥያቄ የአማላጅነት ጥያቄ ነው ። ማራቸው እንጂ ማለት ነው ይህም ጥያቄ የልመና ዓይነት መሆኑን ለማረጋገጥ ብንሻ የእግዚአብሔርን መልስ ማስተዋል ነው ። እግዚአብሔር የመልአኩን አማላጅነት ስለተቀበለ ወደ እስራኤል በምሕረት መመለሱን ለመ[ል]አኩ ነገረው ። መልአኩም አማላጅነቱ ተቀባይነት ስላገኘ ወደ ዘካርያስ አስተላለፈ ። እንግዲህ እግዚአብሔር መልአኩ ፩ኛ/ ስለ እስራኤል ሕዝብ ሊያማልድ ወደ ፈጣሪው በቀረበ ጊዜ «ምን አገባህ አንተን በሥራዬ ምን ጥልቅ አደረገህ» ብሎ የቁጣ መልስ አልሰጠውም ። ይልቁንስ የመልአኩን ባለሟልነት ይገልጽ ዘንድ በመልካምና በሚያቆላምጥ ቃል ተናገረው እንጂ ። ትሁቱ ጌታ ከኃጢአት በስተቀር የሚያስቆጣው ነገር ስለሌለ የመልአኩን ርህራሄና አማላጅነት እንደ ወደደለትና አስደሳች የሆነ መልስ እንደሰጠው ጤናማ አእምሮ ያለው ሁሉ የሚያስተውለው ነው ።

— <u>ሉቃ ወን. ፲፫ ፥ ፲—፱</u> «እንዲህ ብሎ መሰሰላቸው አንድ ሰው በታወቀች በወይኑ ቦታ ውስጥ በለስ ነበረችው ፍሬ ሊለቅም ወደ እስዋ ሔደ አላገኘም የወይኑን ጠባቂም የዛችን በለስ ፍሬ ሊለቅም ሲመላለስ እነሆ ሦስት ዓመት ነው አላገኘሁም እን ግዲህስ ምድራችንን እንዳታቦዝን ቁረጣት አለው እሱም መልሶ እንዲህ አለው ። አቤቱ የዘንድሮን እንኳ ተዋት ዙሪያዋን ቆፍሬ አፈር እስከአስታቅፋት ፍግ እስከ አፈስባት ድረስ ። ምናልባት ለከርሞ ታፈራ እንደሆነ ያለዚያ ግን እንቆርጣታለን»

<u>የምሳሌው ትርጉም</u> ፡— እንደሚከተለው ነው ፤

— አንድ ሰው የተባለው እግዚአብሔር (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው



— በበለስ የተመሰለችው አንድም ቤተ እስራኤል ነች እንዲሁም በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ናቸው ።

— የወይን ቦታ ሰራተኛ (ጠባቂ) መላእክት ናቸው ።

<u>ት ን ታ ኔ ፤</u>

፩ኛ/ እግዚአብሔር የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ (ሰው ሆኖ) ሕግ በሚጠብቁባት በኢየሩሳሌም ያሉትን አይሁድ ሊያድን እንዲሁም ሃይማኖት ምግባር ባገኝባቸው ብሎ መጣ ። ነገር ግን ከእስራኤል ዘንድ ሃይማኖት ምግባር አላገኘባቸውም መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤልን ምግባር ሃይማኖት ባገኝባቸው ብዬ ስመላለስ እነሆ ሦስት አመቴ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ዞሮ ያስተማረው ሦስት ዓመት ነው ይህንን ሲያመለክት ነው) ። ነገር ግን ሃይማኖት ምግባር አላገኘሁባቸውም ለሌላው ሕዝብ ምሳሌ ሆነው የእነሱን ምሳሌ ተከትሎ ከእውነተኛው የመዳን መንገድ እንዳይወጣ አጥፋቸው ብሎ ቅዱስ ገብርኤልን ያዘዋል ። መጋቤ ሐዲስ ቅ/ገብርኤልም ለጌታ መልሶ «ጌታ ሆይ ምናልባት ለሚመጣው ዘመን ሃይማኖት ቢይዙ ምግባር ቢሠሩ እረዳቸዋለሁ ወይም ተራድቼ ሥራ እስከሠሩቸው ድረስ ለዛሬው ታገሳቸው ። ነገር ግን የእኔን ተራዳኢነትንቀው ወደ ሃይማኖት ወደ ፍጹም ምግባር የማይገቡ ከሆነ ታጠፋቸዋለህ ማለቱ ትዕዛዝህ ተፈጻሚ ይሁን ።

፪ኛ/ «አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው እግዚአብሔር በሰው ፊት አያደላምና» ሮሜ ፪ ፥ ፲፩ እንደተባለው ሁሉ ምሳሌው በአይሁድ ብቻ ተመስሎ የሚያበቃ አይደለም መላው የአዳም ዘርን የሚያካትት ነው ። ከላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ለአንድ ወገን ብቻ አይደለምና አምላክነቱ ስለዚህ ምሳሌው ለእስራኤል ዘንፍስ ለክርስቲያኖች ሁሉ የተመሰለ ነው ።

ጌታችን በምድር ላይ በሚኖሩ የአዳም ዘሮች ኃጢአት አዝኖ ጠባቂ መላእክቶቻቸውን ጠርቶ «እነሆ ሃይማኖት ምግባር ስፈልግባቸው ይኸው ሦስት ዓመቴ ነው ። ሦስት ዓመት የሚለውን በሰዎች የእድሜ ደረጃ ይመስላል ። የሰው ልጅ አራት የዕድገት ወቅቶች እንዳሉት የታወቀ ነው ። የህጻንነት ፥ ጉርምስና ፥ ጉልምስና ፥ እርግና (እርጅና) እንግዲህ ሦስት ዓመት ሲል ሕጻኑን ትቶ ሌሎች ሦስት የእድገት



www.ethiopianorthodox.org

ደረጃዎችን ሲያመለክት ነው ። ሕጻንነት ንጽሐ ጠባይ የማያድፍበት የፍጹምነት ወቅት ስለሆነ «እውነት እላችኋለሁ፡ የእግዚአብሔርን መን ግሥት እንደሕጻን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባበትም አላቸው» ማርቆስ ፲ ፥ ፲፰ በቀሩት በሦስቱ የእድገት ደረጃዎች በየጊዜው ጌታ ወደ እኛ ሕይወት በመንፈስ ይመላለሳል ። በጉርምስናችን ወቅት ህይ ወታችንን ይጎበኘዋል የቅድስና ሕይወት ያጣል አዝኖ ይሔዳል ከእን ደገና ስሜታችን በረድ ባለበት ወቅት ደግሞ ዛሬስ ፍሬ አፍርተው ይሆን ብሎ ህይወታችንን ይጎበኘዋል ። ፍሬ ሃይማኖት የለም ከእንደ ገና በስተርጅና ዘመናችንም ይጎበኘናል ከርሞ ጥጃዎች አሁንም ሕይ ወታችን እንደ ጎሰቆለ ነው ። ጌታም ተቆጥቶ ጠባቂ መላእክትን «እነሆ ወደዚህ ሰው ህይወት ስመላለስ ሦስት ጊዜዬ ነው ።ነገር ግን እርሱ ከዛሬ ነገ ፍሬ ሃይማኖት ያፈራል ብዬ ስጠብቀው እየባሰበት ነው ስለዚህ እሱን አብነት አድርገው ሌሎችም ከሃይማኖት ከምግባር በአፉ እንዳይሆኑ አስወግዱት» ብሎ ያዛቸዋል ጠባቂ መላእክትም፥ «አቤቱ ጌታ ሆይ ይህቺን ያሁንዋን ብቻ ታገስ እኛ ተራድተን ምግባር እንዲሠራ እናደርገዋለን ዳሩ ግን ተራዳኢነታችንን ንቆ ምግባር የማይሠራ ከሆነ ታጠፋዋለህ» በማለት በአማላጅነታቸው አማላጅነታቸውን ተራዳኢነታቸውን ጥላ ከለላ አድርጎ ለሚኖር ሰው ያማልዱታል ከመቀስፍም ያድኑታል ። ታዲያ እንዲህ ሲባል አማላ ጆቻችን ያሰምሩናል እያልን ወደ ፍጹም ምግባር ከመግባት ወደ ኋላ እንድንል አይደለም ። አማላጆቻችንን አማልዱን ስንል ሃይማኖትና ምግባር ይዘን መሆን አለበት አለበለዚያ ራሳችንን በኃጢአት «ውስጥ ሆን ብለን ከተን አማልዱን እያልን ብንጮህ መቅሰፍት ይከተለናል እንጂ ምህረት አይወርድልንም» እግዚአብሔር የሚዘበትበት አምላክ አይደለምና ራስን ከኃጢአት ለማውጣት ሳይጥሩ ቅዱሳንን አማልዱን ማለት በእነርሱም ሆነ በእግዚአብሔርም ላይ ከማሾፍ የተለየ አይደ ለም ። ስለዚህ የቅዱሳን መላእክትን አማላጅነት ሳናውቅ ለምንሰራው ኃጢአት ሲረዳን አውቀን ስለ ኃጢአታችን አማልደው የሚያስምሩ መላእክት አሉን ብለን ኃጢአት መሥራት ሐኪም ዘመድ አለኝ ብሎ ሆድን በቢላዎ እንደመዘንጠል ይቆጠራል ።

ሉቃ ወን. ፩ ፥ ፲፱ «እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው መል አኩ ገብርኤል ነኝ»

አየኸውን! የእግዚአብሔር ባለሟል ቅዱስ ገብርኤል ስለባለ ሟልነቱ ሲናገር «በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ»



ሲል በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ማለቱ በቁሙ ለእግዚአብሔር የተወሰነ ፊትኖሮት እርሱም እንደ ንጉስ ወታደር በእግዚአብሔር ፊት ተገትሮ የሚቆም መሆኑን አይደለም ። ሊያሳውቅ የፈለገው የእግዚአብሔር ፊቱ ወደ ሁሉም ነው በአራቱም አቅጣጫ ነው ። ቅ/ገብርኤል ሊገልጽ የፈለገው አማላጅነቱን ነው «የእግዚአብሔር ባለሟል የምሆን እኔ ገብርኤል ነኝ» ማለቱ ነው ምንግዜም ከእግዚ አብሔር የማይለይ ለዳንኤል ራዕይን የገለጠ እሱ ነውና ። በእግዚ አብሔር ፊት መቆም ማማለድን (ባለሟልነትን) የሚገልጽ መሆኑን በመዝሙር ፻፭ (፻፮) ፥ ፳፫ ላይ የምናነበው ነው «የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ» ማለቱ ባያማልዳቸው ኖሮ በባለሟልነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ባይለምንላቸው ኖሮ ማለት እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም ። እንደዚሁም ቅ/ገብርኤል በእግ ዚአብሔር ፊት የምቆም ማለቱ አማላጅነቱን ባለሟልነቱን ሲገልጽ ነው ። እንዲሁም መላእክት የትም ቦታ መገኘታቸውን በዚሁ አባ ባል እንረዳለን የእግዚአብሔር ፊት የትም ቦታ ነው ካልን መላእክትም እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ ካልጠፋ እሱ ባለበት ቦታ እነርሱም የሚኖሩ ከሆነ የትም ቦታ ብንጠራቸው ይራዱናል ማለት ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ የመላእክትን ተራዳኢነት ሲገልጽ ሰውን ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉ ናቸው ብሏል ። ዕብ ፩ ፥ ፲፬ ዛሬ በዚህ ዓለም ሰው የጸለየውን ጸሎት ያቀረበውን መስዋዕት ለማሳረግ ይወጣሉ ይወርዳሉ ኋላ ግን ዋጋቸውን ተቀብለው አርፈው ይኖራሉ ። ዛሬ ግን እኛን በማማለድ ይራዳሉ ።

ቅዱሳን መላእክት በአማላጅነታቸው ለሚተማመኑ ለክርስቶ ሳውያን ጸሎታቸውን በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ እንደሚችሉና ፍጹም ምሕረት ሊያሰጡ እንደሚችሉ ዮሐንስ በራእይ ተመልክቶታል ። ዮሐንስ ራእይ ፰. ቊ. ፫—፭ ። ሌላ መልአክ ከወደ ምሥራቅ መጣ በታቦቱ (በመሠዊያው) ፊት ቆመ የወርቅ ጽና ይዟል (በቂስ አምሳል ነው ያየው ) በመንበሩ ላይ ባለ በታቦቱ ፊት ለቅዱሳን ጸሎት አምሳል መርገፍ የሚሆን ብዙ ዕጣን ያሳርግ ዘንድ አፍሰው ሰጡት ።

የዕጣኑ ጢስ ለቅዱሳን ጸሎት አምሳል ከመሆን ጋራ ወደ እግዚ አብሔር ያረገው በመልአኩ እጅ ነው ። ማዕጠንተ ወርቁን እንሥቶ የኃጥአን ጸሎት አምሳል (ምሳሌ) የሚሆን ኅራረ ዕጣኑን ወደ ምድር



www.ethiopianorthodox.org

ደፋው ወደ ምድር በደፋው ጊዜ ነጐድጓድ መብረቅ ደብልቅልቅ ሆነ አለ ። ኃጢአትን በሠሩ ሰዎች ላይ መቅሠፍት ታዘዘ ሲል ነው ።

አንድ መልአክ የተባለው መጋቤ ብሉይ ቅዱስ ሚካኤል ነው ። የወርቅ ጥና መያዙ ጸሎት የሚያሳርግበትን ሥልጣን ከእግዚአብሔር ማግኘቱን ሲገልጽ ነው ።

. በጎ መዓዛ ያለው ጸሎቱ ከቀደሙት ቅዱሳን ጸሎት ጋራ በሱ ቃል ወደ እግዚአብሔር ዐረገ ። የቀደሙት ቅዱሳን ጸሎትን የሚያሳርግበትን ሥልጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተቀበለ ሁሉ ኃጥአንን የሚያጠፋበትን ሥልጣን ገንዘብ አድርጓል ። ለጻድቃን እንደ ጸለየ በኃጥአን ጸለየባቸው ። በኃጥአን ላይ በጸለየባቸው ጊዜ መቅሠፍት ታዘዘባቸው በአማላጅነቱ ለሚተማመኑ ደግሞ በመጸለይ ምሕረትን አገኙ ።

እንዲሁም ሌላ መልአክ የሚለው መጋቢ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል ነው ጸሎት በሚያሳርግበት ቦታ ቆመ የምእመናንን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የሚያሳርግበት ሥልጣን ገንዘብ አድርጓል (ተቀብሏል)

ጌትነቱ በሚታወቅበት ጽኑዑ ፍርድ በሚፈረድበት በዓለም መላእክት በሱ ጸሎት ጸሎተ ቅዱሳን ደኅርትን (የኋለኞቹ ቅዱሳን ጸሎት) በጎ መዓዛ ያለው ዕጣን አድርጎ ያሳርግ ዘንድ አሳርግ አሉት በጸሎቱ በአማላጅነቱ የሚተማመኑ ምእመናን የእርሱ ጸሎት ከጸሎተ ቅዱሳን ደኅርት ጋራ በጎ መዓዛ ያለው ዕጣን ሆኖ በርሱ ቃል ወደ እግዚአብሔር ዐረገ ። የምእመናንን ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር የማሳረግ ሥልጣን እንደተሰጠው ሁሉ ለእግዚአብሔር ወንጌል ለማይታዘዙ ዓመጸኞች ላይም ጸልዮባቸው መቅሠፍት እንደሚያመጣባቸው ሲገልጽ በኃጥአን ጸሎት አምሳል የተመሰለውን ኅራሪ ዕጣኑን ወደ ምድር ደፋው ። ያን ጊዜ መነዋወጥ ሆነ ይላል ።

እንግዲህ ክርስቲያኖች ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን መላእክት የእኛን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ የምትለው ከላይ የጠቀስናቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ይዛ እንጂ ከምንም ትንሥታ አለመሆኑን የተገነዘባችሁ ይመስለኛል ።



## መላእክት ሲሰገድላቸውና ሲከበሩ ይገባቸዋል

ስግደትም ሆነ ክብር በሁለት ወገን ይከፈላል ። ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳን ሰዎችና መላእክት ። እግዚአብሔር ብቸኛ ገናና አምላክ ስለሆነ ለእሱ የሚቀርበው ምሥጋና ፥ ክብር ፥ ስግደት ለማንኛውም ፍጡር አይቀርብም በሌላ አንጻር ደግሞ እግዘአብሔር የቀደሳቸውና ያከበራቸውን ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ በተሰጣቸው ክብር ልና ከብራቸው የፀጋ ስግደት ልንሰግድላቸው መንፈሳዊ ግዴታ አለብን ። «ያዘጋጃቸውን እነሱን ጠራ የጠራቸውን እነሱን አጸደቀ የአጸደቃቸውን እነሱን አከበረ» ሮሜ ፰ ፥ ፴ እንግዲህ እግዚአብሔር ያከበረረውን ማክበር እንጂ ማዋረድ ለእግዚአብሔር ተገዢ መሆንን አያሳይም «ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ» እንደተባለው እሱ ያከበራቸውን አናከብርም የሚል ካለ ጌታን የናቀ መሆኑን ሊገነዘበው ይገባል ።

የዮሐንስ ራዕይ ፲፱ ፥ ፲ እንዴት ይተረጐማል? አንዳንዶቹ ለመላእክት መስገድ አግባብ አይደለም የሚሉት ይህን ጥቅስ በመጥቀስ ነው ።

በመሠረቱ ይህ ጥቅስ ለመላእክት መስገድ እንዳለብን የሚያስገነዝብ እንጂ አትስገዱ የሚል ሆኖ አናገኘውም የተቃዋሚዎቹ አባባል ስንመረምረው ብዙ ስህተትና ግድፈት እንዳለበት እናምናለን ።

በቅድሚያ ዮሐንስ ለመልአኩ ሳይገባው በስህተት ስግደት አቀረበለት የሚለው አባባላቸው ምን ያህል ከእውነት የራቀና ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር የሚጋጭ መሆኑን እንረዳለን ።

ዮሐንስ ተሳሳተ ይሉ ዘንድ የዮሐንስን ማንነት መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስረዳው ሁኔታ የተረዱትና የተገነዘቡት አይመስልም ። የዮሐንስን ማንነት ማወቅ ለፈጸመው ድርጊት ትክክለኛነት ወይም ስህተትነት ሊገልጽልን ይችላል ።

ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ታዖሎጎስ በሚል ቅጽል የሚጠራ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው ዘላለማዊ ገዢ ገባሬ ኩሉ ምሉውስተኩሉ የሆነው አምላክ ህልወና ተገልጾለት የጸፈ ጌታ የሚወደው ንጹህ ቅዱስ ድንግል ። በቅድስናው በንጽሕናው በድንግልናው እመቤታችን በአደራ የተሰጣቸው ዮሐ ወን/ ፲፱ ፥ ፳፮ እስከ እግረ መስቀል ድረስ ከጌታ ያልተለየ «እስክመጣ ድረስ ይኑር» ዮሐን ወን/ ፳፩ ፥ ፳፪ የተባለለት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ አካል ከሀልውና ተገልጾለት እንኳን ምድራዊው ቀርቶ ሰማያዊው እውቀት ተገልጾ



www.ethiopianorthodox.org

ለት የእግዚአብሔርን አንድነት ሦስትነት የሥጋዌን ምሥጢር አበጥሮ አንጠርጥሮ ያሠፈረ ታላቅ ሐዋርያም ነቢይም ድንግልም ነው ። ይህን ቅዱስ ሰው ስለትንሹ ነገር ለመልአክት መስገድ አግባብ አለመሆኑ ተዘንግቶት ወይም አጥቶት ተሳስቶ ሰግዶ ወቀሳና ማስጠንቀቂያ ተሰጠው ብሎ መናገርና ማስተማር ወደር በማይገኝለት የስህተት ማጥ ውስጥ መግባት ነው ። ምንም እንኳን ሰው እንከን የማይወጣለት ፍጹም በኩለሔ ባይሆንም ነገር ግን ዮሐንስን በዚህ ማማት መንፈስ ቅዱስን መፅረፍ ነው ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ሰው «ወደ እውነት ተመርቶ ሌሎችንም ይመራል እንጂ ወደ ስህተት አይመራም ምክንያቱም የተቃኘው ወደ እውነት በሚመራው በእውነት መንፈስ ነውና ዮሐ ወን/ ፲፮ ፥ ፲፪—፲፭ ።

ስለዚህ በጌታችን የእውነት መንፈስ ተብሎ የተመሠከረለት መንፈስ ቅዱስ ዮሐንስን ወደ ስህተት መራው ቢባል በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል መናገር አይሆንም? «መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ደግሞ ኃጢአቱ አይሠረይለትም ። ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ለመሞላቱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረው ነው ሐዋ ሥራ ፪ ፥ ፩ ።

በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ሰው የሚያመልከው ማንን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል ሌሎችንም ያስተምራል ለማን መስገድ እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል ። ሌሎችንም ያስተምራል እንጂ ስግደት ለማይገባው ሁሉ ሲንበረከክ አይታይም ። እንኳን ይህን የእግዚአብሔርን ነገር ስንኳ ሳይቀር ያውቃል ፩ኛ ቆሮ ፪ ፥ ፲—፲፪ ።

መንፈስ ቅዱስ የጥበብ ፥ የማስተዋል የምክርና የኃይል የእውቀት መንፈስ መሆኑ በኢሳይያስ ፲፩ ፥ ፲፪ ። ላይ የተገለጸ ነው ። እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ ላይ አድሮበታል ከተባለ ለመልአክ መስገድ አግባብ አለመሆኑን እንዴት ሳያስተውለው ፥ ሳያውቅ ቀረ ? ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ዮሐንስ ለመልአኩ መስገዱ አግባብ ያለው አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ ተገንዝቦ ለእኛ አብነት ሊሆነን እንደሆነ ነው ።

በዚያች ቅጽበት መንፈስ ቅዱስ ተለይቶት ነበር የሚሉ ከሆነ ማስረጃ መጥቀስ አለባቸው ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከሐዋርያት የተለየበት ወቅት በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጠቀሰም በጸርሐ ጽዮን በእሳት አምሳል ፀጋው ከታደላቸው በኋላ ጌታ በተናገረው መሠረት «እርፍ ይዞ ወደኋላ የሚያርስ ገበሬ የለም» የሚለውን አባባል ይዘው እስከ ሞት የታመኑ መሆናቸው ነው የተዘገበው ጌታም «እስከ ዓለም



ፍጻሜ ከናንተ ጋር ነኝ» ማቴ ፳፰ ፥ ፲፱ ብሎ ተናገረ እንጂ እለያችኋለሁ አላለም ።

ምነውሳ ዮሐንስ መጥምቅ በወህኒ ሆኖ ስለ ክርስቶስ መጠየቁ መንፈስ ቅዱስ እንደተለየው የሚያረጋግጥ አይደለም ቢሉ አይደለም ዮሐንስ መጥምቅ ደቀመዛሙርቱን ወደ ጌታ ዘንድ መላኩ እሱ ስለጌታ ማንነት ተጠራጥሮ ሳይሆን የላካቸው ሰዎች ተጠራጥረው ነበርና አይተው አምላክነቱን ይረዱት ብሎ ነው እንጂ ። እርሱስ ያጠመቀውን የመሰከረለትን ሊያጣው እንዴት ይችላል? ማቴ ፲፩ ፥ ፪ ።

እንግዲህ ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ዮሐንስ ለመልአኩ የሰገደው አግባብ መሆኑን ተረድቶ ነው ። ከተባለ መልአኩስ አትስገድልኝ ማለቱ ስለምንድን ነው?

መልስ ፡— ስለ ሦስት ነገር አትስገድልኝ ብሎታል ።

1ኛ/ <u>ስለ ትህትና</u> ፡—

ሚካኤል ቢሉ ስሙ እንደሚጠቁመው ሚ ፡ መኑ ፡ ካ ፡ ከመ ፡ ኤል አምላክ በተገናኘ መኑ ከመ አምላክ ማለት ነው በአማርኛ እንደ አምላክ ያለ ማነው ማለት ነው (41) ስለዚህ ሚካኤል መባሉ በትህትናው አምላኩን በመምሰሉ ስለሆነ ለትህትና ብሎ አትስገድልኝ ብሎታል ። ሰዎች እርስ በርሳቸው ትህትና ሲለዋወጡ አይገባም አይገባም እንዲባባሉ ሁሉ መልአኩም አይገባኝም ማለቱ ነው ለትህትና ባይሆን ኖሮ በምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ አስጠንቅቆት ሳለ ምዕራፍ ሃያ ሁለት ላይ በድጋሚ ሲሰግድ ሕገ እግዚአብሔርን በመጣሱ በሰይፍ በቀላው ነበር ። ነገር ግን አግባብ አይደለም ማለቱ ስላልሆነ በድጋሚ ሲሰግድለትም አሁንም የትህትናን ነገር ነው የተናገረው ቅዱሳን ምንግዜም ቢሆን እንደሰይጣን አክብሩን አይሉምና ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሚገባ ያምናሉ እግዚአብሔር ግን እንዲከበሩ ያደርጋቸዋል ።

2ኛ/ <u>ስለ ዮሐንስ ክብር ሲል ነው</u> ፡—

ዮሐንስ በክብር ከመልአኩ እኩል ሆኖ ስለነበር ይህንን ክብሩን ሊገልጽለት ስለፈለገ መልአኩ አንተኮ ከእኔ ጋር በክብር እኩል

---

(41) አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 589



www.ethiopianorthodox.org

ነህ ታዲያ እንዴት ትሰግድልኛለህ እባክህ ተገቢዬ አይደለም ሁለታችንም ለእግዚአብሔር እንስገድ ሲል ነው ስግደት የበላይና የበታችነትን የሚያመለክት ስለሆነ ።

## 3ኛ/ ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር ሲል ነው

ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ «ካህናት ሰውን ሁሉ እንደሚዳኙ አታውቁምን እናንተ ሰውን ሁሉ የምትዳኙ ከሆናችሁ ይህን የትንሹን ነገር ልትፈርዱ አይገባችሁምን ። የዚህንስ ዓለም ዳኝነት ተውትና መላእክትን ስንኳ እንድንገዛ አታውቁምን» ፩ኛ ቆሮ ፮ ፥ ፪—፫ ።
በማለት የካህናት ሥልጣን ምን ያህል የከበረና የገነነ መሆኑን ገልጾአል ይህን በማስመልከት አንድ ታሪክ ይተረካል ስለ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው ።

በ344 ዓ.ም. በአንጾኪያ ከተማ አትናስዮና ሲፋንዶስ ከተባሉት ባልና ሚስት የተወለደው ዮሐንስ አፈወርቅ የመጀመሪያ ሥራው ጥብቅና ነበረ የኋላ ኋላ ግን ይህ ሥራ ስላላረካው ማናቸውንም ነገር ትቶ ክርስቲያን መሆንን ወደደና ከአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ ከመሊትስ ዘንድ ሦስት ዓመት ከተማረ በኋላ ተጠመቀ ። በተወለደ በ30 ዓመቱ በእናቱ ሞት ምክንያት የአንጾኪያን ከተማ ለቆ ወደ ሌላ አገር መንኖ መነኮሰ ከመነኮሰ በኋላ ሁለት ዓመት በዋሻ ተቀመጠ ብዙ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ጻፈ በ380 ዓ. ም. በህመም ምክንያት ወደ አንጾኪያ ተመልሶ ከኤ ጲስ ቆጶሱ ከመሊቲየስ ድቁና ተቀበለ ። ዮሐንስ በብህትውና ሊያሳልፍ ቢሆንም የመጀመሪያ ሐሳቡ የኋላ ኋላ ግን ወንጌልን ለሕዝቡ መስበክ እንዳለበት መረጠ ። እምነትንና ፍቅርን ትሕግሥትንና ትሕትናን በአንድነት ገመዱ አስሮ ለሕዝቡ 7 ዓመት ወንጌልን ከሰበከላቸው በኋላ በ387 ዓ.ም. በአንጾኪያ ከተማ ፓትሪያርክነት ተሾመ (42)

ዮሐንስ በአንጾኪያ ከተማ 12 ዓመት ሲሰብክና ሲያስተምር ኖረ ። በዚያን ዘመን እንደ ዮሐንስ ስብከትን አሳማሪ እውነትን ተናጋሪ ተነስቶ አያውቅም ይባላል ። በቤተ ክርስቲያን በበዓል ቀን ሕዝቡ

(42) ፓትሪያርክ ማለት የግሪክ ቋንቋ ሲሆን ፓተር ወይም ፓትር አባት ማለት ነው ። ያርክ ማለት መዠመሪያ ወይም በር ከፋች ማለት ነው ፓትሪያርክ የመዠመሪያ አባት ወይ የመዠመሪያ በር ከፋች ማለት ነው ።
(43) መጽሔት እሚን ገጽ 57 — 59



ሲሰበሰብ በቀኝና በግራ እየተንገራደደ ሲሰብክ ሕዝቡ በሰሙ ጊዜ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ገሚሱ ሲስቅ ገሚሱ ያለቅስ ነበር ። ይባላል የዮሐንስንም ስብከት ለመስማት የሚሰበሰበው ሕዝብ እስከ 2 እልፍ ይደርስ ነበር እሑድ እሑድ ቀርቶ በዘወትር የሚሰበሰበው ሕዝብ ልክ የለውም ነበር ። ከስብከቱና ከአነጋገሩም ጣዕም የተነሣ ሕዝቡ ዮሐንስ አፈወርቅ ብለው ሰየሙት ይባላል ። በተአምረ ማርያም ላይ አፈወርቅ የተባለበት ሌላው ምክንያት ሰፍሮአል ።

ሐሊናው በመንፈሳዊ ሐሳብ ተገርቶ የክርስቶስ ሁኔታ ምሥጢሩ ልብ በሚነካ ስብከት እየገለጸ ከወርቅና ከብር ይልቅ የከረረ እምነትንና እውነትን ስለተናገረና ስለአስተማረ ሕዝቡ ሁሉ አፈወርቅ ወይም አፈ ዕንቁ ብለው ሰይሙት ይባላል (43)

ከላይ ያለው ታሪክ ለዋናው ነጥባችን መነሻ ይሆን ዘንድ ነው ። አሁን ወደተፈለገው ሐሳብ እንዝለቅ ለዚሁ ለዮሐንስ አፈወርቅ ሁለት ወዳጆች ነበሩት ። ንጉሡ አርቃድዮስ ንግሥቲቱ አውዶክስያም ይባላሉ ልጅ እየወለዱ ይሞትባቸዋል በምን ምክንያት ልጅ እንደማያድግላቸው ሲጠይቁ ደግ ሰው ክርስትና ቢያነሣላችሁ ይሆናል አሏቸው ። ከዮሐንስ አፈወርቅ የበለጠ ደግ ሰው አለን ብለው ሴት ልጅ በወለዱ ጊዜ መጥተህ ክርስትና አንሳልን ብለው ላኩበት ። እርሱም ጥሪውን አክብሮ ሲሔድ በመንገድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከተላከ መልአክ ጋር ይገናኛል ። የበቃ ነውና ሊያየው ችሎአል ። ዮሐንስም መልአኩን ወዴት ትሔዳለህ ብሎ ጠየቀው መልአኩም ሲመልስለት አሁን አንተ የምትሔድበትን ብላቴና ነፍሷን ከሥጋዋ ለይተህ አምጣ ብሎኝ የታዘዝኩትን ለመፈጸም ወደዚያ መሔዴ ነው ይለዋል ገናናትና ቆየኝ ላጥምቃት ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ከተሰጣት በኋላ የታዘዝከውን ትፈጽማለህ እስከዚያው ግን ከዚሁ አትንቀሳቀስ ብሎት በስልጣነ ክህነቱ ገዝቶት ሄደ መልአኩም የዮሐንስን ግዝት ጠብቆ ባለበት ቆመ ። ዮሐንስ ልጅቷን አጥምቋት ረስቶት በሌላ መንገድ ተመለሰ ።

የካህናት መዓረጋቸው ደግ እንደሆነ ስለሚያውቅ ያ መልአክ ወደ ላይም ወደታችም ሳይል አሥር ዓመት ከዚያው ሥፍራ ቆሞ ኖረ ። አሥር ዓመት ሲሆናት ለባል ታጨች ያጠመቅካት ብላቴና እነሆ ለአቅመ ሄዋን አድርሳ ባል ልታገባ ነውና መጥተህ ባርከህ ስድዳት ብለው ለዮሐንስ አፈወርቅ ላኩበት ። እርሱም በጥሪው መሠረት የዛሬ አሥር ዓመት ልጅቱን ሊያጠምቅ ሲሔድ በሔደበት መንገድ



www.ethiopianorthodox.org

ሲሔድ መልአ[illegible]ን ቆሞ አገኘው ። «ምነው ከዚህ ቆመሃል አለው?» መልአኩም ሲ[illegible] ልስለት «የካህናት መዓረጋችሁ የከበረ ነውና ሙች ወዲያ ወዲህ ያሰኛል ቃልህን አክብሬ አንተ ቆይ ካልከኝ ወዲህ ወዲያና ወዲህ ብዬ አላወቅም» አለው ከዚያም ዮሐንስ በዝንጉነቱ ራሱን ወቅሶ መልአኩን የታዘዘበትን ያደርግ ዘንድ አሰናብቶታል ። (44)

ከዚህ ታሪክ የምንረዳው ቢኖር የሥልጣነ ክህነትን ክቡርነት ነው ። እንግዲህ መልአኩም ለዮሐንስ ወንጌላዊ አትስገድልኝ ማለቱ ዮሐንስ ካህን ስለነበረ ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር ሲል በሥልጣነ ክህነት እንደሚበልጠው ሊያስገነዝበው ሽቶ ነው እንጂ ኃጢአት ሆኖ ለጣኦት እንደመስገድ የሚቆጠር ሆኖ አይደለም እንዲህማ ቢሆን ኖሮ ከታች በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብዙ ቅዱሳን ሰዎች ለመላእክት ባልሰገዱ ነበር ።

— ኦሪት ዘፍ. ፲፱ ፡ ፩—፪ «ሎጥ በግምባሩ ተደፍቶ ለመላእክት ለሚካኤልና ለገብርኤል እንደሰገደ ተዘግቧል ሁለቱ መላእክት ስህተት ሰርተሃል ለእኛ መስገድ ከፈጣሪ ጋር ያጣላሀል አላሉትም ።

መጽ. ኢያሱ ፭ ፡ ፲፫ «ኢያሱ ለመላእክት አለቃ ለቅዱስ ሚካኤል ሲሰግድለት ቅዱስ ሚካኤል አትስገድልኝ ተጠንቀቅ አላለውም ። ኢያሱም ለመላእክት አለቃ ለቅዱስ ሚካኤል መስገዱም አግባብ መሆኑን አውቆ ነው እንጂ ተሳስቶ ወይም ደንግጦ አይደለም «እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን ። የምታመልኩትን ከአሁኑ ምረጡ» በማለት አምልኮቱ በአንድ እግዚአብሔር ላይ ብቻ መሆኑን አረጋግጦአል ።

— ዜና መዋዕል ቀዳ. ፳፩ ፡ ፲፮ ዳዊትና ሽማግሌዎች ለመልአኩ በግምባራቸው ተደፍተው መስገዳቸው ተገልጾአል ። እንግዲህ ዳዊት ተገቢ ያልሆነ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ሥራ ሠራ ሊሉት ይደፍራሉ ።

— ትንቢተ ዳንኤል ፰ ፡ ፲፭ «ዳንኤል ለቅ/ገብርኤል ሁለት ጊዜ ሰግዶለታል ። ደንግጦ እንጂ ወዶ ፈቅዶ ያደረገው አይደለም የሚሉ

---

(44) የቅ ጳውሎስ መጽ ንባቡ ከነትርጓሜው ገጽ 210



ከሆነ ታዲያ ለምን በናቡከደናጾር ቁጣና በአንበሶቹ ጉድጓድ ትጣላለህ በተባለ ጊዜ ደንግጦ ለጣኦት አልሰግድም እግዘአብሔርን አልካደም? ዳንኤል በድንጋጤ ከአምልኮተ እግዚአብሔር የሚያወጣ ሥራ አልሠራም ቢሠራ ኖሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብር ሳይሆን ውርደት በጠበቀው ነበር ። ደግሞም መላእክት ግሩምና አስደንጋጭ ግርማ እንዳለባቸው ካመኑ ለምን አያከብሩአቸውም በፍጥረታቸው ሳንወድ በግድ ከመደፋታችን በፊት ወደን ፈቅደን ክብራቸውን አውቀን የፀጋ ስግደት አንሰግድላቸውም? አይ ሲገለጹ ብቻ ነው ሊሰገድላቸው የሚገባው አሁን ግን በሌሉበት እንዴት ይሰገዳል የሚሉ ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔርን ያምናምነው በዓይናችን ስላየነው አይደለም ነገር ግን የነቢያትን የሐዋርያትን ዓይን የእኛ ዓይን አድርገን የእነሱን እጅ የእኛ እጅ አድርገን በፍጹም ሃይማኖት እንዳየነው እንደዳሰስነው አድርገን እናምናለን እንጂ ካላየነው በስተቀር አንሰግድለትም አናምነውም ብንል የእምነት ሰዎች አንባልም' «ሳያዩ የሚያምኑ ብጹአን ናቸው» ዮሐን. ወን. ፳ ፡ ፳፱ ተባለ እንጂ አይተው ዳሰው ያመኑ ብጹአን ናቸው አልተባለምና እኛም በብሉይ ኪዳን የነበሩ አበውን ዓይን ዓይን አድርገን የብሉይ ኪዳንን ህግና ትምህርት እንደተቀበልን እንዲሁም የሐዋርያትን ዓይን ዓይናችን አድርገን ሐዲስ ኪዳንን አምነን እንደተቀበልን ሁሉ የቀደሙት ቅዱሳን አበው በተገለጹላቸው ጊዜ ለቅዱሳን መላእክት እንደ ሰገዱላቸው የጸጋ ስግደት መስገድም ተገቢ መሆኑን ስላስረዱን መላእክትን በዓይነ ሥጋችን ባናያቸውም መኖራቸው ግን የማይታበል ሐቅ ስለሆነ የፀጋ ስግደት በስዕላቸው ፊትም ሆነ በስማቸው በታነፀ ቤተክርስቲያን ሂደን በመንፈስ (በእምነት) እንስግድላቸዋለን «እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስ ሊሰግዱለት ይገባል» ዮሐን. ወን. ፬ ፡ ፳፬ እንየደተባለው ሁሉ «የእግዚአብሔር መናፍስት» ራዕይ ፬ ፡ ፲ ተብለው ለተጠሩት መላእክትም በመንፈስ (በእምነት) የፀጋ ስግደት እንሰግድላቸዋለን። ተገልጾላቸው በነበረ ጊዜ የሰገዱላቸው ቅዱሳን አበው ያገኙትን ጸጋ እኛም እናገኘዋለን ። እምነት ይበልጥ ፀጋን የሚያሰጠው ሳያዩ ሲያምኑና ሲታመኑ ነው ።

## ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልአክ (ሚካኤል) ነው ?

በመሠረቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምሥጋና ይገባውና የመላእክት ፈጣሪ እንጂ ከመላእክት ጋር የሚደመር ፍጡር አይደለም ። ሰይጣን ያደረባቸው ሰዎች ግን የባሕርይ አምላክ የሆነውን



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሚካኤል ጋር አንድ አድርገው ሲናገሩ ይሰማሉ ። እንዲህ ዓይነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆነ ትምህርት የሚያስተምሩት አርዮሳውያን ናቸው ።

አርዮሳውያን ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው ትምህርት ከዚህ እንደሚከተለው ባጭሩ ተገልጾአል ።

ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ በፊት (Prehuman State)
በዋችታወር ሶሳይቲ እምነት ክርስቶስ (ሚካኤል) የመጀመሪያው የይሖዋ ፍጡር ነው ። ይህንንም እምነታቸውን እንዲህ ሲሉ ይገልጡታል «ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት መላእክት ያላቸው አይነት መንፈሳዊ አካል ነበረው» (45)

በእነሱ እምነት እንግዲህ ከሥጋዌ በፊት ፍጹም መልአክ ነበረ ማለት ነው ። ሚካኤል በሚል ስም ይታወቅ ነበር ይላሉ ። በይሁዳ መ ላ ፩ ፡ ፱ ላይ ስለ ሙሴ ሥጋ የተከራከረው መልአክ ሚካኤል ክርስቶስ ነው ለይሖዋ ታዛዥ ሆነ ። ይላሉ ።

ሰው በሆነ ጊዜ (The Hman State ፡) የክርስቶስን ሰው መሆን ሲናገሩ «ይሖዋ የልጁን ሕይወት ከሰማይ ወስዶ በማርያም ማህፀን ወስጥ አስቀመጠው ። ሌሎች ልጆች በእናታቸው ማህፀን እንደሚያድጉ ሁሉ ኢየሱስም በማርያም ማህፀን ውስጥ ማደግ ጀመረ (46) በማለት ሚካኤል በሚል ስም ይጠራ የነበረው መልአክን ይሖዋ ሰው እንዲሆን እንደወሰነና ከመልአክነቱ አዋርዶ ሰው እንዳደረገው ያስተምራሉ ።

ስለዚህ ክርስቶስ ምንም እንኳን የይሖዋ ቃል ተብሎ ቢጠራም ከይሖዋ ጋር በፍጹም የተካከለ አይደለም ። ነገር ግን ለአምላክ ታዛዥ በመሆኑ የተንጣ የፀጋ አምላክ አድርጎታል ይላሉ ። ሰው ሆኖ በምድር ላይ በኖረበት ጊዜ መንፈሳዊ ሰው (Spirit Person) አል ነበረም ሰው ብቻ ነበረ ሲወለድም ፍጹም ሰዋዊ ፍጡር ሆኖ ነው ልክ እንደ መጀመሪያው ፍጡር እንደ አዳም ይላሉ ።

---

(45) ታላቁን አስተማሪ ማዳመጥ ገጽ 172
(46) ታላቁን አስተማሪ ማዳመጥ ገጽ 24



ከሥጋዌ በኋላ (The Posthuman) ፡ ይሖዋ ክርስቶስን ከሞት ባሳነሰው ጊዜ ታላቅ ኃይል መንፈሳዊ አድርጎ ነበር ያስነሳው በተነሳበትም ወቅት በሥጋው ሳይሆን በማይታይ መንፈሳዊ አካል ነው ይላሉ ሥጋውንስ በየት አኖረው ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ደግሞ እንደ ሙሴ ሥጋ ይሖዋ በፈለገው መንገድና ሁኔታ በአንድ ቦታ አስቀምጦታል ። ሩዘርፎርድ የተባለው የዋችታዎር ሶሳይቲ ሁለተኛው ፕሬዘዳንት ደግሞ ስለ ክርስቶስ ሥጋ ሲናገር «ለወደፊቱ በምትመሠረተው (በ1000 ዓመት) ማለት ነው የምድር አገዛዝ ለተመረጡ ሰዎች በኤግዚቢሽንነት ይታያል ብሏል (47)

አርዮሳውያን ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን እምነት ባጭሩ ስንገልጸው

መልአክ — ሰው — መልአክ በሦስቱ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት የለም መጀመሪያ መልአክ ነበረ ቀጥሎ በይሖዋ ትዕዛዝ ፍጹም ተዋርዶ ሰው ሆነ መልአክነቱን አጥቶ ቀጥሎም ታዛዥ በመሆኑ ከበፊቱ መንፈሳዊ ፍጡርነቱ የበለጠ ክብር አግኝቶ ልዩ መልአክ ለወደፊቱ ለምትመሠረተው አዲሲቱ ዓለም ንጉስ ይሆን ዘንድ የታጨ መልአክ ሆነ ።

ከላይ የተጠቀሰው የአርዮሳውያን ትምህርት ፍጹም ከመጽሐፍ ቅዱስ የራቀ ኢክርስቲያናዊ ትምህርት ነው ።

ጳውሎስ ወገኖቹ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ምን ብለን እንመነው መልአክ ነው ብለን እንመነው ባሉት ጊዜ ስለ ጌታችን ማንነት ሲያስረዳ «ከሆነ ጀምሮ ከመላእክቱ ማንን አለው፡ አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድኩህ ዳግመኛም አለ እኔ አባት እሆነዋለሁ እሱም ልጄ ይሆነኛል ። ዕብ ፩ ፡ ፭ ብሎ ጌታችን ከመላእክት የተለየ መሆኑን ካስረዳ በኋላ ስለ ጌታችን ሲናገር ደግሞ «ዳግመኛ በኩርን ወደ ዓለም በሰደደው ጊዜ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ይሰግዱለታል» ብሎ መላእክት ሁሉ የሚሰግዱለት የሚንበረከኩለት እንደሆነ ገልጾአል ።

---

(47) The Harp. of God P. 173



www.ethiopianorthodox.org

የመላእክት ፈጣሪ መሆኑን ሲገልጽም «ስለ መላ እክቱም አለ መላእክቱን ነፋሳት የሚላኩትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው» ይልና ስለ ጌታ መልአክ አለመሆን ሲያስረዳ ደግሞ «ስለ ልጁ ግን አለ ጌታ ሆይ ዙፋንህ ለዘላለም ነው የመንግሥትህ በትር የጽድቅ በትር ነው» ብሎአል ። ስለ ፈጣሪነቱም ሲገልጽ «ዳግመኛም እንዲህ አለ አቤቱ አንተ አስቀድሞ ምድርን ፈጠርክ ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው» በማለት «እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» ከሚለው ጋር አቆራኝቶ ነገራቸው «እነሱ ያልፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃል (ፍጡር ናቸውና) እንደ መጋረጃም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጣሉም አንተ ግን መቼም መቼ አንተ ነህ (ከእግዚአብሔርነቱ ተለውጦ እንደማያውቅ ሲናገር ነው) ዘመንህም የማይፈጸም ነው ። ከሆነ ጀምሮ ከመላእክት ማንን አለው? በቀኝ ተቀመጥ? ማንንም አላለም ብሎ መልአክ ነው ለሚሉት የማያወላዳ መልስ ሰጥቶአል ዕብ ፩ ፥ ፭—፲፬ ።

ደግሞም ጳውሎስ የክርስቶስንና የሚካኤልን አንድ አለመሆን ሲያስረዳን «ጌታችን ከሰማይ ይወርዳል በሊቀ መላእክት ቃል በእግዚአብሔር መለከት ድምጽም ያዝዛል» ፩ኛ ተሰሎንቄ ፬ ፥ ፲፮ ። ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚካኤል ጌታ ፈጣሪ እንደሆነና ሚካኤልም የእሱ ታዛዥ መሆኑን ገልጾአል ።

በዮሐንስ ራዕይ ፲፪ ፥ ፩—፲፯ ። ባለው ላይ የጌታችንና የሚካኤልን ልዩነት ግልጽ ሆኖ ሰፍሩአል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው ። ስለ ሁላችን ኃጢአት ሲል የሰውን ሥጋ ተዋህዶ በቀራንዮ አደባባይ የተሰቀለ የሞተ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ የባህርይ አምላክ ነው (48)

---

(48) ኢሳ 45 ፥ 20—24 ትን ሆሴ 13 ፥ 4 ቲቶ 2 ፥ 12—13 ሐዋ 4 ፥ 12 ሉቃ 2 ፥ 11 ትን ኢሳ 9 ፥ 6 ራእይ 1 ፥ 8, ራእይ 22 ፥ 12 ኢሳ 40 ፥ 10 የሐዋ ሥራ 1 ፥ 9 መዝ 46 (47) ፥ 5 መዝ 49 (50) ፥ 2 ዮሐ ወን 1 ፥ 1 ሮሜ ፥ 5 1ኛ ዮሐ 1 5 ፥ 20—21



## ማ ጠ ቃ ለ ያ

— ቅዱሳን መላእክት የተፈጠሩት በዕለተ እሁድ ነው መዝ ፻፵፰ ፥ ፪—፭ ።

— መላእክት ለምሕረትና ለመዓት ይላካሉ ። በአማላጅነታቸው ለሚተማመኑት ሰዎችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ያማልዳሉ ።

— መላእክት አያገቡም አይጋቡም ማቴ ፳፪ ፥ ፴ ።

— መላእክት ረቂቃን አካላት ናቸው ።

— ሊቃነ መላእክት ሰባት ናቸው ራዕይ ፬ ፥ ፮



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሦስት

## ተዝካርና ፍትሐት

መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ በምዕራፍ ፫ በቁጥር ፳ ላይ «ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል ሁሉ ከአፈር ነው ሁሉም ወደ አፈር ይመለሳል» እንዳለው ሁሉ በቀዳሚው አዳም ትዕዛዝ መጣስ ምክንያት ባጠቃላይ በአዳም ዘሮች ላይ የሞት አዋጅ ታውጇል ።

ዛሬ እገሌ ወእገሌ ሳይል ሁሉንም በጊዜው የሚያስተናግደው መልአከ ሞት ያልገባበት ቤት ያልነካው ሰው እንደሌለ አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው እሙን ነገር ነው። ሞት በእያንዳንዱ ሰው ጫንቃ ላይ ተሰይሞ ያለ ነው ። ይህ ሞት አንጀቱን ያላሳረረው ፣ በቀቢጸ ተስፋ ባሕር ያላሰጠመውና ቅስሙን ያልሰበረው ሰው ቢኖር ዓለምን ንቆ እንደ መርገም ጨርቅ ተጠይፎ ለወንጌል ያደረ የወንጌል አርበኛ ነው ። አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ግን ልቡ በሞት የደማ የሞት ባላንጣ ነው ።

የቴክኖሎጂው ርቀትና ምጥቀት የሞትን መውጊያ ሊያስወግድ አልቻለም ዛሬ በዓለማችን ላይ አሳዛኝ የሆኑ አሟሟቶች ይከሰታሉ ።

በጣም የሚፋቀሩ ባልና ሚስት በሞት ምክንያት ይለያያሉ እናት የምትወደው ልጅዋን በሞት ተነጥቃ አንጀትዋ ስፍስፍ እስኪል ታለቅሳለች ። ግን መፍትሔ አይኖረውም ። እንደ ነፍሱ አድርጎ የሚወዳት የትዳር ጓደኛው የሞተችበት ሰው ሚስቱን ዳግመኛ ሊያገኛት ስለማይችል ለሟች ሚስቱ የአበባ ዝንጣፊ በመውሰድ በሐውልትዋ ላይ በማስቀመጥ ሟች ፍቅረኛውን ያዘክራል ። ይህ ዓይነቱ ሙታንን የማዘከር ልምድ በነጮች ዘንድ የተለመደ ከሆነ ውሎ ከርሟል ።

በአንጻሩ ደግሞ በሞቱ ወገኖቻችው ሐውልት ላይ ወቅት እየጠበቁ በመሔድ ምርር ያለ ለቅሶ የሚያለቅሱና ራሳቸውን ለልክፍት አሳልፈው የሚሰጡ ሰዎች ቁጥርም ጥቂት አይደለም ።



እነዚህ ሁሉ ግን ለሟቹ የሚሰጡት ጥቅም አንዳችም የለም ። በምውታን ሐውልት ላይ አበባ የማስቀመጡ ልምድ ምናልባት ቋሚውን ሊያስደስትና ሊያረካ ቢችልም ሟችዋ ግን የመጣላትን (አበባ መዓዛ በአፍንጫዋ ስባ ትፍሥሕት ልብ የሚሰጣት ሆኖ አይደለም ። አድራጊዎቹም ይኸን አበጥረው አንጠርጥረው የሚያውቁት እውነታ ነው ። ዳሩ ግን የማይጎዳ ባሕል ስለሆነ በነጮች ዘንድ የማይቀር ልምድ ሆኖ ተይዞአል ።

በእኛ ቤት ክርስቲያን ባህል ደግሞ ከዚህ ለየት ያለ የሙታን መታሰቢያ ይደረጋል ። ምናልባት እነሱነታቸውን የዘነጉና ፈረንጅኛውን ብቻ የሚያደንቁ አንዳንዶች ይህን ጥንተ መሠረቱ ከአበው ሲያያዝ የመጣውን ሐዋርያዊ ሥርዓት ሲንቁና ሲተቹ ይታያሉ ። ይኸውም ቤት ክርስቲያን ለሞቱ ወገኖችዋ የምታደርገው ጸሎተ ፍትሐትና ተዝካር ነው ። ዛሬ ምእመናን ለሞቱ አማንያን ወገኖቻቸው የሚያደርጉት ጸሎተ ፍትሐትና ተዝካር አውሮፓውያን በሞቱ ሰዎች ሐውልት ላይ ከሚያስቀምጡት የአበባ ዝንጣፊ አንሶና ተነውሮ እንደ መጥፎ ልምድ ተቆጥሮ በአንዳንድ አላዋቂዎች ዘንድ ሲተች ይሰማል ።

ግን ቤት ክርስቲያን ሐዋርያዊት እንደመሆንዋ ሁሉ እምነትዋና ሥርዓትዋ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ።

በእያንዳንዳችን ሊጤን የሚገባው ዓቢይ እውነት አለ ይኸውም የፍጡር በደለኝነትና የእግዚአብሔር ቸርነት ። የእግዚአብሔር ርህራሄውና ቸርነቱ ወሰን የለውም ። ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ እንደተናገረው «ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው ርኅራሔው አያልቅምና» ሰቆቃው ኤርምያስ ፫ ቁ. ፳፪

በእርግጥም ነው ከሰው ልጅ ጥፋት ይልቅ የእግዚአብሔር ምሕረት እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ምድር አሸዋ የበዛ ነው ። የዝናምን ጠብታ የቆጠረ አለ? እንደዚያው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቸርነት ልንወስነው አንችልም ። ለዚህም ማረጋገጫ ዛሬ ዓለም በከፍተኛ የኃጢአት ደረጃ ላይ ሳለ ፈጥኖ በመቅሰፍት አለመጥፋቱ ነው ። ምክንያቱም ኃጢአት በሚበዛበት ቦታ የእግዚአብሔር ቸርነት ይበዛልና ። ክርስቲያኖች የአምላክን ቸርነትና ርህራሄ ያውቃሉ ይመሰክራሉ ። ይህ ያልገባቸውና ያልተዋጠላቸው ከእግዚአብሔር ቸርነትና ርህራሄ ውጭ



www.ethiopianorthodox.org

የሆኑ አንዳንዶች በእግዚአብሔር ቸርነት ጥላ ሥር የተጠለሉትን አማንያን ልቡና ለማጠራጠር በከንቱ እየደከሙ ነው ።

ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ይቅር ባይነት ወሰን የሌለው መሆኑን ስለምታምን ምንጊዜም ቢሆን ሰዎች ተስፋ እንዳይቆርጡ ታስተምራለች ከዚህ እምነትዋ በመነሣትም የበላይ ጠባቂዋ የሆነውን የመሲህ ክርስቶስን ትምህርት መሠረት በማድረግ በሃይማኖታቸው ጸንተው ለሞቱ ምዕመናኖችዋ ጸሎተ ፍትሐት ተዝካር እንዲደረግ ታዛለች ።

ምናልባት ሰው ሊጸድቅ የሚችለው በሕይወተ ሥጋ ሳለ በሠራው የጽድቅ ሥራ ብቻ እንጂ ከሞተ በኋላ በሌሎች በሚቀርብለት መሥዋዕትና ጸሎት አይደለም የሚል ጥርጥር ያለበት ሰው ቢኖር የእግዚአብሔርን ቸርነትና ማዳኑን የካደ መሆኑን ሊያውቅ ይገባዋል ። ምክንያቱም የሌሎች ጸሎትና የእግዚአብሔር ቸርነት ሳይሆን የሰው የው ፍጹምነት ብቻ ለጽድቅ እንደሚያበቃ አድርጎ መወሰዱ ነውና ። ዳሩ ግን እንኳን የሰው ልጅ ሰማያት እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐን አለመሆናቸው በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የተገለጸ ነው/ ፤

እንግዲህ ሰው ለመንግሥተ ሰማይ የሚበቃው በፍጹም ምግባሩ ሳይሆን በእግዘ አብሔር ቸርነት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። ይህ ማለት ግን ምግባር አያሻም ማለት አለመሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል ። ምግባራችን መንግሥተ ሰማያን እንድንወርስ ፍጹም አያደርገንም የእግዚአብሔር ቸርነት ካልታከለበት ለማለት ተፈልጎ ነው ። «ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለምና ።

ምንም እንኳን ንስሐ የበደለን እንዳልበደለ የምታደርግ ደገኛ ሥርዓት ብትሆንም ምን ያህሉ ሰው ነው ለኃጢአቱ ሁሉ ንስሐ የሚገባው ። በዚህም አልን በዚያ ፈቃደ ሥጋ የሰለጠነበትን ሰው በሥራው ፍጹም ይሆናል ብሎ መገመት ስህተት ነው ። በእርግጥ ከማንኛውም ሰው ዘንድ ነቅ የሌለባት ፍጽምት ሃይማኖት ትኖረው ዘንድ ይጠበቃል በሃይማኖታችን ጥርጣሬ ሊኖርብን አይገባምና በእርግጥ በምግባርም እንደሰማዩ አባታችን ንጹሐን እንድንሆን ብንታዘዝም የባህርያችን ድክመት ፍጹማን ሊያደርገን አልቻለም በእሱ ቸርነት ፍጹምነት ደረጃ ላይ የደረሱ የሉም ማለት አይደለም ሰው ግን ምንም እንኳን የፍጹምነት ሥራ የሠራ ቢመስለውም ራሱን ፍጹም አድርጎ ማቅረብ



አይገባውም ። ለዚህም ምሳሌ ቅዱሳን ከበቁ በኋላ ራሳቸውን ኃጢአተኛ አድርገው ስለሚያቀርቡ «ኃጢአታችንን ይቅር በለን» ሲሉ ይጸልያሉ ።

ማንም ሰው በምሠራው ፍጹም ምግባር ለመንግሥተ ሰማይ እበቃለሁ ቢል በዚህ ሰው ልቡና ውስጥ ዲያብሎስ እግሩን አንፈራጦ መቀመጡን ልንገነዘብ ይገባል ። እንዲህ አይነት የትዕቢት አስተሳሰብ ከጥንተ ጠላት ዲያብሎስ የተገኘ ነውና ።

የአንድ ባህታዊ ታሪክ ለምሳሌነት እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይችላል ከሰው ርቆ ንጽህ ጠብቆ ዳዋ ጥሶ ጤዛ ለብሶ ድንጋይ ተንተርሶ ድምጸ አራዊትን ጸብአጋንንትን ታግሶ ለብዙ ዘመን በብህትውና ይኖር ነበር ። ታዲያ ጌታ ተገልጾ «እንደ ሥራህ ልስጥህ እንደ ቸርነቴ» ቢለው ባሕታዊው በሥራው ተመክቶ «ቸርነትህንማ በከተማ የላመ የጣመ እየበሉ በፋሚሊ አልጋ ለሚንፈላሰሱ ምእመናን አድርገው ለእኔ ግን እንደ ሥራዬ ሥጠኝ ብሎታል»

በእርግጥ በሰው ሰውኛው አመለካከት ይህ ሰው በጾም በጸሎት በሰጊድ የተጠመደ ስለሆነ ሥራው ፍጹም ነውና ሥራው ለጽድቅ ያበቃዋል ልንል እንችል ይሆናል ። ዳሩ ግን ትሑቱ አምላክ ሳይቆጣ «እሺ እንዳልክ የሥራህን ዋጋ እሰጥሀለሁ» ነው ያለው ። የሥራው ውጤት ምን ሆነ? ከብህትውናው ወጥቶ ለብዙ ዘመን በእግዚአብሔር ጥበቃ ከኃጢአት ርቆ የነበረው ሰው በኃጢአት ማጥ ወድቆአል ።

ከዚህ የምንረዳው ቢኖር ሰው በሚሠራው ሥራ ብቻ ፍጹምና ለመንግሥተ ሰማይ የበቃ ሊሆን አይችልም የእግዚአብሔር ቸርነት ሊታከልበት ይገባል ለማለት ነው ። ከዚህ በመነሳት ለሞቱ ክርስቲያኖች የሚደረገው ፍትሐትና ተዝካር አግባባዊ መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱሳን ምሥክርነት በመጥቀስ መናገር እንችላለን ።

የእውነት አባት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የተናገረው ቃል አለ ይኸውም «ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ» የሚለው ነው ። ዮሐ.ወን. ፲፬.ቁ.፲፬ ። በመሠረቱ ይህ አባባል ግልጽና የማያከራክር ሲሆን ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን አምላካዊ ቃል መሠረት አድርጋ ለሞቱ ምእመናን ጸሎተ ፍትሐት ብታደርግ የሚያስነቅፋት ሳይሆን የአምላክዋን ቃል በፍጹም



www.ethiopianorthodox.org

አምና ተግባራዊ በማድረግዋ የሚያስመሰግናት ነው ። የሚነቅፍ የሚጠራጠር እንጂ ያረጋገጠ አይደለምና ። የአምላካችን ቃል የታመነና ተፈጻሚነት ያለው ነው ለዚህም «የተናገርኩት ቃል ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፉ ይቀላል» ብሎ የተናገረው ሁሉ ተፈጻሚ እንደሚሆን አረጋግጦልናል ማቴ. ፳፬. ቁ. ፴፭

እንግዲህ በስሜ የምትለምኑትን ማናቸውንም ነገር አደርገዋለሁ እያለ ። አንዳንድ ተጠራጣሪዎች አማኞች በእምነት ስለሞተው አማኝ ወገናቸው የሚያቀርቡትን ልመና ዋጋ ቢስ አድርገው የሚያቀርቡት ከመጽሐፍ ቅዱስ ወጥተው በራሳቸው ሐሳብ ተመርተው መሆናቸውን ሊገነዘቡ ይገባል ።

ማንኛውም ክርስቲያን በፈጣሪው ቃል ላይ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታክል ጥርጥር ሊኖረው አይገባም «የሚጠራጠር ሰው የባህርን ማዕበል ይመስላል ለዚህ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች ነገር አይደረግለትም» እንደተባለ ሁሉ ለሚጠራጦሩ ለእነርሱ ባይሆን ለምናምን ለእኛ ግን እንደ እምነታችን ይሆንልናል ።

ሐዋርያት በሲኖዶስ ስለሞቱ ሰዎች ነፍስ ከገንዘባቸው ለድሆች ለጦም አዳሪዎች ይሰጡ ዘንድ እንዲህም አድርጉ ብለን የምናዘው በሃይማኖት ጸንተው ለሞቱ ሰዎች ነው እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ መሲሕ ክርስቶስን ለሚክዱ (ለካዱ) ሰዎችስ በዓለም ያለውን ገንዘብ ኹሉ ቢመጸውቱላቸው ምንም አይጠቅማቸውም ብለዋል ።

ይህን ጌታ ራሱ ተናግሮታል «በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ ግን በዚህ ዓለምም ቾነ በሚመጣው በደሉ ይቅር አይባልለትም» ማቴ. ፲፪. ቁ. ፴፪ ።

በዚህ ዓለም የሚለው በሕይወተ ሥጋ እያለ ማለት ሲሆን በወዲያኛው ዓለም ሲል ደግሞ በአጸደ ነፍስ ያለውን ማንሳቱ ነው ።እንግዲህ በአጸደ ነፍስ ንስሐ ኖሮ አይደለም ዳሩ ግን በምድር ላይ ያሉ ወገኖቹ በሚያቀርቡለት ጸሎተ ፍትሐትና ተዝካር መማሩንና አለመማሩን ሲገልጽ ነው ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስንና ጌታችን ክርስቶስን ፍጡር ያላለ የባህርይ አምላክነቱን የማነ የቤተ ክርስቲያን አባል ከሆነ የሚደረግለት ጸሎተ ፍትሐት እንደሚጠቅመው መግለጹ መሆኑን ሁላችንም ልብ ልንል ይገባል ።



በሃይማኖት የሚመሥሉን ወገኖቻችን ሲሞቱ በሠሩት ኃጢአት ሞተ ነፍስ ተፈርዶባቸው ሲያል እንዳይገቡ መንግሥተ ሰማይ እንዲገቡ ብንጸልይ አንድም ፍቅርን ያመለክታል ከዚህም በተጨማሪ በወንጌል ቃል ላይ ያለንን ጽኑ እምነት ይገልጻል ።

በወንጌል ላይ እንደተዘ፤በው ጌታችን በዚህች ምድር ላይ በሥጋ ተገልጦ በሚመላለስበት ወቅት የእምነት ገመድ ስቦ ያመጣቸው ብዙ ሰዎች የሞቱ ወገኖቻቸውን እንዲያስነሳላቸው ያለምንም ጥርጥር ለምነውት ወገኖቻቸውን ከሞተ ሥጋ አድነዋል እንግዲህ ክርስቶስ ከሞተ ሥጋ ብቻ ሳይሆን ከሞተ ነፍስም ማዳን የሚችል የባህርይ አምላክ መሆኑን የሚያምን ሰው ሁሉ በፍጹም እምነት በሞት ለተለዩት ወገኖቹ በሠሩት ኃጢአት እንዳይፈረድባቸውና ከሞተ ነፍስ እንዲድኑ ቢለምን በእምነት ያቀረበው ጸሎት በጌታ ዘንድ ተቀባይነት አለው ጌታ አያደላምና ፡

ነገር ግን ጌታን ፈጽመው ለካዱ ቋንጃ ሲቆርጡ ደም ሲያፈሱ ለነበሩ አረመኔዎች ማርልን ብለን ጌታን የምንጨቀጭቅ አይደለንም ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ይቅር የማይባል ኃጢአት አለና ዮሐንስም በመልእክቱ እንደገለጸው «ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል ። ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ ስለዚያ እንዲጠይቅ አልልም አመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው ሞትም የማይገባው ኃጢአት አለ» 1ኛ ዮሐንስ መል ፭ ቁ. ፲፮—፲፯ ።

ቤተ ክርስቲያንም ይህን አምላካዊ ቃል መሠረት አድርጋ ሃይማኖታቸውን ከደው ምግባር ትሩፋት አያስፈልግም ብለው አውቀው በኃጢአት ባህር ሲዋኙ ለኖሩ ሰዎች ቢሞቱ ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ አትፈቅድም ። ዳሩ ግን በሃይማኖት ጸንተው ምግባር ትሩፋት ለመሥራት ቀና ደፋ ሲሉ ለነበሩ አማንያን በሞቱ ጊዜ ጸሎተ ፍትሐትና ተዝካር ታደርጋለች ። ለሟቹም ሆነ ለቋሚው የሚጠቅም መሆኑንም ታምናለች ።

በወንጌል እንዲህ የሚል ታሪክ ተዘግቧል ። አንድ የምኩራብ አለቃ ልጁ ታማበት ጌታችንን እንዲፈውሳት ሊለምነው ወደ ጌታ ዘንድ ይሔዳል ዳሩ ግን ልጅቱ መሞትዋን ሌሎች ያረዱታል ውጤት ለሌለው ነገር ጌታንም ማድከም አስፈላጊ አለመሆኑን ነገሩት ። ምንም



www.ethiopianorthodox.org

እንኳን መልእክተኞቹ ተስፋ ሊያስቆርጡት ይህን ቢናገሩም ጌታ ግን ለዚያ ሰው የተናገረው ቃል የሚያጽናና ነበር «እመን ብቻ እንጂ አትፍራ» የሚል ይህ አነጋገር ቀቢጸ ተስፋን እንደጢስ አትና እንደ ጉም አብና ከዚያ ሰው ህሊና ያጠፋ ነበር ፡፡ በእርግጥም ጌታ እንደተናገ ረው የሞተችይቱን ልጅ አስነስቷታል ፡፡ ማርቆስ ፭ ቁ. ፴፭—፵፫ ፡፡

አዎን «የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ቢኖራችሁ...... የሚሳና ችሁ ነገር የለም» ማቴ ፲፯ ቁ. ፲፱ መባሉን ከህሊናችን ሰሌዳ ላይ ልን ፍቀው አይገባም በወንጌል የተጻፈው ሁሉ የዘመን ፍፃሜ የደረሰብንን እኛን ሊያስተምርና ሊገስጽ እንደተጻፈ ከማንኛውም የወንጌል አማኝ የተሰወረ ነገር አይደለም ፡፡ ታዲያ ከምኩራቡ አለቃ በዛሬ ዘመን ያለነው ክርስቲያኖች የተማርነው ትምህርት ምንድን ነው በእምነት ለሞቱ ወገኖቻችን ሞተ ነፍስ እንዳያገኛቸው ብንጸልይ ከወንጌል ውጭ ያሰኘናል በፍጹም ፡፡ እንዳውም በፍጹም ልባችን በጌታችን አምነንና ተማምነን በሙሉ ተስፋ መለመን እንዳለብን ጌታችን በዚህ ሰው አንጻር አስገንዝቦናል ፡፡

ዛሬም ቢሆን እኮ እኛ ለሞቱ አማንያን ወገኖቻችን የምናደርገ ውን ጸሎተ ፍትሐት እንደማይጠቅምና እንደፈሰሰ ውኃ አድርገው የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ እነዚህ ወገኖች ከላይ በማርቆስ ወንጌል እንደተጠቀሰው ሁሉ የምኩራቡን አለቃ ተስፋ ለማስቆረጥ እንደሞከ ሩት ሰዎች ሲመስሉ በክርስቶስ ላይ እምነት ያለው ክርስቲያን ግን ጌታ ለምኩራቡ አለቃ «እሙን ብቻ እንጂ አትፍራ» ያለውን አምላ ካዊ መልስ በልቡናው ጽላት ላይ ቀርጾ ተስፋ ባለመቁረጥ ቤተ ክርስ ቲያን ያዘዘችውን ማድረግ አለበት ፡፡ የምኩራቡ አለቃ ልጅ ከሥጋ ሞት እንደተነሳች ሁ ሉ ዛሬም በሕይወት ሥጋ ያለው ክርስቲያን ከዝች ምድር ላይ በሞት ለተለየው ክርስቲያናዊ ወገኑ ዘላለማዊ ሞት እንዳይ ገጥመው ቢጸልይለት ጌታ እንደ እምነቱ ያደርግለታል የሚል እምነት አለን ፡፡

ተስፋ መቁረጥ የአሕዛብ እንጂ የክርስቶሳውያን አይደለም ክርስ ቲያን ባለ ተስፋ ነው «በተስፋ ደስ ይበላችሁ» ተብሎ እንደተጻፈ ሮሜ ፲፪. ቁ. ፲፪ ፡፡

ይህን እንድናስተ ውል ይገባል ፡፡ ዛሬ በክርስቶስ ደም ተመሥር ተናል ያልነው ሰዎች ጥንት ጌታ በሥጋ ይመላለስ በነበረበት ወቅት



ካሉት ሰዎች ያነሰ እምነት እንዳለን ፡፡ ምክንያቱም እነዚያ አምላክ ወልደ አምላክ በሥጋ መምጣቱን ሳያውቁ ዳሩ ግን በእምነት ብቻ የሞቱ ወገኖቻችውን እንኳን እንዲያድን እንደ ተማጸኑት ፡፡ በእምነት ያቀረቡት ልመና ግን መልሱ ልቡናን በትፍስሕት የሞላ እንደሆነ ወንጌልን ስናነብ የምናገኘው አማናዊ ነገር ነው ፡፡ ዛሬ ግን እኛ ከእነሱ ይልቅ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አውቀን በስሙ አምነን ተጠምቀን እያለ ነገር ግን የአምላካችንን የማዳን ኃይል የምንጠራጠር አለን የአምልኮት መ ልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደውታል» የተባለው ለእንዚህ ከሀዲዎች ነው ፡፡ ስለዚህ የአምላካችንን የማዳን ኃይል በፍ ጹም ልባችን የምናምን ክርስቲያኖች በእምነት ለሞቱ ወገኖቻችን የምናቀርበው ፍትሐትና ጸሎት ተዝካር በአየር ላይ የሚቀር ሳይሆን በቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ ግብ የሚመታ ነው ፡፡ በወንጌል ተከትቦ የምናነበው ሁሉ የሚያረጋግጠው ይህን ነውና በእምነት ወደ ክርስ ቶስ የቀረቡ ሁሉ ድህነተ ሥጋ እንዳገኙ ዛሬም ክርስቲያኖች በእምነት ወደ ጌታችን በመቅረብ የሞቱ ወገኖቻችን ድህነተ ነፍስ እንዲያገኙ ልናስደርግ እንችላለን «የምትሹትን ለምኑ ይሆንላችሁማል» ተብለ ናልና ለሚጠራጠር ሰው ግን ከጌታ ዘንድ አንዳች አይደረግለትም ፡፡ እምነታችን ነቀ የሌለበት ፍጹም እንዲሆን ተጽፏልና ፡፡

«እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል» ዮሐንስ ወን ፲፬. ቁ. ፲፪ በዚህ አምላካዊ ቃል መሠረት ዛሬ ካህናት አባቶቻችን ለሞተው ምእመን የሚያቀርቡት ጸሎተ ፍትሐት ጠቀሜታ እንዳለው እንገነዘባለን ፡፡

በኢዮጴ የተፈጸመው አማናዊ ድርጊት ለእዚህ እምነታችን ዓይነተኛ ምሥክር ነው ፡፡ «በኢዮጴጣቢታ የምትባል መልካም ደቀ መዝሙር ሞተች ደቀ መዛሙርቱ ጴጥሮስ በዚያ አካባቢ እንዳለ ሰም ተው ወደ እነርሱ እንዲመጣ ለመኑት ጴጥሮስም መጥቶ ተንበርክኮ በመጸለይ ጣቢታ ሆይ ተነሺ ብሎ ከሞት አስነስቷታል ሥራ ፱. ቁ. ፴፮—፵፫ ፡፡

እንደዘሁ ሁሉ እንደ ጣቢታ የሞተው ምእመን እንደ ደቀ መዛ ሙርቱ የሚች ወገኖች እንደ ጴጥሮስ ወደ ጌታ ለምኖ ጣቢታን ከሞት ሥጋ እንዳስነሳት ሁሉ ዛሬም አእይንተ እግዚአብሔር የተባሉ ካህናት ወደ ጌታ ጸልየው ከሞተ ነፍስ ያድኑታል ፡፡ ስንል እናምናለን ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ሎሞተው ምእመን ወደ ጌታ ጸልየው ከሞተ ነፍስ ያድኑታል ። ስንል እናምናለን» ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ሥም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰርይለታል» ያዕ. ፭. ቁ. ፲፬ ።

ከዚህ እንደምንረዳው የእምነት ጸሎት ከኃጢአት ማሠሪያ እንደሚፈታ ነው ። ምንም እንኳን ሟች ራሱ ጠጥቶ ጸልዩልኝ ባይልም ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ሁሉ ብዙዎች ፈውሱን ያገኙት በወገኖቻቸው ልመናና ምልጃ መሆኑን ማስተዋል ይገባል ። ጌታም እምነታቸውን አይቶ እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ በማለት የፈለጉትን ፈጽሞላቸዋል ።

ሐዋርያት በሲኖዶስ እንዲህ ብለዋል «የሞቱ ዘመዶቻችሁን ኹል ጊዜ በቁርባን በቅዳሴ አስቧቸው ይህ እነሱን እጅግ ይጠቅማቸዋል ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር በባለሟልነት ያቀርባቸዋልና ።»

ርቱእነ ሃይማኖት 318 ሊቃውንትም በፍትሐ ነገሥት «ጌታ በሦስተኛው ቀን ስለተነሣ ስለሞቱ ሰዎች በመዝሙር በጸሎት በሣልስቱ መታሰቢያቸውን አድርጉ እንዲሁም የእስራኤል ልጆች በሞዓብ ሜዳ ሠላሳ ቀን ለሙሴ ያለቀሱለትን በማዘከር እናንተም በቀደሙቱ ሰዎች አምሳል ለሞቱ ወገኖቹ ቤተሰቦቻቸው በሠላሣቸው መታሰቢያቸውን አድርጉላቸዋል ።

ከሞተው ሰው ገንዘብ ለነዳያን ስጡ መታሰቢያ ይሆንለት ዘንድ በዚያን ቀን ብትጠሩ በሥርዓትና እግዚአብሔርን በመፍራት ብሉ።(49)

ከሰባ አርድእት አንዱ የሆነ ቀሌምንጦስ ወንጌልን በዓለም ዞሮ እንዳስተማረ ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ በፊልጵ ፬. ቁ. ፫ ላይ መስክሮለታል ይህ ቀሎምንጦስ ለምውታን አማንያን ሊደረግ ስለሚገባው ነገር እንዲህ ይላል ።

---

49 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 22



«ለሞተ ሰው ከገንዘቡ ለነዳያን ይመጽውቱለት ቁርባን ያስቀርቡለት ዕጣን ያሳርጉለት ነፍስ ከሥጋዬ ከተለየሁ በኋላ ከቁርባን ከዕጣን ከመሥዋዕት በቀር ምንም የረባኝ የጠቀመኝ ነገር የለም ዕረፍትም የለኝም መሥዋዕት በተሠዋልኝ ቁርባን በተቀረበልኝ ዕጣን በታጠነልኝ ጊዜ ግን ከዘመዶቼ ጋር ደስ ይለኛል ብላለችና ሙሽራው በጫጉላው ከዘመዶቹ ጋር እንዲደሰት ለነፍስም ዕጣን ካሳጠኑላት መሥዋዕት ከሠውላት ቁርባን ከአስቀረቡላት ከዘመዶቿ ጋር በሰማይ ተድላ ደስታዋ እንደዚህ ነው ።

ዘመዶቻችሁን ከወደዳአችሁስ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጃት ዓይን ያላያት ጆሮ ያልሰማት መንግሥተ ሰማያን ይወርሱ ዘንድ ጸልዩላቸው ንጹሕ መሥዋዕት ሠውላቸው ቁርባን አስቁርቡላቸው ለነዳያንም መንፈሳዊ ምጽዋት መጽውቱላቸው ።

ለአባቶቻችሁ ለወንድሞቻችሁ ለልጆቻችሁ ለወገኖቻችሁ ተዝካር አውጥታችህ ላቸው ፍታት አስፈትታችሁላቸው ይህን በማድረጋችሁ ከነሱ ጋር ደስ ይላችሁ ዘንድ ይህን አድርጉ ብዬ እነግራችኋለሁ እንደ አረማውያንና እንደ አሕዛብ ከሞቱ በኋላ ምን ይረባቸዋል ምን ይጠቅማቸዋል አትበሉ እንዲህም የሚሉ ሰዎች ትንሣኤ ሙታን እንዳለ የማያምኑ ተስፋ ትንሣኤ የሌላቸው ናቸው» (ቀሌምንጦስ ተመልከት)

አንድ ምእመን ሲሞት ወደ መቃብሩ በሚጓዝበት ጊዜ በሰባት ምዕራፍ ሰባት ጊዜ ጸሎተ ፍትሐት ማድረስ ይገባል ፤ ይኸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወረሰ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓት ነው እስራኤል የኢያሪኮን ከተማ ሰባት ጊዜ እየዞሩ በጸለዩ ጊዜ የብረት ቅጥሩ (አጥሩ) ፈራርሶ ወድቋል) መጽ. ኢያሱ ፮. ቁ. ፳ ።

የዘሙኑ ሐዲስ ካህናትም ጽንሐውን ይዘው እያጠኑ ቤተክርስቲያኑን ሰባት ጊዜ እየዞሩ ለእስራኤል የኢያሪኮን ቅጥር እንዳፈራረሰ ሁሉ ዛሬም የምእመናኑን ኃጢአት ደምስስልን በማለት ይጸልያሉ ለሞተውም ምእመን በዚሁ ምሳሌ ሰባት ጊዜ እየጸለዩ ቅጽረ ኃጢአቱን አፍርስለት (ማረው ይቅር በለው) እያሉ ጸሎተ ፍትሐቱን ያደርሱለታል ።



www.ethiopianorthodox.org

በተጨማሪም ነቢዩ ኤልሳዕ የሞተውን ሰው ሰባት ጊዜ ጸልዮ አስነስቶታል ። ነገሥት ካልዕ ፬. ቁ. ፴፫—፴፮ ። በዚያ ምሳሌ ዛሬም ለሞተው ሰው በሰባት ምዕራፍ ሰባት ጊዜ ጸሎተ ፍትሐት ይደርሳል ።

ዳግመኛም ልዩ ምሥጢር አለው ሰባት፣ሰው ሰባት ባሕርያት ያሉት መሆኑን ያመለክተናል ሰው ማለትም ከሰባት ነገሮች የተሠራ ማለት ነውና ። እነዚህም አራቱ ባሕርያተ ሥጋ እሳት ፣ መሬት ፣ ውሃ ፣ ነፋስ ሲሆኑ ሦስቱ ባሕርያት ነፍስ ደግሞ ለባዊነት (ልብማድረግ) ነባቢነት (መናገር) ህያውነት ናቸው ። በእነዚህ በሰባቱ ባሕርያት ተደፋፍሮ የፈጸመውን ኃጢአት ይቅር ብለህ ማርልን ብሎ መጸለይ ነው ።

እንዲሁም በዕብራውያን አቆጣጠር ሰባት ቁጥር ፍጹም ስለሆነ የሞተውን ምእመን መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ፍጹም አድርግልን ብሎ መለመን ነው ። 50

(50) መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ 44



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አራት

## ስለምንኖርባት ምድር ማለፍና ስለመንግሥተ ሰማይ

ይህቺ ዛሬ በሕይወተ ሥጋ የምንኖርባት ዓለም እንደም ታልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ። «ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም» ማቴ ፳፬፥፴፭ ነገር ግን ይኼን አምላካዊ ቃል ባለመቀበል አንዳንዶቹ ምድር ለዘላለም እንደምትኖርና ለዘላለም በምድር ላይ እንደሚኖሩ የሚናገሩ ክፍሎች ተከስተዋል ።

በእነዚህ ክፍሎች እምነትና ትምህርት ከክርስቶስ ልደት በፊት ያሉት ቅዱሳን አበው ሁሉ ወደ ሰማይ አይሄዱም በእነሱ እምነት ወደ ሰማይ የሚሄዱ ሰዎች ወደፊት በምድር ላይ ለሚመሠረተው የአምላክ መንግሥት ገዢዎች በመሆናቸው ታይተውና ተፈትነው ያለፉ የክር ስቶስ ተከታዮች መሆን አለባቸው ። ስለዚኅ በክርስቲያናዊ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ያልተፈተኑ ሕጻናት ወይም ትንንሽ ልጆች ወደ ሰማይ አይወሰዱም ማለት ነው ። በዮሐንስ ራዕይ በም ፲፬ ፣ ፩—፫ ባለው ላይ በተገለጸው መሠረት በሰማያዊ የጽዮን ተራራ ከበጉ ከኢየሱስ ክር ስቶስ ጋር የታዩት 144 000 ሰዎች ብቻ ወደ ሰማይ እንደሚሄዱ ያስት ምራሉ ። ስለዚህ ጥሩ ሰዎች ሁሉ ወደ ሰማይ አይሄዱም ከዚህ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ የተፈተኑና ታማኝ የሆኑ 144 000 ሰዎች ብቻ ከክር ስቶስ ጋር ለመግዛት ወደ ሰማይ እንደሚወሰዱ ያሳያል ይላሉ ። (51)

በአጭሩ አርዮሳውያን ስለ ወደፊቱ ተስፋ ያላቸው እምነት እንደ ሚከተለው ይገለጻል ። ከምድር የተዋጁት 144 000 ሰዎች «ታናሹ መንጋ (Anointed Class) ለወደፊቱ በምድር ላይ ትመሠረታለች ብለው ለሚናገሩት የአምላክ መንግሥት ከክርስቶስ ጋር ገዢዎች የሚሆኑ ሲሆኑ የተቀሩት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩት ሌሎች

---

(51) በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ ገጽ 124



www.ethiopianorthodox.org

በእነሱ አጠራር «ትልቁ መንጋ» (Great Crowd) የሚባሉት ደግሞ የ144 000 ሺዎቹ ተገዢዎች ሆነው በምድር ላይ ለዘላለም ይኖራሉ ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት ያሉት ቅዱሳን አበው ሁሉ«ከትልቁ መንጋ» ውስጥ ነው የሚመደቡት የእምነት አባት የተባለው አብርሃም ሁሉ ሳይቀር ወደ ሰማይ አልሄደም አይሄድምም በእነሱ ትምህርት ።

ስለ «ትንሹ መንጋ» ማንነት ሲጠቅሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሰማይ የሄደው ክርስቶስ ነው ዋነኛው ገዢ እሱ ነው ከዚያ በኋላ የእሱ ተከታይ የነበሩት ሐዋርያት ተከትለዋል ዛሬም ቢሆን ከተለያዩ ዓለማት ወደ ሰማይ የሚሄዱ ሰዎች አሉ ። የመጨረሻው ሰው ወደ ሰማይ በሔደ ጊዜና 144 000 ሰዎች በተሟሉ ጊዜ የአምላክ መንግሥት በምድር ላይ መግዛት ትጀምራለች ይህንንም እንዲህ ይገልጹታል «ይህ አዲስ ንጉሣዊ መንግሥት የመግዛት ሥልጣኑንና መብቱን የሚቀበለው ከታላቁ ንጉሥ ከይሖዋ አምላክ ነው ። ይህ የእርሱ መንግሥት ነው ። መጽሐፍ ቅዱስም በተደጋጋሚ «የአምላክ መንግሥት» ብሎ ይጠራዋል ሆኖም ይሖዋ ልጁን የዚህ መንግሥት ዋና ገዢ አድርጎ ስለሾመው የክርስቶስ መንግሥት ተብሎም ተጠርቷል ።... ከሰው ዘር ካከል የተመረጡ 144 000 ሺዎቹ በዚህች መንግሥት ውስጥ ከክርስቶስ ጋር ይገዛሉ ። በዚህ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ «የእነሱ መንግሥት» እንደሆነም ጭምር ይናገራል ።... ከክርስቶስ ጋር በሰማይ በሚነግሡት በ144 000ዎቹ ብቻ የሚገዛ መንግሥት ነው በዚህም ምክንያት ይህ አገዛዝ ሰማያዊ ተስፋ ካላቸው ከእነዚህ ገዢዎች ውስጥ የመጨረሻው አባል ሲሞትና በሰማይ ከክርስቶስ ጋር ሲተባበር ያበቃል ። ከዚያ በኋላ የክርስቶስ ተገዢዎች አይሆኑም ከእርሱ ጋር ነገሥታት ይሆናሉ እንጂ (52)

ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከላይ የተጠቀሰውን የአርዮሳውያን ትምህርት በፍጹም አይደግፈውም እነርሱ እንደሚሉት 144 000 ሺው ከመላው ዓለም የተወጣጡ እንደሆኑ ነው ። ዮሐንስ ራዕይ ፯ ፥ ፬—፰ እንደሚለው ደግሞ 144 000 የእሥራኤል ወገን ብቻ እንደሆኑ ነው ይህንንም ሲተነትን ከ12ቱ ነገደ እሥራኤል ከእያንዳንዱ 12 000 በሃይማኖት ፍጹማን የሆኑ ማለት ነው ። እንደተመረጡ ነው ። ከእያን

---

(52) በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ ገጽ 136



ዳንዱ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ሲመረጥ ከአሥራ ሁለቱ ነገድ አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ ይሆናል ። ዮሐንስ 144 000 ከእሥራኤል ወገን ብቻ እንደሆኑ ከጠቀሰ በኋላ ከዚህ በኋላ ከሕዝብም ከአሕዛብም ወገን ስፍር ቁጥር የሌላቸው በመንበሩ ፊት በበግዑም ፊት ቁመው ብዙ ሰዎች አየሁ ብሏል ። እንግዲህ እነዚህ በቁጥር እጅግ የበረከቱት ሰዎች በአርዮሳውያን እምነት «ትልቁ መንጋ» ተብለው የሚጠሩት ሲሆኑ የ144 000 ሺዎቹ ተገዢዎች ናቸው ማለት ነው ። ይህ ግን ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ። የባሕርይ ገዢ ክርስቶስ ብቻ ነው 144 000 ሰዎቹም ሆኑ ሌሎች የሚወርሱት አንድ መንግሥተ ሰማይንነው ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በራዕይ የተጠቀሱት 144 000 ሺዎቹ ከእሥራኤል ወገን ብቻ ከሆነ «በትንሹ መንጋ» ውስጥ ሊሆኑ የሚችሉ የሌላ አገር ወገኖች የሉም ማለት ነው ። ስለዚህ ከትንሹ መንጋ ለመሆን የሚፈራረጡ ብዙ የዋህን ከአሁን ተስፋቸውን ቢቆርጡ መልካም ይመስለኛል ምክንያቱም 144 000 ሺዎቹ ከእሥራኤል ወገን ብቻ ናቸው ። በተጨማሪም ስለ 144 000 ሰዎች በራዕይ ፲፬ ፥ ፩—፭ ባለው ላይ እንደተገለጸው «...ከሴቶች ጋር ያልረከሱ ደናግሎች በአፋቸውም ውሸት አልተገኘም ነውር የለባቸውም» ይላል ።

እንግዲህ ዛሬ ከ144 000 ሰዎች ውስጥ ለመሆን የሚጥሩ የአርዮሳውያን አባሎች ከሴት ርቀው ንጽህ ጠብቀው በድንግልና ይኖራሉ? ይልቁንስ ድንግልናን የሚያወግዙ አይደሉምን ። ከሴት ጋር ከረከሱ ከ144 000 ሺዎች ውስጥ እንደማይሆኑ ይወቁት ።

እንዲሁም ከ144 000 ሺዎች ውስጥ ናቸው ብለው ከተናገሩላቸው ከሐዋርያት ውስጥ ሚስት ያገቡ እንደ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጸው እውነታ ነው ። ለምሳሌ ፦— ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስን ብንወስድ ሚስት እንደነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል «ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት ገብቶ አማቱን (የጴጥሮስን) በንዳድ ታማ...» ማቴ ፰ ፥ ፲፬ ።

እንግዲህ ዮሐንስ የተናገረላቸው 144 000 ሰዎች ከሴት ያልረከሱ ደናግል ከሆኑ ጴጥሮስ ከ144 000 ሰዎች አንዱ እንዴት ሊሆን ይችላል?

ለመሆኑ ከምድር የተዋጁት 144 000 እነማን ናቸው? ዮሐንስ ግልጽ አድርጎ እንዳስቀመጠው ከሴት ጋር ያልረከሱ ደናግሎች በአፉ



www.ethiopianorthodox.org

ቸውም ውሸት አልተገኘም ነውር የለባቸውም የተባለላቸው ሄሮድስ ያስፈጃቸው የቤተልሔም ሕጻናት ናቸው ሚቴ ፪ ፡ ፲፰ ።

አርዮሳውያን ግን ከላይ የተጠቀሰውን መመዘኛ ነጥብ ሙሉ በሙሉ የሚያሟሉትን ሕጻናትን ንቀው «ከትንሹ መንጋ» አይደሉም በማለት እንደተናገሩት ከላይ ጠቅሰነዋል ። ይህም የሚያሳየው ትምህርታቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትነት እንደሌለው ነው ።

እራሱ ጌታ ለሐዋርያት ሲያስተምር «ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አትከልክሏቸው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና እውነት እላችኋለሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕጻን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባበትም አላቸው» ማር ፲ ፡ ፲፫

እንግዲህ ሕጻናት በሃይማኖት ፍጹማን ስለሆኑ ለፍጹማን ምሳሌ ሆነው በጌታ አንደበት እየተነገረላቸው በአርዮሳውያን ዘንድ ግን ተንቀው ተተፍተው እናገኛቸዋለን ።

ስለዚህ ከላይ እንዳየነው የአርዮሳውያን «የትንሹ መንጋና የትልቁ መንጋ» ትምህርት በተረትነቱ ስናደንቀው በተአማኒነቱ ግን የበሬ ወለደ ዓይነት ሐሰት ሆኖ አግኝተነዋል ።

መንግሥተ ሰማይ እገሌ ይገባበታል እገሌ አይገባበትም የምትባል አይደለችም ጽድቅ ሠርቶ የተገኘ ሁሉ ይገባበታል «ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብጹዓን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና» ማቴ ፭ ፡ ፲ እዚህ ላይ ገዢዎች ተገዢዎች የሚል ነገር ተጠቅሶ አናገኝም ባጠቃላይ ጽድቅን የሚፈጽሙ ሁሉ በአንድ ሥፍራ እንደሚሆኑ ተናገረ እንጂ»

በምድር ላይ የአምላክ መንግሥት ይመሠረታል የሚለው አባባላቸውን ጳውሎስ ሲነቅፍ «ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉና ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ መጨረሻቸው ጥፋት ነው ሆዳቸው አምላካቸው ነው ክብራቸው በነውራቸው ነው አሳባቸው ምድራዊ ነው እኛ አገራችን በሰማይ ነውና» ፊሊጵ ፫ ፡ ፲፱ ።

የሁሉም ክርስቲያኖች ተስፋ አንድ ነው ሁሉም በአንድ ልብ ሆኖ የሚጠብቀው አንድ ዓይነት ተስፋ ነው ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ነው ። ምድር ግን እንደምታልፍ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘ ሁሉ



ያምናል መሪያችን ፈጣሪያችንና አምላካችን ክርስቶስ ምድር እንደምታልፍ ነግሮናልና ምናልባት «ምድር ግን ለዘላለም ነች» መክብብ ፩ ፡ ፬ ያለውን በመጥቀስ የምድርን ማለፍ የማይቀበሉ ይኖሩ ይሆናል ይህ አባባል ግን የምድርን ለዘላለም ጸንቶ መኖር የሚገልጽ አይደለም ሰሎሞን እዚህ ላይ ሊያስገነዝበን የፈለገው አንዱ ትውልድ ሲያልፍ ሌላው ትውልድ ሲተካ ምድር ግን ከትውልድ ጋር አብራ ሳታልፍ ሳትለወጥ ሌላውን አዲስ ትውልድ ታስተናግዳለች በዚህ ዓይነት ሁኔታ እስከ ፍፃሜ ዓለም ትቀጥላለች ማለቱ እንጂ በመጨረሻው ዘመን አታልፍም ማለቱ አይደለም ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማለፍዋን በማይታበል ቃሉ ነግሮናል ። ማቴ ፳፬፡፴፭

እንዲሁም ማቴ ፭ ፡ ፭ «የዋሆች ብጹዓን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና» መዝ ፴፮(፴፯)፡፱—፲፩«እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ምድርን ይወርሳሉና ገሮች ምድርን ይወርሳሉ» የሚለውንና መሰል ጥቅሶችን በመጥቀስ በምድር ላይ የአምላክ መንግሥት ይሆናል ብለው ሊያስመስሉ ሲሞክሩ ይስተዋላሉ ።

ነገር ግን በምድር የተመሰለችው መንግሥተ ሰማይ ናት ስለምን ምድር ብሎ ጠራት ቢሉ ፡—

1ኛ/ ምድር አልፋ እሷ የምትተካ ስለሆነ ነው እንዲህ ሲባል ግን መንግሥተ ሰማይ በምድር ምትክ ትፈጠራለች ማለት ሳይሆን ደግ የሠሩት ሰዎች በእስዋ ይኖራሉ ይህችኛዋ ግን ከመኖር ወደ አለመኖር ታልፋለች ማለት ነው

2ኛ/ በምድር በሚሠሩት የጽድቅ ሥራ የምትወረስ ስለሆነ መንግሥተ ሰማይን ምድር ብሎ ጠርቷአታል ።

3ኛ/ ምድራውያን ጻድቃን የሚወርሷት ስለሆነ

4ኛ/ በምድር ተድላ ሥጋ ይፈጽማል ይደረጋል እንዲሁም በመንግሥተ ሰማይም ተድላ ነፍስ ይፈጸማልና መንግሥተ ሰማይን በምድር መስሎ ጠራት ።

በተለያዩ ሥፍራዎች «ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ የሚል አባባል ቢገጥመን ይህችን ምድር አለመሆንዋን ማጤን ይገባል ። የሚከተሉትን ማስረጃዎች በጥሞና አጢን ።



www.ethiopianorthodox.org

፪ኛ ቆሮ ፭ ፥ ፩ «ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለን»

ትንታኔ ፥ የነፍሳችን ማደሪያ የሥጋችን መኖሪያ ይህ ዓለም ሲያልፍ በእግዚአብሔር ዘንድ የሰው ልጅ ያልፈጠረው ሌላ ዓለም እንዳለን እናውቃለን ። ምናልባት በእያንዳንዳችሁ ህሊና ምነው ይህን የምንኖርበትን ዓለም የሰው እጅ ፈጥሮታልን? እንዴት እንዲህ ሊል ቻለ? ልትሉ ትችሉ ይሆናል ። በእርግጥ ይህ ዓለም የፈጣሪ የእጁ ሥራ ቢሆንም በዕሩቅ ብእሲ (በፍጡር) ይናኛል ፥ ያ ግን በዕሩቅ ብእሲ እጅ አይናኝምና ። እንዲህ ብሎአል ።

በልዕልና ያለ ያንን ዓለም እንድንወርስ ተስፋ እናደርጋለን (መንግሥት ሰማይን ማለቱ ነው (ዛሬ መከራ የምንቀበልበት) በመከራው የምንደክምበት ያን ዓለም ከወረስነው በኋላ እናዝንም ነገር ግን በዚህ ዓለም ሳለን ላላ እናጽናው ጠበብ እናስፋው በማለት እንጨነቃለን እናዝናለን እንዲሁም ከመከራው ጽናት የተነሣ ሞትን በተለየነው እያልን እንማረራለን ። ያንን ዓለም (መንግሥት ሰማይን) ከወረስን በኋላ ግን ለዚህ ነው እንዴ የምንልበት አይደለም እንደውም ምነው በመከራ ላይ መከራን በጨመርንበት ያሰኛል እንጂ ።

እንግዲህ ክርስቲያኖች እንዲህ ዓይነቱን ሰማያዊ ክብር ተስፋ እናደርጋለን እንጂ አሁን የምንማረርበትን ዓይነት ምድራዊ ኑሮ ተስፋ አናደርግም ።

— ዕብ ፲፩ ፥ ፲፮ «...አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና ።»

ስለ ቀደሙት የእስራኤል ልጆች አንስቶ ጳውሎስ ሲናገር ወደ ወጡበትስ ሀገር ወደባቢሎን መመለስ ሽተው ቢኾን ኖሮ ይመለሱ ዘንድ በተቻላቸው ነበር ማን ከለከላቸው ዳሩ ግን በልዕልና ያለች የበለጠች ሀገር መንግሥት ሰማይን ተስፋ ያደረጉ እንደነበረ ታወቀ ተረዳ ስለዚህ እግዚአብሔር የኹሉ አምላክ ፥ ሲኾን አምላከ ሠለስቱ መባልን አያፍርም ተስፋ ያደረጓት ሀገር መንግሥት ሰማይን አዘጋጅቶላቸዋልና በማለት የቀደሙት አበው እነ አብርሃም እነ ይስሐቅ ሁሉ ተስፋ የሚ



ያደርጉት ሰማያዊትዋን መንግሥት እንደሆነና የሚወርሱትም እርሷን መሆንዋን ጳውሎስ ተናገረ ምድራዊ ኑሮንስ ማንም አይሻም ።

— ቈላስያስ ፫ ፥ ፩ ቅዱስ ጳውሎስ ለቈላስያስ ሰዎች በላከው ክታቡ ስለ ተስፋይቱ መንግሥት ሲያሳስባቸው ከክርስቶስ ጋር ተዋሕዶ ለመኖር ትንሣኤ ልቡና ከተነሣችሁ (በልባችሁ «ክርስቶስን በኩር አድርጋችሁ መነሳታችሁን ካመናችሁ) በአብ ዕሪና የሚኖር ክርስቶስ ካለበት ዘንድ ሰማያዊን ነገር ፈልጉ ምድራዊውን አይደለም» ። ባማለት ምድራዊ ህይወትን ምድራዊ ኑሮን ሳይሆን ሰማያዊ ክብርን መሻት እንዳለባቸው አሳስቧል ።

— ፪ኛ ጴጥ ፫ ፥ ፲—፲፫ «በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምጽ ያልፋሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል ምድርም በእርስዎም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ የእግዚአብሔር ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኮላችሁ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ ። የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይፈታል ። ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ እንጠብቃለን»

ት ን ታ ኔ ፥— ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ሰማይና ምድር ማለፍ ሲነግረን አስቀድሞ የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ በሥልጣን እግዚአብሔር ያልፋል ምድርም ታልፋለች ከምድር በላይ ያለው ም ሁሉ ያልፋል ሰማይን ማለቱ ነው «ጌታ ሰማይና ምድር ያልፋሉ» ያለውን ይዞ ነው ነገር ግን ሰማያት ያልፋሉ ሲል ይህን በግዙፍ የምናየውን ሰማይ ወይም ጠፈር ነው እንጂ ሰባቱ ሰማያትስ አያልፉም ሰባቱ ሰማያት የምንላቸውም መንበረ ጸባኦት ፥ ጽርሐ አርያም ፥ ሰማይ ውዱድ ፥ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ራማ ፥ ኤረር ፥ ኢዮር ናቸው ። እንዲሁም ገሃነመ እሳትም አያልፍም ።

ቅዱስ ጴጥሮስ ሰማይና ምድር የሚያልፉበት ፍጥረት ሁሉ የሚያልፍባት እግዚአብሔር የሚመጣበት ዕለተ ምጽአትን ተስፋ አድርጋችሁ ለምግባር ለትሩፋት ቸኩሉ ካለ በኋላ ይህ ሁሉ ካለፈ እኛስ እንደ ምን ሆነን እንኖራለን ትሉኝ እንደሆነ ሐዲሱን ሰማይ ሐዲሱን ምድር ወርሰን እንድንኖር ተስፋ እናደርጋለን ። ባለማለፍ ጸንታ የምትኖረውን ፤ በማለት ሁላችንም መንግሥተ ሰማይን ተስፋ እንድናደርግ



www.ethiopianorthodox.org

አሳስበን እንጂ ይህን ምድር ወርሰን እንድንኖር እንድንተጋ አልመከ
ረንም እዚህ ላይ መንግሥተ ሰማይን በሐዲስ ሰማይና ምድር መስሎ
ተናግሯታል ። ምድር የመባልዋን ምሥጢር ቀደም ብለን የገለጽነው
ሲሆን ሰማይ ያለበትን ምክንያት እንደሚከተለው እናትታለን ።

ሁላችንም እንደምናውቀው መንግሥተ ሰማይ የተዘጋጀችው
ይህቺ ምድር ከመፈጠርዋ አስቀድሞ ነው ። ሳጥናኤል ለመጀመሪያ
ጊዜ የተፈጠረበት በዚች ቦታ ነው ። ዳሩ ግን ጴጥሮስ ሐዲስ ሰማይ
አየሁ ሲል ዓይን ያላያት ጆሮ ያልሰማት ልቡና ያላስተዋላት ከመ
ታየት እንግዳ ስለሆነች ሲሆን እንዲሁም ጻድቃን ከብሌት ሥጋ ታድ
ሰው በተሐድሶ ተነሥተው የሚወርሷት ስለሆነ ነው ።

ሰማይ መባሉዋም ይህ የምናየው ሰማይ አልፎ እሷ የምትተካ
ስለሆነ እንዲሁም ሰማያውያን መላእክት የሚወርሷት ስለሆነና ሰማ
ያዊ ሥራ ሠርተው የሚወርሷት ስለሆነ ነው ።

— ዮሐንስ ራዕይ ፳፩ ፡ ፩ — ዮሐንስ በዚህ ራዕይ ላይ «ከዚህም
በኋላ ሐዲስ ሰማይ ሐዲስ ምድር አየሁ የቀድሞው ሰማይ አልፏልና
የቀደመችው ምድርም አልፋለችና እዚህ ላይ መንግሥተ ሰማይ ተሰ
ጠች ማለቱ ነው ። ሐዲስ ሰማይና ሐዲስ ምድር የመባልዋ ምሥጢር
ከላይ ተጠቅሷል ያንን ተመልከት ።

እንግዲህ የዚች ምድር ማለፍ የማይቀር መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ
በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ እያስረዳ አርዮሳውያን ግን «በምድር ላይ
ለዘላለም እንኖራለን የሚሉት ለምን ይሆን?» አወን ጳውሎስ እንዳ
ለው ሐሳባቸው ምድራዊ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሳይሆን የሰውን
ምኞት ተከትለው ለመሔድ ስለሚፈልጉ ነው ። ይህ ዓለም ጥንቱንም
ቢሆን የተፈጠረው ለኀልፈት ነው ። የሚያልፈውን ዓለም እንዲያ
ሳልፈው የማያልፈውን በመውረስ ጸንተን እንደ ምንኖር ቅዱስ ጳው
ሎስ በዕብራውያን ፲፪ ፡ ፳፰ ላይ ጠቅሶታል ።

አርዮሳውያን ማቴ ፮ ፡ ፲ «መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ
እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን የሚለውን በመጥቀስ የአምላክ
አገዛዝ በምድር ላይ እንደምትሆን ያስረዳናል ይላሉ ። ዳሩ ግን ጌታ
መንግሥትህ ትምጣ ብላችሁ ጸልዩ ማለቱ እነርሱ እንደሚሉት ሳይ
ሆን እንደሚከተለው የሚተረጐም ነው ።



መንግሥተ ሰማይን ትምጻልን ስንል ከወዲያ ያለች ከወዲህ የሌ
ለች ሁና ከወዲያ ወዲህ የምትመጣ ከወዲህ ያለች ከወዲያ የሌለች ሁና
ከወዲያ ወዲህ የምትሄድ ሁና አይደለም ። ትገለጽልን በሉኝ
ሲል ነው ። አንድም ልጅነት ትሰጠን በሉኝ ሲል ነው ። (ልጆችህ
እንሆን ዘንድ ፈቃድህ ይሁን በሉኝ ሲል) እንዲሁም ሰማያውያን መላ
እክት በሰማይ ሊያመሰግኑህ ፈቃድህ እንደሆነ እኛም በምድር ላይ
የምንኖር ባሮችህ እናመሰግንህ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን በሉኝ አንድም
ኋላ ሙተን ተነሥተን ልናመሰግንህ ፈቃድህ እንደሆነ ዛሬም በሕይ
ወተ ሥጋ ሳለን እናመሰግንህ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን በሉኝ ሲል ነው
እንጂ በምድር ላይ አገዛዝህ ይሁን በሉኝ (የምድርን አገዛዝ ተስፋ
አድርጉ ማለቱ አይደለም ።

ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን መንግሥት መቼ ትመጣለች ወይም
መቼ ትሰጣለች ብለው በጠየቁት ጊዜ ጌታ የሰጣቸው መልስ «የእግዚ
አብሔር መንግሥት በመጠባበቅ የምትገኝ አይደለችም ደግሞም ኮወ
ዲህ አለች ከወዲያ የለችም ከወዲያ አለች ከወዲህ የለችም አትባልም
የእግዚአብሔር መንግሥት እነሆ በመካከላችሁ ነች ማለት እኔን በማ
መን የምትገኝ ነች እኔን ካላመናችሁ ፈጽሞ አታገኙዋትም የመንግሥተ
ሰማይ ባለቤት (ሰ ጪ.) እኔ ነኝ እኔን እመኑ ብሎአቸዋል ።
ሉቃ. ወን. ፲፯ ፡ ፳፩ ።

እንግዲህ ጌታ በተለያዩ ምሳሌዎች የመሰላት መንግሥተ ሰማይ
ከሰባቱ ሰማያት አንድዋ ስትሆን ኃይማኖትን የጠበቁ ምግባር ትሩ
ፋት የሠሩ ሰዎች ሁሉ የሚወርሷት ነች ። ይህንን ያህል ሰው ብቻ
የሚገባባት ነች አትባልም በወንጌል የተጠቀሰውን የመግቢያ መስፈ
ርት ያሟሉ ሁሉ ያለምንም አድልዎ የሚገቡባት ነች ። ከፍርድ ቀን
በኋላ ይህች ምድር ስለማትኖር የሚኖርባት ሰው አይኖርም ። «ከዚህ
በኋላ ብሩህ ታላቅ መንበርን አየሁ በመንበሩ ላይ ተቀምጦ ካለው
ከእሱ በፊት መገለጽ የተነሣ ሰማይና ምድር ሸሹ (አለፉ) ስፍራም
አልተገኘላቸውም (ቦታ ቦታነት አላገኙም «ራዕይ ፳ ፡ ፲፩ በማለት
ለዘላለም እንደሚጠፉ ተገልጹአል ።

ሰማይና ምድር ያልፋል ካላችሁ እግዚአብሔር ሰማይ ዙፋኔ
ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት ብሏል ታዲያ ሰማይና ምድር ካለፉ
እግዚአብሔር የት ይሆናል? የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ ለመሆኑ እግዚአ
ብሔር ሰማይና ምድርን ከመፍጠሩ አስቀድሞ በየት ነበር? በሚል
ጥያቄ ለጥያቄአቸው መልስ እንሰጣለን ። እግዚአብሔርን ሰማይና
ምድር አይወስኑትምና ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አምስት

## መጪው አውሬ

የዓለም ገጽታ ባልተጠበቀ ሁኔታ እየተለወጠ ነው ። የነበረው እንዳልነበር እየሆነ ዘመኑ ከሽማኔ መወርወሪያ ይልቅ እየፈጠነ ፤ ሁሉም ነገር በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ፍጻሜ ዘመን እያዘገመ ፥ ክስተቶች የእልቀተ ዓለምን ዋዜማ እያበሠሩ ነው ወደ ዳግም ምጽአት መቃረባችንን ጸሐፍት በሾለ ብዕራቸው እየከተቡ ነው የሁሉም ትኩረት ወደ ታላቁ መጽሐፍ እየተሳበ ነው ። በአንድ ወቅት ተንቆና ተነውሮ ጡረታ ወጥቶ የነበረው ይህ መጽሐፍ ዛሬ ግን ወርቅነቱን አስመስክሯል በውስጡም ወርቃማ ቃላት መያዙኑ አሳውቋል ።

ዓለሙ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት መስታወትነት መጭውን ጊዜ እየጠበቀ ነው ። በመጽሐፍ ቅዱስ የሠፈሩት ትንቢቶች አንድ በአንድ ወቅታቸውን እየጠበቁ በመፈጸም ላይ ናቸው ቀሪውም ጊዜውን ጠብቆ መፈፀሙ አይቀሬ ነው ትውልዱም በመጽሐፍ ቅዱስ የተዘገቡት ንግርቶች ያለ አንዳች መዛነፍ ተግባራዊ መሆናቸውን እያስተዋለ ስለሆነ ለወደፊቱ የሚሆኑትንም በእምነት የሚጠባበቃቸው ይመስላል ።

በዚህ ዘመን ከሚከሰቱት ክስተቶች መካከል ነቢያተ ሐሰት አንደኞቹ መሆናቸው ፤ ከማንኛችንም መዘንጋት የለበትም የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት በራሳቸው አርዳድና አተረጓጎም የሚተረጉሙ አንዳንድ ነቢያተ ሐሰት መስተዋላቸው የመጨረሻውን ጊዜ መቃረብ የሚጠቁሙ ምልክቶች ናቸው ። እነዚህ ክፍሎች «ግርግር ለሌባ ያመቻል» እንደሚባለው ሁሉ በመጽሐፍ የሠፈሩት ምልክቶች ጊዜያቸውን ጠብቀው መፈጸማቸውን ምክንያት በማድረግ የራሳቸውን አስተሳሰብ በማንጸባረቅ ሲላቸው መጪው ጊዜ ብሩህ ተስፋ እንዳለው ሳይላቸው ደግሞ መጭውን ጊዜ በጽልመት መጋረጃ ጋርደው ተስፋውን ሲያጨልሙበት ይታያሉ ።



ስለዚህ ቀን ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ እንዲህ ይላል «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለመሰብሰባችን በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደናገጡም እንለምናችኋለን ። ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመጽ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደርስምና እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ አምላክ ከተባለው ሁሉ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው» ፪ኛ ተሰሎ ፪ ፥ ፩—፭ ።

## እሱ ማነው ?

ከባሕር የሚወጣው የወደፊቱ አውሬ ማንነት በአሁኑ ጊዜ የዓለሙን ስሜት ወጥሮ ይዞታል ። የአውሬው ነገር ዓቢይ ርዕስ ሆንዋል ታዖሎስ ተብሎ የሚጠራው ዮሐንስ በራእዩ የተመለከተው ይህ የባሕር አውሬ በተለያዩ ሰዎች ዘንድ የተለያየ ትርጉም ተሰጥቶት ይታያል ።

አውሬው የዘመናችን የቴክኖሎጂ ውጤት የሆነው ኮምፒውተር ነው የሚለው አመለካከት ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው?

ሚስተር ዊሊያም ጋሪለን የተባሉ ሰው «የአውሬው መለያ ቁጥር ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት (666) ነው» የሚለውን በመያዝ ይህ ታላቅ የባሕር አውሬ የዘመናችን የቴክኖሎጂ ውጤት የሆነው ኮምፒውተር ነው ብለዋል እንደሳቸው አባባል 666 በማንኛውም ሥፍራ ያለ ምልክት (Universal Code) ነው ። ኮምፒውተር (Computer) የራሱ ቁጥር 666 ነው ብለዋል በዩኒቨርሳል ኮድ አስያየም ።

ቁጥር 6 የኮምፒውተር ልዩ ምልክት ሲሆን እንዲሁም በማንኛውም የዓለም አካባቢ የኮምፒውተር ቁጥር 6 ነው ። በኮዱ መሠረት የኮምፒውተሩ የላቲኑ የፊደል ቁጥር ድምር 666 መሆኑን ከሚከተለው የሒሳብ ስሌት ያስተውሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| A 6 | F 36 | K 66 | P 96 | U 126 | Z156 |
| B 12 | G 42 | L 72 | Q 102 | V 132 | |
| C 18 | H 48 | M 78 | R 108 | W 138 | |
| D 24 | I 54 | N 84 | S 114 | X 144 | |
| E 30 | J 60 | O 90 | T 120 | Y 150 | |

ኮምፒወተር የሚለው ቃል በላቲኑ ስምንት ፊደላት አሉት ። Computer እያንዳንዱ ፊደል የያዘውን ቁጥር አውጥተህ ደምር ።

| | |
|---|---|
| C | 18 |
| O | 90 |
| M | 78 |
| P | 96 |
| U | 126 |
| T | 120 |
| E | 30 |
| R | 108 |
| ድምር | 666 |

ይህንን አቀማመር መሠረት በማድረግ አውሬው ኮምፒውተር ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል የ«ኮምፒውተር» ሞክሼ ስሙ «አውሬው» ሲሆን በቤልጅግ የሚገኘው «የትልቁ ኮምፒውተር» የሞክሼ ስሙ ትልቁ አውሬ» ነው ይላሉ ።

ዶ/ር ጃክቫን እንዳጋለጡት ይህ ቁጥር 666 የሆነው የመላውን ዓለም ሕዝብ የሚቆጣጠረው በዚህ ታላቅ ኮምፒውተር ነው ይህም ኮምፒውተር ብራሲልስ ላይ ከተተከለው ከኤል ደብልዩ ኤፍ ቲ የዓለም ባንክ ኮምፒውተር ጋር ተያይዟል (ተገናኝቷል) ማዕከላዊው ኮምፒውተር የሚገኘው በላክስምበርግ ነው ።

— ዲያብሎስና ሲኦል ወይም በላቲኑ ፊደል (Devil and Sheol)

— ሕዝብና ኃጢአት ወይም በላቲኑ (People and Sin)

— ዲያብሎስና ደራጎን (Devil and Dragon)



ከላይ በተዘረዘረው መሠረት በጥንቃቄ ብናሰለቸው 666 የሚለውን ለአውሬው የተሰጠውን ምልክት ያስገኛሉ ።

ዳሩ ግን ዮሐንስ ራዕይ ም. ፲፫ ላይ የተጠቀሰው የባሕር አውሬ በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ኮምፒውተር አይደለም ሊሆንም አይችልም ምክንያቱም ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በላከው በሁለተኛ ክታቡ ላይ «የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ» በማለት ሰብዓዊ ፍጡር መሆኑን ገልጾታልና እንዲሁም እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ ... ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው» በማለት ከሰዎች ወገን መሆኑን ሰው የሚያዘው የሚሠራው የሰው የሥራ ውጤት እንዳልሆነ በግልጽ አስቀምጦታል ።

666 የሚለው ቁጥር የኮምፒውተር ድምር ውጤት ሊሆን እንዴት ቻለ?

የዚህን መልስ ኮምፒውተርን የሰሩትና ስሙን ያወጡትን ሰዎች ያውቁት ይሆናል ምናልባት አውሬው ዓለምን በኮምፒውተር የሚቆጣጠር ሊሆን ስለሚችል ዋናው ዓለምን የሚቆጣጠርበት መሣሪያ ኮምፒውተር እንደሚሆን ለመጠቆም ይሆናል ወይም ደግሞ በዘሁ ሰው መላው ዓለም ኮምፒውተራይዝድ ሊሆን ይችላል ያን ለመጠቆም ይሆናል ።

ነገር ግን 666 የሚለው የአውሬ ምልክት ትክክለኛ ትርጉም በኋላ ይገለጻል ። አሁን ዮሐንስ ወዳየው ራእይ ትንታኔ እንግባ ።

## ራዕዩ የታየበት ቦታ

ከጥንተ መሠረቱ ስንነሳ እንዲህ የሚተረክ ትረካ አለ ከሰባቱ ዮናናውያን (ግሪካውያን) ታላቁ ኤፌሶን ይባል ነበር ። ይህ ኤፌሶን የተባለው ሰው ቢፓልክና በደምግባት በጣም የተዋበች ሳር ቅጠሉ ሳይቀር የሚያረግ ድላት አንዲት ሴት ይወልዳል ስምዋንም አርጤምስ ይላታል ።

ውበትን ከደም ግባት ጋር አጣምራ የያዘችው አርጤምስ ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ የብዙ ወንዶችን ልብ ትስብ ጀመር በፍቅርዋ ፍላጻ የተወጉ የተለያዩ ታላላቅ ሰዎች ለኑሮ ጓደኝነት ይጠይቋታል ።



www.ethiopianorthodox.org

አርጤምስ ግን ሙንፈስ ትእቢት አድሮባት ነበርና ቆንጆውን ብታምር እውቀት የለህም ትለዋለች ጠቢባን መጥተው ሲጠይቋት ደግሞ ጥበብ ቢኖርህ እኔን አንደላቆ የሚያኖር ሀብት ንብረት የለህም በሚል ፌዝ ትሸኛዋለች በሐብታቸው የሚሙኩ ለእኛስ በጅ ትላለች ብለው ሲመጡ ሐብት ቢኖራችሁ ሙልክ የላችሁም በማለት በሚመጡት ላይ እያፌዘች ትኖር ነበር ።

አንድ ቀን ቆርኔሌዎስ የሚባል አንድ ሥራየኛ ላግባሽ አላት ለብዙ ባለጸጋ ለብዙ ጥበበኛ ለብዙ ሙልከ ሙልካም ያልሆንለት ለአንተ እንደምን ይሆንልሀል አለችው እርሱም ሲሙልስላት ሙቹስ አንቺ የምትሽው ሙከበሩን አይደለም ን እንድትከበሪ ላደርግ እችላለሁ ይላታል ። እርስዋም እኔን እንደ አምላክ እንድሙለክ ካደረግክ ምን ቸገረኝ ፈቃደኛ እሆናለሁ አለችው ።

እርሱም «ለአርጤምስ የማይሰግድ ሰው ቢኖር ቤቱ ይሙዘበራል ሀብቱ ይወረሳል» ብሎ በወረቀት በሙጻፍ አጋንንትን በምስሐቡ ጠርቶ ሰው ሰብስቤ በማስተምርበት ጊዜ ከወደ ላይ ድምፅ እያሰማችሁ አምጥታችሁ ጣሉልኝ አላቸው ሕዝቡን ሰብስቦ በሚያስተምርበት ጊዜ ድምፅ እያሰሙ ሙጡ እስቲ ዝም በሉ ከወደላይ የምሰማው ድምፅ አለ ብሎ ተነሥቶ ቆሞ አጋንንቱም እንደ ተባሉት ያቺን ወረቀት ጣሉለት አንሥቶ አንቦ ለሙ ቤቴ ለአርጤምስ አምላክነቷን የሚሙሰክር ከወደላይ ከወረደላት ለሙ ቤቴ ለአርጤምስ ሰገድሁ ብሎ ሰግዷል ሌሎችም እሱን አብነት አድርገው ሰግደውላታል ።

በዚህ የተነሣ አርጤምስ ተደስታ ቆርኔሌዎስን ታገባለች ከእርሷም ዜውስን ወልዷል ። ዜውስንም የአምላክ ልጅ አምላክ ብለው ሰግደውለታል ከሞቱም በኋላ እንደ ተነሡ እንዳረጉ አድርጎ ያሳያቸዋል ሥዕላቸውን ሥለው ምስላቸውን ሙስለው እነርሱን እያመለኩ የሚኖሩ ሁነዋል ።

ሐዋርያት «ወንጌልን በዓለም ዙራችሁ ስበኩ» በተባሉት አምላካዊ ትዕዛዝ ሙሠረት ይህን ዓለም ዕጣ በዕጣ ተካፍለው ለማስተማር በሚወጡበት ጊዜ ምድረ ፅርእ (ግሪክ) ለቅዱስ ዮሐንስ ደርሳዋለች ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስም ዮሐንስን እየሙራ ወስዶ ከዚያ ያደረሰውና ይሙለሳል ቀደም ብለን በገለጽነው ሙሠረት ግሪክ በተለያዩ የጣኦት አምልኮት የተያዘች ነበር ዮሐንስም ከጣኦት አምልኮ እንዲወጡ



ትምህርቱን ጀመር እንዲህ ሲል «ዜውስ አርጤምስ ቢሏችሁ ምን ቁም ነገር ናቸው ጥንቱንም የዕለተ ዐርብ ፍጥረታት ናቸው ዛሬም ሥጋቸው በመቃብር ነፍሳቸው በገሃነም ተይዟል ፃ(ፀሐይ በጨረቃም ያመልኩ ስለነበረ «ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ቢሏቸው ቀድሞም የዕለተ ረቡዕ ፍጥረታት ናቸው ኋላም ኃላፍያን ናቸው ሰማዩን ምድሩን የብሱን ባሕሩን የፈጠረ አምላክ አለ ብሎ ከዚህ ሊያይዞ ጌታ ከፅንስ ጀምሮ ያደረገውን ተአምራት ያስተማረውን ትምህርት የሠራውን ትሩፋት ቢነግራቸው ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ተመልሰው በክርስቶስ አሙኑ ተጠሙቁ (53)

ከ፶፩—፷፰ ዓ.ም. ባለው ጊዜ የሮማ ቄሣር የነበረው የኔሮን ቄሣር ወንድም ድምጥያኖስ ነበር ። ይህ ቄሣር ገና በሕይወት ሳለ ምስሉን አሠርቶ እንዲሰገድለት ሲል የታናሽ እስያ ክፍል ወደምትሆን ወደ ኤፌሶን ላከው ያን ጊዜ ዮሐንስ ወንጌላዊ በሐዋርያነት ተግባሩ ላይ እንዳለ ይህን ምስል አይቶ በጣም ተቃወመ የኤፌሶን ክርስቲያኖችም ከዮሐንስ ጋር ሁነው የድምጥያኖስን የግብዝነት ሥራ ተቃወሙ በዚህ ጊዜ ዮሐንስ ተይዞ ወደ ሮም እንዲወሰድና የተቃወመበትን ፍርድ እንዲቀበል የሮማ ምክር ቤት ወሰነ ያን ጊዜ የዘጠና ዓመት አረጋዊ ነበር ፍርዱን ለመቀበል ወደ ሮማ ሄደ እዚያም በደረሰ ጊዜ የሮም ዳኞች በደሴተ ፍጥም እንዲጋዝ ወሰኑበት ዮሐንስም በሮማ ቄሣሮች ያመጹ ሁሉ ወደሚታሰሩበት ወደደሴተ ፍጥም ተወሰደ (54)

በደሴተ ፍጥምበግዞት ላይ ሳለ መንፈስ ቅዱስ የወደፊቱን የዓለም ጉዞ ምን እንደሚሙስል በራእይ አሳይቶታል ራእይ ፩ ፥ ፱ ።

<u>የወደፊቱ ሐሳዊ ሙሲሕ ዮሐንስ ካየው ራእይ አንዱና ዓቢይ ነው</u>

<u>ዮሐንስ ራእይ ሙ፲፫ ከቁ ፩—፲፰ (ከነማብራሪያው)</u>

«አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ» አለ

---

(53) መቅድመ ራእየ ዮሐንስ ንንድምታው
(54) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 36



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ከባሕር ሲወጣ አየሁት ያለው አውሬ በቁሙ የዱር አውሬ አይደለም ምሳሌያዊ አነጋገር ነው ። አውሬ የተባለው ሐሣዌ መሢሕ ነው እኔ ክርስቶስ ነኝ ብሎ የሚመጣው የአመጽ ሰው ባሕር የዓለም ምሳሌ ነው ። በባሕር ውስጥ የተለያዩ የውሃ አውሬዎች ይገኛሉ ጉማሬ ፣ ዘንዶ ፣ አሣነባሪ የመሣሰሉት እንዲሁም በምድር ላይ በተፈጥሩአቸው ሰብአዊ ሆነው በግብራቸው አውሬ የሆኑ ሰዎች ይኖሩበታል እንዲሁም በባሕር ውስጥ ደጋግ ነፍሳት እንዳሉ ሁሉ በምድርም ላይ ደጋግ ሰዎችም አሉ ታዲያ ባሕር ከማለት መሬት ማለት አይቀለውም ባሕርን ምን አስመረጠው ቢሉ ባሕር የረጋ አይደለም እንደዚሁም ሁሉ ሐሣዊ መሢሕ ከባሕር ወጣ ማለቱ ግዛቱ መንግሥቱ (ስልጣኑ) ገና አለመደላደሉን ለሚረጋገጥ ነው በብዙ ጦርነትና ምትሐታዊ ተአምራት ነውና ዓለምን የሚያንበረክከው ።

## ትውልዱ

የሐሣዊ መሢሕን ትውልድ ከነገደ ዳንና ከነገደ ኤሳው መሆኑን ይናገሩለታል ከዳንና ከኤሳው ወገን ነው የሚወለደው የሚለው ግምት ኤሳው በኩርናውን ለምሥር ወጥ ሲል የለወጠና ያልተባረከ ስለሆነ ይሆናል ዳን ደግሞ ያዕቆብ ከሒጋዊት ሚስቱ ከራሔል ውጭ ከአገልጋዩ ከባላ የወለደው ስለሆነ ከሕግ ውጭ የተወለደ በመሆኑ ይሆናል ዘፍ ፵፱ ፡ ፲፮—፳ ።

የሐሣዊ መሢሕ አባቱ ከነገደ ኤሳው እናቱ ከነገደ ዳን ናቸው ። የሐሰት ነቢያት እናቱን በድንግልና ጸንሰሽ በድንግልና ትወልጃለሽ ከአንቺም የሚወለደው መሢሕ ነው ስለሚሉዋት ከመቃብር አረሚቁማ ስትጸልይ አንድ ዐይና ጐልማሳ ከወደ ምሥራቅ መጥቶ ከክብር (ከድንግልና) ያሳንሳታል ዳሩግን የትዕቢት ምንጭዋ የሆነው ዲያብሎስ ትዕቢት አሳድሮባት ከድንግልና መውጣትዋን እያወቀች በድንግልና ፀነስሁ በድንግልና ወለድሁ ትላለች ። ልጅዋም ከተወለደ በኋላ በዲያብሎስ የትዕቢት መንፈስ እየተመራ ያድግና አምላክ ነኝ ማለት ይጀምራል ብዙ የጦር ሰዎችንም ያሰባስባል ።

## ገጽታው ምን ይመስላል ?

ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ እንደተመለከተው አካሉ ቆቅሻም ነው አንድ ዐይኑ የሞተች ናት (የፈሰሰች) ሌላኛው ዐይኑ ደግሞ ደም



የሰረበው ፈጣጣ ነው ታሕታይ ከንፈሩ ትልቅ ነው ለበናም (ለንቦጫም) ነው ። አፉ የአንበሳን አፍ ይመስላል ተብሏል ። አውራ ጣቱ ጠማማ ነው እግሩ ወላፈ ነው የድብን እግር ይመስላል ። ራእይ ፲፫ ፡ ፪ ።

## ዐሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች የተባሉት ምንድናቸው ?

ቀንድ የሚያገለግለው ጠላትን ለመውጋት ነው ። የሚበቅለውም ከጊዜ በኋላ ነው እንዲሁም ይህ መሳቲ ከጊዜ በኋላ መንግሥቱን ሲያደላድል በሥሩ የሚመለምላቸው እንደ ቀንድ የእርሱን ተቃዋሚዎች እየወጉ የሚጥሉ አሥር ተወራጆች ይሾማል እነዚህም የእርሱ ዋና አጫፋሪዎች ናቸው ። ምናልባትም በአሥር ታላላቅ የእርሱን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ በሚተባበሩ አገሮች ላይ የሚሾሙ ይሆናሉ ።

ሰባት ራሶች የተባሉት ሰባት ሀገሮች ናቸው እነዚህ ሀገሮች የሐሣዊ መሢሕ ዋና መናሐርያ እንደሚሆኑ ይገመታል እነርሱም ፋርስ (ኢራን) ባቢሎን (ኢራቅ) ፅርዕ (ግሪክ)ሜዶን ፤ ግብፅ ፤ ሮም ፤ ኢየሩሳሌም ናቸው ዳን ፯ ፡ ፯—፳ ።

ሌላ አመለካከትም አለ ሰባት ራሶች የተባሉት በእዚህ ሐሣዊ መሢሕ ዘመን የሚፈጸሙ ሰባት ዋና ዋና ኃጢአቶች ናቸው እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

### <u>፩ኛ. ኃጢአተ አዳም</u>

እግዚአብሔር አዳምን በመልኩና በአርአያው እንደፈጠረውና አክብሮ አግኖ በኤደን ገነት እንዳስቀመጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ተከትቦ የምናገኘው ነው ዘፍ. ፩—፳፮ ፪ ፡ ፯—፲፯

አዳም ግን እግዚአብሔር ባስቀመጠው ቦታ ጸንቶ አልቆየም የእግዚአብሔርን አምላክነት ለሙንጠቅ እጅግ ቋመጠ ስለሆነም በእርሱ አስተሳሰብ በምክረ ሰይጣን ወደ አምላክነት ወደምታደርሰው እጸ በለስ ጉዞ አደረገ ከዚህ ቀደም በዓይኑ ዘንድ ክብርና ሞገስ ያልሰጣት ፍሬ ዛሬ ግን ልዩ ክብርና ሞገስ አግኝታ በእጁ ተቀጥፋ ለመበላት በቃች እንደተመኘው አምላክ አልሆነም እንደውም እራቁቱን ቀረ



www.ethiopianorthodox.org

እንጂ የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንደሚለው ተረት ይህ የአዳም በደል በአዳም ብቻ ላይ ሳይሆን በልጅ ልጆቹ ላይ ሳይቀር ተዛምቶ ሁሉም የሞት ባሪያ ሆኖ ግዛቱን በሲኦል ለ፭ሺ፭፻ ዘመን ያህል አድርጓል ።

ይህ የአዳም ኃጢአት (አምላክነቱን መሻት) በዚህ በሐሣዊ መሢሕ ዘመን ይደገማል አምላክ ነኝ ይላልና ለዚህም አሁን ባለንበት ዘመን በዓለም እየተከሰተ ያለው ክስተት ዓይነተኛ ማረጋገጫ ይሆናል ብዙ ሐሰተኞች ክርቶሳውያን ከየአህጉራቱ ብቅብቅ እያሉ ነውና እነዚህ ሁሉ አውሬው ባይሆኑም ዳሩ ግን የአውሬው መንገድ ጠራጊዎች መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል ።

ዋናው መሳቲ ግን በቀድሞ ዘመን የነገሱት ነገሥታት እነ ናቡከደ ናጾር እነ ዳርዮስ የነገሡት በእርሱ አንጋሽነት እንደሆነና ሰማይን ከነ ግሱ ምድርን ከነልብሱ የፈጠረ እርሱ መሆኑን ከእርሱ ሌላ ፈጣሪ አምላክ እንደሌለ በድፍረት ይናገራል ።

## ፪ኛ. ቅትለት አቤል

የእናት ሆድ ዥጉርጉር ነውና አቤልና ቃየል ከአንድ ሔዋን ማህፀን የወጡ ቢሆኑም ዳሩ ግን አቤል የዋህ ቃየል ደግሞ መሠሪ ነበር ። እግዚአብሔር በባሕርይው ንጹህ ነውና ንጹህ ነገር ይሻል ብሎ አቤል በንጹህ ልቡና ለእግዚአብሔር ያቀረበው መስዋእት ተቀባይ ነትን ስላገኘ በንጹህ ልቡና ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን ንጹህ መስዋእት ባለማዘጋጀቱ ምሥዋእቱ ቅድመ እግዚአብሔር ያልደረሰ ለት ቃይል በወንድሙ ቀንቶ ገድሎታል ዘፍ ፬ ፥ ፩—፰ ። እንዲህ ዓይነቱ ቃየላዊ ድርጊት በዚህ በሐሣዊ መሢሕ ዘመን በዓለም ላይ በስፋት ይፈጸማል ወንድም ወንድሙን ያጠፋል እህት እህትዋን ያለ ርህራሄ ትገድላለች እንኳን በጥቅም ለተዛመደው ቀርቶ በሥጋ ለተዛመደው የማይራራበት የብላ ተባላ ዘመን ይሆናል ።

## ፫ኛ. ጥቅመ ሰናዖር

በጥንትዋ ባቢሎን ሰዎች ከጥፋት ውሃ በኋላ በምድር ላይ መብዛት በጀመሩበት ጊዜ ታላቅ የኃጢአት ግንብ ለስማቸው ማስጠሪያ መገንባት እንደጀመሩና ሐሳባቸው ከግብ ሳይደርስ በሰናዖር ምድር ላይ



የተጀመረው ታላቁ የባቢሎን ግንብ በውጥን መቅረቱ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸ ነው የአመጽ ሥራ ነውና ዘፍ ፲፩ ፥ ፩—፱ ።

እንደዚሁም ሁሉ በአውሬው ዘመን የሰው ልጆች ቴክኖሎጂ ከተጠበቀው በላይ ይመጥቃል ዓለም ኮምፒውተራይዝድ ትሆናለች ከመራቀቃቸው የተነሣ የእግዚአብሔርን መኖሪያ ሰማይን ለማሰስ የእግዚአብሔርንም አለመኖር ለማረጋገጥ ከፍተኛ ዘመቻ በሰማይ ላይ ያደርጋሉ ምናልባት ዛሬ ሳይንስ ያልደረሰባቸው ግኝቶች በዚያን ዘመን ይገኛሉ ። ሰው ሁሉ የቴክኖሎጂውን ውጤት እስከማድነቅና እስከ ማምለክም ይደርስበታል አውሬው ይህን ሁሉ የማድረግ ኃይልና ሥልጣን ያለው ነው በአውሬው ጐትጓችነት የቴክኖሎጂ ግንብ እስከ ሰማይ እስከ እግዚአብሔር መኖሪያ ሊገነቡ ማለትም በመንኰራኩር ወይም ከዚያም ለየት ባለ መሣሪያ በመጠቀም ለመጓዝ የሚከጅሉትና ሙከራውንም የሚያደርጉበት ዘመን እንደሚሆን ይገመታል ።

## ፬ኛ. ኃጢአተ ሰዶም

ሰዶም የተባለችው ሀገር በውስጥዋ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ትዕግስት ቻል በማለት በሚሠሩት አስጸያፊ ኃጢአት እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሎጥና ቤተሰቦቹን ከከተማዋ አስወጥቶ በውስጥዋ የሚኖሩትን ሰዎች ከሰማይ እሳትና ዲን አዝንቦ ጨርሱዋቸው ል ዘፍ. ፲፱—፩—፳፱ ።

የሰዶም ሕዝቦች ይፈጽሙ የነበረው ኃጢአት ግብረ ሰዶም ተብሎ ይጠራል ። ወንዶች ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ይቃጠሉ ነበር እንዲሁም ሴቶችም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕሪያቸው በማይገባው ለውጠዋል ።

ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት ተፈጽሞ የነበረ ኃጢአት ከተዳፈነበት ቦታ ተቀስቁሶ በመውጣት በሐሣዊ መሢሕ ዘመን በመላው ዓለም ላይ ይቀጣጠላል ። ግብረ ሰዶም (Homo Sexuality) በአሁኑ ጊዜ እንደ ሰደደ እሳት በዓለም ላይ እየተቀጣጠለ መሆኑ ከተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች እየተሰማ ነው በተለይ በሰለጠነው ዓለም መሰይጠን ሆኖ ግብረ ሰዶም (Homo Sexuality) ሕጋዊ እንዲሆን የሚጠይቁ ብዙ ሰላማዊ ሰልፎች ተደርገዋል ። በአሜሪካን ግብረ ሰዶም ፈጻሚዎችን



www.ethiopianorthodox.org

በሚመለከት በተደረገው ጥናታዊ መረጃ ሀሳባቸውን ከሰጡት ሰዎች መካከል ሰባ ስምንት በመቶው የሚሆኑት ግብረ ሰዶም ፈጻሚዎች ሙሉ መብት ሊሰጣቸው ይገባል ሲሉ የተቀሩት አሥራ ሰባት በመ ቶው ብቻ ጫና ሊደረግባቸው እንደሚገባ ተናግረዋል ።

ይህ የሚጠቁመው ዓለማችን ሙሉ በሙሉ ወደ ግብረ ሰዶም እየተዘፈቀች ሙሄድዋን ነው እንግዲህ በሐሳዊ መሢሕ ዘመን ግብረ ሰዶም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል ቅዱስ ጋብቻ ወንድና ሴት የሚያ ደርጉት ግንኙነት ይነወራል በተመሣሣይ ጾታ የሚደረገው ግንኙነት ይጸድቃል የዓለም ሕዝብ አብዛኛውን የግብረ ሰዶም ፈጻሚ ይሆናል አውሬው ይህን ያስደርጋል ኃይሉና ስልጣኑ ስለሚኖረው ።

## ፫ኛ. ኃጢአተ እሥራኤል

እሥራኤል በእግዚአብሔር ላይ የፈፀሙት ኃጢአት ብዙ ነው ከሁሉም ግን የከፋው የእስራኤልን ቅዱስ እግዚአብሔርን ትተው በአ ሕዛብ ጣኦታት ማምለካቸውና ለእነሱም መስገዳቸው ነው እንደዚ ሁም ሁሉ በሐሣዊ መሢሕ ዘመን ሰዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር አም ልኮት ወጥተው ወደተለያየ አምልኮት እንደሚገቡ የሚጠቁም ነው ።

በአሁን ጊዜ ያለው ሁኔታ ከላይ የተጠቀሰው ሁኔታ ሊደርሱ በደጅ ላይ መሆኑን የሚገልጽ ነው የተለያዩ እምነቶች በዓለም ላይ እየተከሰቱ ነው ሰዎች በግላጭ ሰይጣንን ማምለክ ደረጃ ላይ ደርሰ ዋል እንግዲህ ለወደፊቱ ደግሞ የአውሬው አምላኪዎች ይሆናሉ ማለት ነው ።

## ፬ኛ. ቅትለተ ዘካርያስ

የእግዚአብሔር ካህን የነበረው ዘካርያስ የተገደለው በተልእኮ እያለ በቤተ መቅደስ ውስጥ ነበር እርሱም ጥፋት ኖሮበት ሳይሆን በግፍ ነው ።

እንደዚህም ሁሉ አእይንተ እግዚአብሔር የተባሉ ካህናት በሐሣዊ መሢሕ ጊዜ ግልጋሎታቸው ለእውነተኛው የቀራንዮ በግ ስለሆነ መከራ ይደርስባቸዋል በግልጋሎት ላይ እንዳሉም ሊያስገድላቸው ይችላል ። ስለዚህ ይህ የሚያመለክተን የቅዱሣን ካህናትን መከራ



መቀበልና በሰማዕትነት ማለፍ ሲሆን እነ ሄኖክና ኤልያስ ሌሎችም ቅዱሳን በዚህ አውሬ እንደሚገደሉ የተጠቀሰ ነው ።

## ፭ኛ. ሞተ ወልደ እግዚአብሔር

ንጹህ ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም በደል ሳይኖርበት አይሁድ በቅንአት መንፈስ ተነሳ ስተው ለመከራ በኋላም ለመስቀል ሞት አሳልፈው እንደሰጡት በወ ንጌል ላይ የተጻፈ ነው በጌታ ላይ የተፈፀመው ግፍ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ሳይበድል የበደለ አስመስለው አይሁድ በግፍ ለሞት አብቅተው ታልና እንዲሁም ሁሉ በዚህ ሐሣዊ መሢሕ ዘመን በክርስቶስ ያመኑ ክርስቲያኖች ሳይበድሉ እንደበደሉ አድርጎ በውሸት በማቅረብ በግፍ ይገደላሉ ደማቸው እንደ ክረምት ጐርፍ ይጐርፋል ምድራዊ ዳኛ አይዳኛቸውም ደማቸው በምድራዊ ፈራጆች ዘንድ በከንቱ ፈሶ ይቀ ራል በላዕላዊ ፈራጅ ዘንድ ግን ይታያል እነዚያ ገፈኞቹም ለእሳት ይጠበቃሉ ።

«ከራሶቹም ለሞት እንደ፥ታረደ ሆኖ አንድን አየሁ ለሞት የሆነ ውም ቁስል ተፈወሰ» ይህ ትርጓሜ የሚመለከተው ቀደም ብለው ሰባቱ አርእስት ተብለው ከተጠሩት ከሰባቱ ሀገሮች አንድዋ የሆነችው ኢየ ሩሳሌምን ነው ።

## ምክንያቱ ምን ይሆን ?

አይሁድ ክርስቶስን በቅንአት አሳልፈው እንደሰጡት ጲላጦ የተባለው ሮማዊ መስፍን ስለተረዳ ክርስቶስን ነፃ ሊለቀው ሽቶ ነበ አይሁድ ግን ይህን ቢያደርግ የቄሣር ወዳጅ እንዳልሆነ ስለተናገ «እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ እናንተ ተጠንቀቁ» በማለ እጁን በውኃ ይታጠባል አይሁድ ግን እንደ አንድ ልብ መካሪ እን አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው «ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አ

ክርስቶስም ለቤዛ ዓለም መጥቷልና እርቃኑን በመስቀል እንደ ብራና ተወጠረ የመጣበት ዓላማ እንደተፈፀመ ያሳውቅ ዘ ተፈፀመ ብሎ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ሥጋውም ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አ በሦስተኛውም ቀን ሞትን ድል አድርጐ ተነሣ በአርባኛውም በምሥጋና አረገ ።



www.ethiopianorthodox.org

ዳሩ ግን አይሁድ በራሳቸው ላይ የተናገሩት መርገም ጊዜውን ጠብቆ ደረሰ «ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን» በእርግጥም ሆነ የልጅ ልጆቻቸው ሳይቀሩ የሰቆቃ ሕይወት አሳለፉ ይህም የመከራ ጊዜ የጀመረው ጌታ ከተወለደ ከ፸ ዓመት በኋላ ነው ።

የሮማውያን የግፍ ጡጫ እስራኤላውያንን አንገፈገፋቸው ስለ ዚህ ቤተ እስራኤል ከሮማውያን የባርነት መዳፍ ነፃ ለመውጣት እን ቅስቃሴ ጀመሩ ይኸውም የሆነው ከ፷፮—፸ ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር በዚህ እንቅስቃሴያቸው ግን እንዳሰቡት በድል አድራጊነት ተወ ጥተው የነፃነትን ሽማ ሊጎናጸፉ አልተቻለቸውም ይልቁንም ወደ ባሰ የግፍ ሕይወት መራቸው በጊዜው የነበረው ቄሳር ቬሰፖስያኖስ (አስፋስያኖስ) ኋላም ልጅ ቲቶ (ጥጦስ) በየተራ የእስራኤልን እንቅስ ቃሴ ለማክሸፍ በወሰዱት እርምጃ ከፍተኛ የእልቂት ዘመቻ በነገደ እስራኤል ላይ ታወጀ ትልቁ የአይሁድ ቤተ መቅደስ ሁ ሉ እስከመፍ ረስና እስከ መቃጠል ደረሰ በተለይ እስራኤል መሸገውበት በነበረው ማሳዳ ላይ የተደረገው ዕልቂት እጅግ ከባድና አሰቃቂም መሆኑ ይነ ገራል እስራኤል በዚህ ስፍራ ባደረጉት መራራ ጦርነት ላይ በጠላቶቻ ቸው እጅ ከመውደቅ ይልቅ ራሳቸውን በራሳቸው መግደልን ስለመረጡ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ልጆችና ሚስቱን ከገደለ በኋላ ወንድሞቹን ደግሞ የሚገድል ተመርጦ ዘጠኙን ከገደለ በኋላ በራሱ ጐራዴ ራሱን ይገድላል በዚህ ዓይነት አሚሚት እስራኤል እርስ በርሳቸው ከተላ ለቁ በኋላ በዋሻ ውስጥ ተደብቀው የነበሩ ሁለት አሮጊቶችና አምስት ሕጻናት እስራኤላውያን ብቻ በሕይወት ተገኝተው በጠላቶቻቸው እጅ ወድቀዋል ።

በተለያዩ ዘመናት ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ያደረጉት ትግል ሁሉ ስኬታማ ሊሆን ባለመቻሉ በየጊዜው የመከራ ስልቻ መሸከም እድላ ቸው ሆነ ከብዙ መራራ ትግል በኋላ ግን እግዚአብሔር የወሰነው ጊዜ ሲደርስ በቃት አልቆላታል ከእንግዲህ እስራኤላ የምትባል አገር በገጸ ምድር ልትኖር አትችልም ተብሎ በብዙዎች ዘንድ የተደመደ መላት እስራኤል ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. ላይ ዓለምን ባስደነቀ ሁኔታ ሉዓላዊት መንግሥት መሆንዋንና ነፃ መንግሥት መመሥረትዋን ለመላው ዓለም ይፋ አደረገች በዚህ ጊዜ ያልተደነቀና ያላተገረመ ቢኖር የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢታዊ ቃል በፍጹም ልቡ አምኖ የተቀበለ ብቻ ነበር ።



እንግዲህ ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ምዕ፳፬ ቁ፴፪ ላይ «ነገሩን በቦለስ ዕወቁ በለስ ቅጠሉ የለመለመ ዓዶቅ ያወጣ እንደሆነ መከራ (ምጽአት) እንደደረሰ ዕወቁ» ያለው ለዳግም ምጽአት ዋዜማ እንደሆነ ተናግሯል ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት በለስ የቤተ እስራኤል ምሳሌ መሆ ንዋን ይናገራሉ ። እንግዲህ በለስ ቅጠሉ ሲለመልም ግንድ ሲያወጣ ያን ጊዜ በጋ መድረሱን ዕወቁ ሲል ከክርስቶስ ላደት ከ፸ ዓመት በኋላ የፈራረሳቸውና በመላው ዓለም ላይ እንደ አፈር የተበታተነችው እስራ ኤል ከየተበታተኑበት ተመልሰው በሚሰባሰቡበት ጊዜና የራሳቸውን ሉዓላዊ መንግሥት በሚመሠርቱ ጊዜ ያን ጊዜ የወልደ እጓለ እመሕያው የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት መቃረቡን ልብ በሉ ባለው መሠ ረት ዛሬ እስራኤል ሉዓላዊት መንግሥት ከሆነች ፵፭ ዓመት ሆኑዋ ታል ።

እንግዲህ አብቅቶላታል አክትሞላታል ስትባል የነበረችው ይህቺ አገር ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሁኔታ የራስዋን መንግሥት እንደ መሠ ረተች ሁሉ ለወደፊቱ ደግሞ ከባሕሩ ውስጥ ይወጣል ተብሎ በተነገረ ለት አውሬ መሪነት ዓለምን የምትመራበትን በትረ ሥልጣን እንደ ምትጨብጥ ይገመታል ።

## ምድር ሁሉ አውሬውን ይከተላል !

መላው የዓለም ሕዝብ ይህ በአውሬ የተመሰለው ሐሣዊ መሢሕ በሚያደርገው ምትሐታዊ ተአምር ይሳባል ይደነቃል አውሬው በም ትሐታዊ ተአምራቱ ሕዝቡን ሁሉ ያስገርም ዘንድ ሥልጣን ለሰጠው ለዘንዶ ይሰግዱለታል ይገዙለታል አውሬውን ማን ይመስለዋል? ማን ይስተካከለዋል? ብቸኛ ገናና አምላክ ነው ብለው ያመልኩታል ።

## ዘንዶ የተባለው ማን ነው?

በዮሐንስ ራእይ በም. ፲፪ በቍ. ፫ ላይ «ታላቅ ቀይ ዘንዶ» በማለት ስለ ዘንዶው ማንነት ይናገራል ይኸ ዘንዶ አባታችን አዳምንና እናታችንን ሔዋንን ያሳተ ጥንተ ጠላት ዲያቢሎስ ነው ዘፍ. ፫.፩—፳

ታላቅ መባሉ የቀድሞ ተፈጥሮውን (ክብሩን) ለመግለጽ ነው የመላእክት ሁሉ አለቃ ነበርና ።



www.ethiopianorthodox.org

ቀይ ያለበት ምክንያት ተፈጥሮው እንደሌሎቹ ብርሃናውያን መላእክት ሁሉ ከእሳት ነውና ዕብ. ፩ ፥ ፯ ።

አውሬው ተሳዳቢ ነው ፤

ጽኑ ጽኑ ስድብ ይናገር ዘንድ ከዘንዶው (ከዲያብሎስ) ተልኩዋልና አፉን ይከፍታል እግዚአብሔርን ሊሳደብ የእግዚአብሔርን አምላክነት ሽሮ ራሱን አምላክ ሊያደርግ ። እንዲሁም ዛሬ ለአውሬው ጥርጊያ መንገድ እያዘጋጁ ያሉ በአውሬው መንፈስ የሚነዱ አንዳንዶች እግዚአብሔርን በመሳደብ ላይ ናቸው «በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበር «ቃልም ሥጋ ሆነ» ዮሐ. ወን ፩ ፥ ፩—፲፬ በማለት ወንጌላዊው የገለጸውን እውነታ ስተው በሥጋ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር አይደለም ብለው የካዱ ።

አውሬው ስድቡን በዚህ ብቻ አያበቃም አርባ ሁለት ወር ሙሉ (ሦስት ዓመት ከመንፈቅ የወደደውን የምትሐት ታምራት በማድረግ ራሱን ብቻ ከፍ በማድረግ የእግዚአብሔርን ማደሪያ ሳይቀር ይሳደባል ።

የእግዚአብሔር ማደሪያው የት ነው ።

«እኔ ግን በምህረትህ ብዛት ወደ ቤትህ (ማደሪያህ) እገባለሁ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ» መዝ ፭ ፥ ፯

«ኢየሱስም ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትን የሚገዙትን ሁሉ አወጣ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና ቤቴ የጸሎት ቤት ተባላለች ተብሎ ተጽፎአል እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው» ማቴ. ፳፩ ፥ ፲፪ና ፲፫ ።

ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ቤት ወይም ማደሪያ የሚባለው በአንድ መልኩ ክቡር ሥጋው ቅዱስ ደሙ የሚፈተትበት የእግዚአብሔር ስሙ የሚጠራበት የሚቀደስበት ቤተክርስቲያን ነች እንግዲህ ዛሬም ቢሆን ቤተክርስቲያንን የሚያንቋሽሹ ሁሉ በአውሬው



መንፈስ የሚመሩ ለመሆናቸው ማረጋገጫችን የእግዚአብሔር ቃል ነው ። ራእይ ፲፫ ፥ ፲ ።

እንዲሁም እግዚአብሔር ማደሪያው ትሆነው ዘንድ ከአንስተ ዓለም መርጦ የቀደሳት ድንግል ማርያም ነች መዝ ፻፴፩/፻፴፪) ፥ ፲፫ ። እግዚአብሔር የሰጣትን የአማላጅነት ክብር መናቅ ከመሰደብ የሚቆጠር ነውና ።

አውሬው የሚቀረው የለም በሰማይ የሚያድሩትን ቅዱሳንን ይሳደባል ዋጋ ኃይል እንደሌለቸው አድርጎ በመቁጠር ። ዛሬም በአውሬው መንፈስ የሚመሩ አንዳንዶች ከአውሬው ተቀድመው በሰማይ የሚያድሩ ቅዱሣን መላእክትንና ጻድቃን ሰማዕታትን እየተሳደቡ ነው የማይገጣጠም ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ እያወጡ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሲሉ ሰውነታቸውን ለእሳት አሳልፈው የሰጡትን ጻድቃን ሰማዕታት «በሕይወት ያለ ውሻ (ኃጢአተኛ) ይበልጠቸዋል ። መታሰቢያቸው ተረስቷል ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም መክ. ፱ ፥ ፩ በማለት ለጻድቃን ያልተነገረውን የተነገረ በማድረግ ያቀርባሉ ።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ጻድቃን ሲታሰቡ እንደሚኖሩ መታሰቢያቸውም ለዘለዓለም እንደሚኖር እነርሱንም (በሰማይ ያሉት ቅዱሣን) ማሰብ በረከትን እንደሚያሰጥ በስፋት ጠቅሷል ። መጽምሳ ፲ ፥ ፯ መዝ. ፻፲፩ ፥ ፯ ኢሳ ፶፯ ፥ ፩

ዋጋ ያላቸው መሆናቸውንም ጌታ ራሱ ገልጾዋል «የሚያምን ብኝ ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም» ዮሐ ወን ፲፩ ፥ ፳፭ በማለት ዋጋቸው ዘለዓለ ማዊ ሕይወት ማግኘት መሆኑን ገልጾአል ።

ይህን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ ከአእምሮ አስጠፍቶ የእግዚአብሔርን ቅዱሳን መሳደብ የአውሬ ተግባር ነው ።

አውሬው ለጊዜው ከቅዱሳን ከምእመናን ጋር ይጠላ ዘንድ ድል ይነሣቸው ዘንድ ሥልጣን ስለተሰጠው ይህን ጊዜያዊ ድል በማየት የምድር ወገኖች ለአውሬው ይንበረከካሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

**ከአውሬው ጋር ውጊያ የሚገጥሙት ቅዱሣን (ራእይ ፲፩ ፥ ፩—፲፫**

ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን (አርባ ሁለት ወር) ሐሣዊ መሢሕ በሚሰለጥንበት ዘመን ልክ (ያስተምሩ ዘንድ ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በበጉ ደም የታተሙትንና ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ላይ የተጻፉትን የጸኑ ዘንድ ።

ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች የተባሉት ኤልያስና ሄኖክ ናቸው ሄኖክ ማለት ተሐድሶ ማለት ነው ተሐድሶ በዘይት ነውና ኤል ያስም ማለት ዘይት ማለት ነው ። የእግዚአብሔር ባለሟሎች የሚ ሆኑ ሁለት መምህራን እኚህ ናቸው በትምህርታቸው የሰውን ልብና ብሩህ ያደርጋሉና ።

እነርሱም እስከዛሬ ድረስ የሞትን ጽዋ ያልተጎነጩ ዛሬ በብሔረ ሕያዋን የኖሩ ናቸው ኋላ በፍጻሜ ዘመን መጥተው ስለ አውሬው ሐሣዊ መሢሕ መሆን ስለ ታላቁ ጌታ ስለፈጣሪያችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ታላቅነትና አምላክነት ይመሰክራሉ ።

«ማቅ ለብሰው» መታየታቸው በሰማዕታት ሞት ኀዘን ተኞች መሆናቸውን ለመግለጽና እንዲሁም መከራ እየተቀበሉ ለማስተማር የመጡ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው ።

ጠላቶቻቸውን የሚያጠፋ እሳት ከአፋቸው ይወጣል ሰማዩን ያዘዙታል ዝናም ለዘር ጠል ለመከር እንዳይሰጥ ይከለክሉ ዘንድ ሥልጣን አላቸው ኤልያስ በዘመኑ በአክአብና በኤልዛቤል ጣኦት ማምለክ ተቆጥቶ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሰማይን ለጉሟል ዝናብ እንዳይሰጥ ያዕቆብ ፭ ፥ ፲፯ ።

ውሃውንም ወደ ደም ይለውጣሉ የሐሣዊ መሢሕን ምትሐታዊ ተአምር በአማናዊ ተአምር ያከሽፉ ታል ። የወደዱትን ያህል መቅ ሠፍት እያመጡ በሰው መከራ ያጸናሉ ሐሣዊ መሢሕ አምላክ አይ ደለም ብለው ሰማዩን ምድሩን የብሱን ባሕሩን የፈጠረ አምላክ አለ ብለው መስክረው አስተምረው ከፈጸሙ በኋላ ሐሣዊ መሢሕ ያስ ገድላቸዋል ።



ጌታቸው በተሰቀለበት አገር በኢየሩሳሌም ሕዝብ አሕዛብ እያየው ሬሣቸው ሦስት ቀን ተኩል ወድቆ ይታያል በዚህ ዓለም የሚኖሩ የሐሣዊ መሢሕ ግብራበሮች ደስ ይሰኛሉ እርስ በርሳቸው የደስታ መግለጫ ስጦታ ይለዋወጣሉ እነዚህ ሁለት ወይራዎች ሐሣዊ መሢሕን በመቋቋም የክርስቶስ ወገኖችን በእምነታቸው እንዲጸኑ አድርገዋልና ሐሣዊ መሢሕም እንዳይቀበሩ ይከለክላል ከሦስት ቀን ተኩል በኋላ ነፍሳቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዛ መጥታ ታድርባቸዋልች ይነሣሉ ጥግ መቋሚያ ሳይሹ ይቆማሉ ሁሉም በሚሰበሰቡበት በቀኑ እኩሌታ ይነሳሉ ዙሪያውን ከበው በሚያዩዋቸው ሰዎች ዘንድ ሁሉ ፍርሀት ሽብር ይሆናል ከወደ ሰማይም ድምጽ ይሰማል ኑ ወደዚህ ውጡ የሚል እነርሱም በክብር ወደ ሰማይ ያርጋሉ ጠላቶቻቸው እያዩአቸው ያን ጊዜ ፍጹም መነ ዋወጽ ይሆናል ።

## ከምድር የሚወጣ ሌላ አውሬ

«ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ የበግ ቀንዶችን የሚ መስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት» ራእይ ፲፫ ፥ ፲፩ ።

ይኸኛው አውሬ ሐሣዊ ኤልያስ እንደሆነ ይነገራል በፍጻሜ ዘመን ኤልያስ እንደሚመጣ አስቀድሞ ስለተገለጸ ሐሣዊ መሢሑም የቀሩትን ለማሣመን ሐሣዊ ኤልያስን ያዘጋጃል በእርሱ ያላመኑ ሌሎችን ይበልጥ ለማስተማመን ። ከየብስ ተነሣ ማለቱ ሐሰተኛው ኤልያስ የሚመጣው የሐሣዊ መሢሕ መንግሥት ከተደለደለ በኋላ ስለሆነ ነው ።

የበግ የመሰሉ ሁለት ቀንዶች አሉት የተባሉ እርሱ አስከትሎ አቸው የሚመጡ ሐሰተኛ ኤልሳዕና ሐሰተኛ አብድዩ ናቸው በግ ይመስላል ማለት ኤልያስ ነኝ ይላል ኤልያስን ለመምሰል ይሞክራል እሳት ከሰማይ ያወርዳል ሰዎች እውነተኛው ኤልያስ መስሎአቸው በሚከተሉት ጊዜ ሐሣዊ መሢሕ አምላክ እንደሆነ ይናገራል ያስ ተማምናል ።

የሐሣዌ መሢሕን ሥዕሉን ሥለው ምስሉን መስለው እንዲ ይዙ ያደርጋል ይይዙ ዘንድ ያዝዛቸዋል በሐሣዊ መሢሕ በተመሰ



www.ethiopianorthodox.org

ለው ምስል በተሣለው ሥዕል ቃል ያሳድርበት ዘንድ ሥልጣን ይሰጠዋል(ምስሉን በምትሐት ያናግረዋል) ።

በሐሣዊ መሢሕ ለተመሰለው ምስል ለተሣለው ሥዕል ያል ስገዱትን እንዲሞቱ ያደርጋል (በዐዋጅ ነው)

ታላቁ ታናሹም ድሆችም ባለጸጎችም ጌቶችም ባሮችም በቀኝ እጃቸው ዘመር ዘመስ (ዘመርምያዋዖስ) ብለው ይጽፉዘንድ ያውም ባይሆን በግንባራቸው ይጽፉ ዘንድ ያዝዛቸዋል እንዲጽፉ ያደርጋቸዋል ከእነዚህ ውጭ ምልክቱ ካልተደረገላቸው ውጭ ያሉት እን ዳይገዙ እንዳይሸጡ ያስደርጋል ።

«ብልህ አዋቂ የሆነ የአውሬውን መለያ ቁጥር ይቁጠረው የሰው ቁጥር ነውና ቁጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው ።»

## 666 ምሥጢራዊ ፍቺ

፩ኛ/ ብልህ አዋቂ የሆነ ዕውቀት ያለው የሐሣዊ መሢሕን መጠኑን ያውቃል በሰው ልክ መጠን ሦስት ክንድ ከስንዝር ቁመት ያለው ነው ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት አሥራው (ጅማቶች) ያሉት የዕለተ ዐርብ ፍጥረት (ሰብአዊ ፍጥረት) ነው ። በሃይማኖት አባቶች እምነት የወንድ ሰው ጅማት (ሥር) ፮፻፷፮ ሲሆን የሴቶች ደግሞ ፫፻፴፫ ነው ስለዚህ አውሬ የተባለው ሐሣዊ መሢሕም ከሰው ወገን የሆነ በዕለተ ዐርብ የተፈጠረ የአዳም ወገን ነው ብሎ ሌላ ፍጥረት አለመሆኑን ሲገልጽ ነው ።

፪ኛ/ የሐሣዊ መሢሕን የስሙን ቁጥር አእምሮ ያለው ሰው ያውቃል በእብራይስጥ መርምያስዋዖ የአውሬው ስም ነው በውስጡ ሰባት ፊደላት አሉት የእነዚህ ፊደላት ቁጥር ድምር 666 ይመጣል ።

ይኸንንም ግልጽ ለማድረግ የእብራይስጡን ፊደል ከነቁጥራቸው ማሳወቅ ያስፈልጋልና ከእዚህ እንደሚከተለው ይዘረዘራል ።

የእብራይስጡ ፊደል (Alphabet) እያንዳንዱ ፊደል ከሚወክለው አሐዝ (ቊጥር) ጋር በሚከተለው ሠንጠረዥ ለመግለጽ እሞክራለሁ ።



**የፊደላቱ ስም**

| በእንግሊዝኛ ፊደል ALPHABET | በአማርኛ ፊደል | ፊደሉ የያዘው የቁጥር ዋጋ (Numerical Value) |
|---|---|---|
| Aleph | አሌፍ | 1 |
| Beth | ቤት | 2 |
| Gîmel | ጋሜል | 3 |
| Daleth | ዳሌጥ | 4 |
| He | ሂ | 5 |
| Wáw | ዋው | 6 |
| Zayin | ዛይ | 7 |
| Hêth | ሔት | 8 |
| Têth | ጤት | 9 |
| Yôdh | ዮድ | 10 |
| Kaph | ካፍ | 20 |
| Lámedh | ላሜድ | 30 |
| Mêm | ሜም | 40 |
| Nûn | ኖን | 50 |
| Sàmekh | ሳምኬት | 60 |
| Ayîn | ዔ | 70 |
| Pé | ፌ | 80 |
| Câdhe | ጻዴ | 90 |
| Qôph | ቆፍ | 100 |
| Rês | ሬስ | 200 |
| Sin | ሳን | 300 |
| Taw | ታው | 400 |



www.ethiopianorthodox.org

መርምያዋፆስ የሚለውን የአውሬው ስም ሰባት ፊደላት ያሉት ናቸው ።

መ—ምሜ—40

ር—ሬሳ 200

ም—ምሜ —40

ያ—ዮድ—10

ዋ—ዋው— 6

ፆ—ዔ— 70

ስ—ሳን—300

## መርምርያዋዓስ — 666 (ድምር)

ከላይ በተገለጸው መሠረት 666 የአውሬው የስሙ ቁጥር ነው እንግዲህ 666 የሚለውን ማኀተም በወዳጆቹ ቀኝእጅና ግንባር ላይ ያትማል ማለት ነው እነዚህ ሰዎች በአውሬው ዘንድ ባለሟልነትን ሲያገኙ 666 የሚለውን የአውሬውን መታወቂያ ቁጥር በእጃቸው ወይም በግንባራቸው ላይ ያትማሉ የማያትሙት ግን እንዳይገዙ እንዳይሸጡ ይከለከላሉ ።

ዳሩ ግን በአሁኑ ጊዜ 666 የሚለው «የንግድ ምልክት» ሆኖ በሀገራችን የገባ ሲሆን በተለያዩ እቃዎችም ላይ ይህን ቁጥር ታትሞ እናገኘዋለን ቁም ነገሩ ከቁጥሩ ሳይሆን ከእምነቱ ነው አንድ ሰው 666 የታተመበትን ዕቃ ገዝቶ ቢጠቀምበት በልቡናው የአውሬው ምልክት ነውና አውሬውን ተቀብየዋለሁ ብሎ ካላመነ በስተቀር በክርስቲያናዊ ሕይወቱ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም ቁጥር ከእግዚአብሔር መንግሥት አይለይምና ዳሩ ግን አውሬውን አምናችሁ ለመቀበላችሁ ምልክት እንዲሆንላችሁ ኑ እናትምባችሁ ቢሉን ልናደርገው አይገባንም ። ወይንም በቅናሽ ዋጋ እቃዎችን ትገዙ ዘንድ ክርስቶስን ክዳችሁ አውሬውን ተቀብላችሁ ይህን ምልክት አድርጉ ቢሉን ፈጽሞ ማድረግ የለብንም ።



## በመጨረሻስ ?

በእግዚአብሔር ዘንድ ቀነ ቀጠሮ የተያዘላት ዓለም ወደ ፍጻሜዋ ታመራለች ጣዕምዋ ለዛዋ ይሟጠጣል ፍጻሜ ዓለም ይሆናል ምድር ከመሠረትዋ ትናጋለች ፀሐይ ማቅ ታጠልቃለች ብርሃንዋን ታጣለች ከዋክብት እንደ ቃሪያ ፍሬ ከሰማይ ላይ ይረግፋሉ የህልውናቸው ጊዜ አክትሟልና ከእንግዲህ ወዲህ እነርሱን እያየ የሚደነቅ ሰብአዊ ፍጡር አይኖርምና ።

በታላላቅ ድንጋይ የታተሙ መቃብሮች በውስጣቸው የያዙአቸውን ሙታን ይሰጣሉ የሙታን ሥጋ ከረዥም የእንቅልፍ ዓለም ይባንናል ሁሉም ወደ ፍርድ አደባባይ ይሰበሰባሉ ታላቁ ዘንዶ ለብዙዎች ምክንያት ስህተት የሆነው ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ በእሳት ሠንሠለት ታሥሮ ወደ ገሃነም ይጣላል ።

ፊተኛው ሰማይና ምድር ከፍጡራን ፊት መጽሐፍ ተጠቅልለው ያልፋሉ ሥፍራም አይገኝላቸውም ለዘለዓለም ያልፋሉ ይጠፋሉ ።

በበጉ ደም የተዋጁ ሃይማኖታቸውን የጠበቁ ታማኝ የክርስቶስ ዜጎች ገናናውንና እውነተኛውን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ሊቀበሉ ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ የድንግል ማርያም ልጅ የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ መለኮታዊ ግርማ ይመጣል ብዙ የብዙ በሚሆኑ ቅዱሣን መለእክት ታጅቦ በግርማ በክብር ይመጣል አቤት (በዚያን ጊዜ በፊቱ ችሎ የሚቆም ማን ይሆን? ሰማያት በታላቅ ትኩሳት ይቀልጣሉ እሳት ከፊቱ ይነዳል አመጣጡም በሥጋ ማርያም ነው መጥቶም ዝም አይልም እንደቀድሞው ከሀና ወደ ቀያፋ ከዚያም ወደ ጲላጦስ ሲወስዱት ዝም እንዳለ ሁሉ በዚህ ዓይነት አመጣጥ አይደለም እጅግ በሚያስደነግጥና በፍጹም መለኮታዊ ክብሩ እንጂ በዙሪያው ጥቅል ነፋስ አለ ማለት ኃጥአንን ከፊቱ ጠራርጐ ወደ ገሃነም የሚጨምር ማቴ ፳፭ ፥ ፴፩ ፈጣሪያችን በክበብ ትስብእት በግርማ መንግሥቱ በሚመጣበት ጊዜ ዝም አይልም ጻድቃንን እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ወደ እኔ ብሎ ለዘለዓለም ሕይወት ይጠራቸዋል ኃጥአንን ደግሞ «እናንተ ርጉማን ከእኔ ሂዱ» ብሎ ወደ ዘለዓለም እሳት (ሞት) ይልካቸዋል ።)



www.ethiopianorthodox.org

ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ መስለ ከእግዚአብሔር ዘንድ ትወርዳለች ማለት ለምእመናን ትሰጣለች ምዕመናን ርስት ሙንግሥተ ሰማያትን እጅ ያደርጋሉ ብርሃን ለብሰው ብርሃን ተጐናጽፈው ለዘንተ ዓለም በፍስሐ ይኖራሉ ።

ለዚህ አስደሳች ሕይወት የተጠራው መላው የሰው ዘር ቢሆንም በተጠሩበት መጠራት ጸንተው ለመመረጥ የሚበቁ ምን ያህል እድለኞች ናቸው!

እውነተኛና የታሙንህ ጌታ ሆይ ለዚህ እድል አብቃን አሜን!



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ስድስት

## ተጠራጣሪዎች የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

1. ዮሐንስ ወንጌል ፩ ፥ ፫ «...አንቺ ሆይ ካንቺ ጋር ምን አለኝ?» ይህን ማለቱ አማላጅነትሽን አልተቀበልኩም ማማለድ አትችይም ማለቱና አማላጅነትዋን መናቁ አይደለም ።

በዚህ ቤቃና ዘገሊላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ተአምሩን እንዳደረገ ተገልጿል ። ነገር ግን ከዚያ በፊት ተአምር አላደረገም ማለት አይደለም ። ሥጋን ተዋህዶ ከተገለጸ በኋላ ብዙ ሰው በተሰበሰበበት ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተአምሩን ማድረጉን ሲገልጽ ነው እንደዚሁም ሁሉ በዚህ በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ላይ የእመቤታችን አማላጅነትዋ ይፋ የወጣበትና የታወቀበት ነው ።

ሠርግ ተጠርተው በሄዱበት ቤት የወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ እመቤታችን ጠጅ አልቆባቸዋል እኮን አለችው ። እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር አለ ። እመቤታችን የወይን ጠጅ አልቆባቸዋል'ኮ ብላ ለጌታ መንገርዋ እርሱ የማያውቀው ነው ብላ አይደለም ። እርሱ የማያውቀው ነገር እንደሌለ ታውቃለች ። እንኳን ይኸን ግልጽ የሆነ ክስተት ቀርቶ ስውር የሆነውን ልቡና ያሰበውን ኩላሊት ያመላለሰውን ሳይቀር እንደሚያውቅ እያወቀች ልክ ሌሎቹ ሰዎች ጌታን ደካማ ሰው አድርገው እንደሚወስዱት ሁሉ እ'ሰዋም አለማወቁን አውቃ አሳወቀችው ብሎ የሚያምን የሚያስተምር ቢኖር እጅግ የተሳሳተ ከመሆኑም አልፎ ጌታንም ሆነ እናቱን እንደመሳደብ ይቆጠርበታል ።

እርሱ የወይን ጠጅ እንዳለቀባቸው አውቆ ዝም ማለቱ የእርስዋ አማላጅነት እንዲታወቅ ስለፈለገ እርስዋ እንድትጠይቀው ብሎ ነው ። እርስዋም የወይን ጠጅ እንዳለቀባቸው እንደሚያውቅ እያወቀች አልቆባቸዋል'ኮ ብላ መናገርዋ የእርሱ ፈቃድ ጥያቄው (ልመ





www.ethiopianorthodox.org

ናው) ከእርስዋ እንዲመጣ ብሎ መሆኑን ስለተረዳችና ስለምታውቅ ነው ። እንዲህማ ባይሆን እመቤታችን የወለደችውን የልጅዋን ማንነት አላወቀችም ያሰኛል ። ነገር ግን ከእመቤታችን የተሰወረ ነገር አልነበረም ። (ሉቃ ፩ ፡ ፴፰) ሉቃ ፪ ፡ ፶፩)

ታዲያ ሁለቱ ተስማምተው ወይም በመንፈስ ተግባብተው ከሆነ ጥያቄውን ያቀረበችው ስለምን «አንቺ ሆይ ካንቺ ጋር ምን አለኝ?» ሊላት ቻለ? የሚል ጥያቄ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር ምክንያቱንና የአባባሉን ትርጉም እንደሚከተለው እንደሆነ እንገልጽለታለን ።

አባባሉን አበክረን ስንመለከተው የነቀፋ ወይም አማላጅነትዋን ያለመቀበል ሳይሆን እንዳውም የፍቅር ፣ የትህትና የመቀበል መልስ ሆኖ እናገኘዋለን «እናቴ ሆይ ውሀውን ወይን ጠጅ አድርግላቸው ብለሽ ስትለምኝኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ካንቺ ጋር ምን ጸብ አለኝ? ከፍቅር በስተቀር ያልሽውን እፈጽምልሻለሁ ማለቱ ነው ። አባባሉ በዚህ መንፈስ መተርጐም እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል ። ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ ፲፯ ቍ. ፲፰ መመልከት ይቻላል ። በዚህ ምዕራፍ ላይ ኤልያስን ትቀልብ የነበረች መበለት ልጅዋ ይታመምና ይሞትባታል ። በዚህን ጊዜ ሴትየዋ የሰማይን መስኮት ዝናም እንዳይሰጥ የዘጋ ምድር የዘሩባትን እንዳታበቅል የገዘተው ታላቅ የእግዚአብሔር ነቢይ በቤትዋ ከእርስዋ ጋር እያለ ልጅዋ መሞቱ አሳዝኖአት «የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ኃጢአቴንስ ታሳስብ ዘንድ ልጄንስ ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃልን» አለችው ።

እንግዲህ ሴትዮዋ «የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ?» ማለትዋ ካንተ ጋር ጸብ አለኝ ወይ ላንተ ከመታዘዝ አንተን ከማስደሰት በስተቀር ያስከፋሁህ ነገር አለን? ማለትዋ መሆኑ ከማንኛችንም ሥውር አይደለም ። እንደዚሁም ሁሉ ጌታም «አንቺ ሆይ ካንቺ ጋር ምን አለኝ ሲል? «እምቢ እልሽ ዘንድ ካንቺ ጋር ጸብ አለኝ ወይ ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ይሆንልናል ። አንድም ውኃውን ጠጅ አድርግላቸው ብትይኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ውኃውን ጠጅ ላላደርግላቸው ከሠርግ ቤት ተጠርቼ መጥቻለሁን ውኃውን ጠጅ ላደርግላቸው ነው የመጣሁት (ታምራትን ልገልጽ ነው የመጣሁት) ሁሉም ነገር አስቀድሞ የተወሰነና በእርሱ ዘንድ የታቀደ መሆኑን ገለጸላት ።



«ነገር ግን ጊዜዬ አልደረሰም» ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ጊዜ ቦታ አለውና «ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንዲል ።» በቀትር የሚሠራውን በሰልስት አይሠራውምና በሰለስት የሚሠራውን በነግህ አይሠራውምና ።

በተጨማሪም «ጊዜዬ አልደረሰም» ማለቱ ጠጁ ፈጽሞ አላለቀም ነበር ። ጠጁ ሳያልቅ በዚያው ላይ ውኃ አስጨምሮ ቢሆን ኖሮ ያለውን አበረከተው እንጂ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ አልቀየረም ብለው ምክንያት በደረደሩና ተአምራቱ ድንቅ ባልተባለም ነበር ። ስለዚህ ጠጁ ፈጽሞ እስኪያልቅ ጠብቂኝ ያን ጊዜ ታምራቴን አሳያለሁ በዚያን ጊዜ የአንቺም አማላጅነት የእኔም አምላክነት ይታወቃል ሲል ነው ። ሌላም ምክንያት ነበረው በዚያች ቅጽበት ይሁዳ ከሠርጉ ቤት ወጥቶ ስለነበር እርሱ እስኪመለስ ድረስ ጠብቂ ምክንያቱም እርሱ (ይሁዳ) በሌለበት ቦታ ተአምራቱን አድርጐ ቢሆን ኖሮ ከተአምራቱ ቢለየኝ በሞቱ ገባሁበት ብሎ ይህን ምክንያት አድርጐ በቀረበ ነበርና ጌታን ለመሸጥ ያነሳሳው ምክንያት እንደሌለ ምክንያት ለማሳጣት ።

እንግዲህ እመቤታችን የጠየቀችው አማላጅነትዋ በልጅዋ ዘንድ ተቀባይነትን እንዳገኘ ስላወቀች ለሰዎቹ «የሚላችሁን አድርጉ» ስትል ነግራቸዋለች ። ልመናዋ በጌታ ዘንድ ተቀባይነትን ባያገኝ ኖሮ አማላጅነቴን ነቅፎታል (አልተቀበለኝም) ብላ ዝም ብላ በተቀመጠች ነበር ። ዳሩ ግን ከላይ እንደተገለጸው የጌታ መልስ መልካምና አማላጅነትዋን መቀበሉን የሚገልጽ መሆኑን ስለተረዳች የሚላችሁን አድርጉ ብላለች ።

በተጨማሪም አማላጅነትዋን ጌታ እንደተቀበለው የሚያስገነዝበን ዝቅ ብሎ የጠየቀችውን መፈጸሙ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡ ነው ።

ነገር ግን ይህን ሳያጤኑ ጌታን እንደ አንድ ተራ ስርዓተ አልበኛ ልጅ ቆጥሮ እናቱን በንቀት ከኔ ምን አለሽ? በሥራዬ ምን ያገባሻል ብሎ ዘልፏታል ብሎ መናገርና ማስተማር ጌታን ከመሳደብ አልፎ የስድብና የትዕቢት አስተማሪ አድርጐ ማቅረብ ነው ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን የጌታን ትሁትነት «ለእናቱ እየታዘዘ ማደጉን ነው» (ሉቃ. ፪ ፡ ፶፩) ። እርሱ እኛን እናትና አባታችሁን



www.ethiopianorthodox.org

አክብሩ እያለ እርሱ እናቱን «አንቺ ሴት በኔ ሥራ ምን አገባሽ ብሎ
ተቆጣት ፣ ገለመጣት» ብሎ መናገር ጌታን ከአንድ ደካማ ሰው አሳ
ንሶ ማየት ነው ። ጌታ ግን እንኳን ለእናቱ ለሰቀሉት ለአይሁድም
የትዕቢት መልስ አልመለሰም «የሚያደርጉትን አያውቁምና አባት
ሆይ ማራቸው» ከማለት ሌላ ።

2. ዕብራውያን ፯ ፥ ፫ «መልከ ጼዴቅ አባትና እናት የትውልድም
ቁጥር የሉትም ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም»

ይህን በመጥቀስ መልከጼዴቅ አባትና እናት እንደሌሉት እንደ
መልአክ አድርገው የሚመለከቱት አሉ ። ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ
አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም ማለቱ ትውልዱና ነገዱ
ከአብርሃም ወገን ሳይሆን ከአሕዛብ ወገን ነውና ነገዱ። አይሁድ
ሁሉ በትውልዳቸውና በነገዳቸው የሚመኩ ስለሆነ ወገኖቹን አይ
ሁድን ደስ ለማሰኘት ብሎ እንደ ሆነ ነው እንጂ የመልከ ጼዴቅን
ትውልድስ ታሪክ ጸሐፊዎች ግብጻውያን ዮሐንስ መደብርና አቡሻህር
በ፩ኛው ክፍል ወልደ ንጉሠ ግብጽ ወኖባ ዘነግሠ በከነዓን ይለዋል
የኖባና የግብጽ ንጉሥ ልጅ ማለት ነው ።

ኢየሩሳሌምን መጀመሪያ የቀረቀረና ያቀናት ሲዱ ይባላል ። እር
ሱም የግብጽና የሱዳን ንጉሥ ነበር ይባላል ። ከግብጽም ተሻግሮ
በከነዓናውያን ላይ በኃይል ነግሦባቸዋል ። በሀገሪቱም ላይ ከገሊላ
ባሕር ዳር ከተማ ሠርቶ በስሙ ቤት ሳይዳ አሰኝቷታል (ቤተ ጸጋ
ወሣህል) በዕብራይስጥ ቋንቋ የስጦታና የይቅርታ ቤት ማለት ነው ።
(ዮሐ. ፩ ፥ ፪) ። ሲዱ ሳሌምን ይወልዳል ፣ በሳሌም ኢየሩሳሌም ተብ
ላለች ። ሳሌም ሚልኪንና መልከጼዴቅን ይወልዳል ። መልከጼዴቅ
ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ የእውነት ንጉሥ የእውነት ገዢ ማለት
ነው ። እርሱም በቀራንዮ ላይ ቤተ መቅደስን አሠርቶ የደም መሥ
ዋዕት ሳይሆን በኅብስት በወይን ሲሰዋበት ስለኖረ መልከጼዴቅ
የልዑል እግዚአብሔር ካህን የእውነትና የሰላም ንጉሥ ተባለ በሚሞተ
ክህነቱም አብርሃምን ባርኮታል ትውልዱም ከነገደ ከነዓን ነው ።
አባትና እናቱም ከአሕዛብ ወገን ናቸው ።

ከመልከጼዴቅ እስከ ዳዊት ድረስ ሺህ ዘመን ከነዓናውያን
ኢየሩሳሌምን ወርሰዋት ኑረዋል ። ከዚህ በኋላ ዳዊት በነገሠ በ፲ኛው
ዓመት ዘርዓ ከነዓንን ነቅሎ ዘርዓ አብርሃምን ተክሎበታል ። በመጀ



መሪያ ዘመን በምድረ ከነዓን ከተማ የቀረቀረ የከነዓን ልጅ በኩሩ
ሲዶን ይባላል ። የሲዶንም ልጆች በአባታቸው ስም ከተማይቱን
ሠርተው ሲዶን ወይም ሲዶና ብለው ሰየምዋት ። ሁለተኛይቱን ግን
ጢሮስ ብለው ሰየምዋት ይባላል ።

3. ፩ኛ ጢሞ ፪ ፥ ፭ እግዚአብሔር አንድ ነው ሲል በባሕርይ በመ
ለኮት ሥላሴ አንድ መሆኑን ሲያስገነዝብ ሲሆን ፣ ሰው ሆኖ ሰውና
እግዚአብሔርን ያስታረቀ ኢየሱስ ክርስቶስም አንድ ነው አለ ።
በተለየ አካሉ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ
ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ መዋሐዱን ሲያስረዳ ነው ። ጌታችን ኢየ
ሱስ ክርስቶስም ለሁሉ ቤዛ አድርጐ ራሱን አሳልፎ ለሕማም ለሞት
መስጠቱን ገልጾ እርሱ ታርቆን በተለየ አካሉ ለአዳምና ለልጆቹ
ሁሉ መስዋት ሆኖ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ህይወቱ ከመን
ፈስ ቅዱስም ጋር እንዳስታረቀን ገለጸ ። እግዚአብሔርነት የሦስቱም
ገንዘብ ነውና እግዚአብሔር የሚለው ስም የሥላሴ የአንድነት ስም
ነው ።

ምናልባት አንድ ሰው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው
የሚለውን በአማላጅነት ወስዶት ዛሬም ከእግዚአብሔር አብ ጋር
የምንገናኝበት አማላጃችን መሆኑን የሚያስረዳ ነው ሊል ይችል
ይሆናል ። ይህ ግን ስሕተታዊ አመለካከት ከመሆኑ አልፎ የሥላሴን
የባህርይ አንድነትና በመለኮታዊ ሥልጣን አንድ መሆናቸውን የሚ
ጻረር ነው ። በእርግጥ ጌታችን ኢየስሱ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰ
ቅሎ ስለ አዳም ካሣ ሆኖ መቅረቡ የማይካድ ቢሆንም የማስታረቅ
አገልግሎቱ ግን የተፈጸመው በመስቀል ላይ ነው ። ከዚያ በኋላ ግን
ሲያስታርቀን የሚኖረው በእለተ አርብ የፈጸመው የማስታረቅ አገል
ግሎቱ ነው ። ይኸውም ተልዕኮ ለዘለዓለሙ ህያው እንደሆነ ቅዱስ
ጳውሎስ በዕብራውያን ፯ ፥ ፳፭ ላይ ገልጾታል «ዘወትር በእርሱ በኩል
ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ለዘለዓለም ሕያው ነውና ያስታር
ቃቸዋል»

• መጽሔት አሚን ገጽ 14—15



www.ethiopianorthodox.org

በዕለተ ዓርብ ባደረገው ተልዕኮ እስከ ምጽአት ድረስ ሲያድን በት የሚኖር ስለሆነ ያስታርቃቸዋል ሊል ቻለ እንጂ ዛሬም ክርስቶስ አብን ይለምናል ማለቱ አይደለም ። ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንድነት ሆኖ ምልጃን ይቀበላል ይማለዳል እንጂ አያማልድም ። በባህርይ በመለኮታዊ ሥልጣን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነውና ። አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም ከተባለ ታዲያ ክርስቶስ ለአብ የሚያማልደው ለምንድን ነው? ነገር ግን በዕለተ ዓርብ የፈጸመው የማስታረቅ አገልግሎት ዛሬም እኛን ከአብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ባጭሩ ከእግዚአብሔር ጋር ሲያስታርቀን ይኖራል እንጂ ዛሬ ኃጢአት ስንሠራ ከኃጢአታችን ለመንጻት የክርስቶስን ዳግመኛ መ ስቀል የምንጠባበቅ አይደለንም ። ይህንን ሁኔታ ግልጽ ሲያደርግ ጳው ሎስ ለዘለዓለም ሕያው ነውና ያስታርቃቸዋል ብሎ ሕያው ዘለዓለማዊው አምላክ የፈጸመው የማስታረቅ ተልዕኮ ዘለዓለማዊ መሆኑን አስረገጠን እንጂ ክርስቶስ ዛሬም ያማልዳል አላለም ።

4. ዮሐ. ፲፱ ፥ ፴ «ጌታችን ኢየሱስም ሆምጣጣውን ከተቀበለ በኋላ ተፈጸመ አለ» ተፈጸመ ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

፩ኛ/ በመጻሕፍት ይወርዳል ፥ ይወለዳል ፥ ይጠመቃል ፥ ዞሮ ያስተምራል በመጨረሻም ስለ ሁሉ ኃጢአት ተላልፎ ይሰጣል የተባለው በነቢያት የተነገረው ሁሉ እነሆ ደረሰ ተፈጸመ ማለቱ ሲሆን ፤

፪ኛ/ በማኅጸን የጀመረው ካሣ አሁን በዚች ሰዓት ተፈጸመ ብሎ ስለ አዳም ፍጹም ካሣ መክፈሉን መግለጹ ነው ።

5. ፩ኛ ዮሐ. መል. ፪ ፥ ፩ «ልጆቼ እንዳትበድሉ ይህን እጽፍላችኋለሁ ፥ የበደለም ማንም ቢኖር ጰራቅሊጦስ አለን ከአባት ከ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ቸር ነው ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ»

የዚህ መልእክት ዓላማ በድሎ ንስሐ የገባ ሰው ቢኖር ተስፋ ቆርጦ በበደል ላይ በደል በኃጢአት ላይ ኃጢአት እንዳይጨምር በሠራው የኃጢአት ሥራ ተጸጽቶ በደልኩ ብሎ ንስሐ እንዲገባ የሚመክር ሲሆን በኃጢአቱ ተጸጽቶ ንስሐ ለሚገባ ለዚያ ሰውም



ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ የሚሰድልን ጰራቅሊጦስ አለን ከኃጢአታችን ያነጻናል ያድሰናል ። ጰራቅሊጦስ ማለት መንጽሒ ፥ (የሚያነጻ) መጽንዒ (የሚያጸና) መስተፍሥሒ ፥ (የሚያስደስት) መስተሥርይ ፥ ከሣቲ ፥ የሚገልጽ ናዛዚ (የሚያረጋጋ ማለት ነው ። ስለሆነም ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ ቸር የባሕርይ አምላክ ነው ። ብሎ የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት ይመሰክራል እንጂ ክርስቶስ ጠበቃ ነው ከአብ ዘንድ ቀርቦ ስለ ኃጢአታችን ይሟገታል የሚል ቃል በፍጹም አልተጻፈም አግባባዊ አነጋገርም አይደለም ።

6. ፩ኛ ጢሞ ፬ ፥ ፩—፭ «መንፈስ ግን በግልጽ ይናገራል በኋላ ዘመን ብዙዎች ሃይማኖታቸውን እንደሚክዱ የሚያስቱ አጋንንትንና የሚያጠራጥረውን የሰይጣናትን ትምህርትም እንደሚከተሉ ሐሰትን የሚናገሩ በገዛ አሳባቸው የሚቃጠሉ ናቸው ። ጋብቻን እርም የሚሉ ምግቦችን የሚከለክሉ ጽድቅን የሚያውቁአት በልተው ያመሰግኑ ዘንድ እግዚአብሔር ለአማኞች የፈጠረውን «እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም ነውና ምንም የሚጣልም የለበትምና አመስግነው ከተቀበሉት በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ይቀደሳልና»

ይህን ቃል በሚገባ አንብበው ያልተረዱ አንዳንዶች በራሳቸው ትርጉምና አረዳድ በመውሰድ አንዳንዶች ምንኩስናን (ድንግልናን) ለመንቀፍ ነው ሲሉ ደግሞ ሁሉንም ፍጥረት እንድንበላ ተፈቅዷልና አይጡንም ግመሉንም ፥ እባቡንም አህያውንም መብላት አለብን እንዲሁም ከቅጠላ ቅጠልም ጫት ፥ ሲጋራ የመሳሰሉት ሁሉ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ስለሆኑ እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም ነውና የሚጣልም የለበትም ስላለ እኛም ጫት በመቃማችን ሲጋራ በማጤሳችን ልንወገዝ አይገባም ይላሉ ።

በመሠረቱ እግዚአብሔር የፈጠረው ሥነ—ፍጥረት ሁሉ ውብ ያማረ እንከን የማይወጣለት መሆኑ በሁላችንም ዘንድ የታመነ ሲሆን ነገር ግን «ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል» እንደሚባል ሁሉ ለምግበ ሥጋና ለምግበ ነፍስ የተፈጠረውን ለእንክርዳ ለተዘከር የተፈጠረውን ለይቶ ማወቅና በየአግባቡ መጠቀም የሰዎች ሥራ ነው ። ለእንሰሳት የተሰጠውን ሣርና ቅጠል ሰው ቢበላ ከህመምና ከጉዳት በስተቀር የሚያተርፈው ነገር እንደሌለ የታወቀ ነው ። እንዲሁም እባ



www.ethiopianorthodox.org

ብን ይዞ እስከነመርዙ ቢበላው መርዙ በሙላ ሰውነቱ ተሠራጭቶ እንደሚገድለው እያወቀ ቢያደርገው ይህ ሰው የራሱ ገዳይ መሆኑ እንደሆነ ሊያጤነው ይገባል ።

የቅዱስ ጳውሎስ አገላለጽ ግን አንዳንድ የሐሰት መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ለመንቀፍ ተብሎ የቀረበ ነው ። በዞራስትርን እምነት ለዚህ ዓለም ሁለት ፈጣሪዎች አሉ ። እነርሱም ደግ አምላክና ክፉ አምላክ ተብለው ይጠራሉ ። ደጉ አምላክ ወንድ ሲፈጥር ክፉው አምላክ ሴትን ፈጠረ ይላሉ ። አያይዘውም ከምግቦችም በደጉ አምላክ የተፈጠሩና በክፉው አምላክ የተፈጠሩ እንዳሉም ይገልጻሉ ። ስለዚህ የደጉ አምላክ ወገኖች ለመሆን የሚፈልጉ ሁሉ ደጉ አምላክ የፈጠራቸውን ብቻ መብላት አለባቸው እንዲሁም በክፉው አምላክ ከተፈጠሩት ከሴቶች ጋር መጋባት የለባቸውም ። ስለ ሆነም ጋብቻን ርኩስ ይሉ ነበር ። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን እምነት ሲነቅፍ እንጂ እሱ ራሱ የመረጠውንና የያዘውን የድንግልና ህይወት መንቀፉ አይደለም ። (፩ኛ ቆሮ ፯ ፥ ፩—፯)

ቅዱስ ጋብቻም ሆነ የድንግልና ሕይወት ሁለቱም በአግባቡ ከተያዙ ለመንግሥተ ሰማያት ያበቃሉ ። ነገር ግን ከዚህ ወጥቶ ግቢ ርኩስ የሚል ቢኖር እርሱ ራሱ ርኩስ መሆኑን መግለጹ መሆኑን ሊገነዘበው ይገባል ። ምክንያቱም የተገኘው በጋብቻ ነውና ። እንዲሁም በድንግልና መኖርን (ሥርዓተ መላዕክትን) ንቆ ይህ አስፈላጊ አይደለም አያጸድቅም የሚል ቢኖር ይህም ሰው ምንም የማያውቅና መላዕክትን የጠላና የነቀፈ ቅዱሳንንም የጸረፈ መሆኑን ይረዳው ።

<u>መነናውያን ሦስት ሕግጋት ነበሯቸው ።</u>

1. አፍን መጠበቅ የመጀመሪያው ሕግ ነው «ማሕተመ አፍ ይባላል» (Signaculum Oris) በአንደበት ክፉና ነገረ ዘርቅ መናገር ክልክል ነው ሥጋ ጠጅና ወተት ዕንቁላልም አይቀመስም (በማናቸውም ቀን)

2. እጅን ከኃጢአት መጠበቅ «ማሕተመ ዕድ» (Signaculum Manum) እንስሳትን መግደል ዕጽዋት አዝርዕትን መቅጠፍ ፍሬ መልቀም ሳይቀር ክልክል ነው ።



3. በንጽሕና መጠበቅ «ማሕተመ ሕጽን» (Signaculum Sins) ጋብቻንና መራባትን ይከለክላል

ጳውሎስ የዚህን ዓይነት እምነት ሲነቅፍ እንጂ ጾምና ፥ ምን ኩስናን ፥ የምንበላውን ለይተን ማወቅ እንደዚሁም ሰውነትን የሚጎዱትን ምግቦች መተው አግባብ አይደለም ማለቱ አይደለም ።

ምናልባት አንድ ሰው ሲጋራ ማጨስ ጫት መቃም ለምን ተከለከለ ብሎ ሊጠይቅ ይችል ይሆናል ።

በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቃል በቃል ሲጋራ አታጭስ ፥ ጫት አትቃም የሚል ባይኖርም ፤ በምሥጢር ወይም በትርጉም ማድረጉ አግባብ አለመሆኑን የሚጠቅስ አለ ።

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ናዝራውያን ሲጋራ የማይጨስበትን ምክንያት ሲገልጹ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ጊዜ (ቀን) የሌሎች ዕጽዋት ቅጠሎች ሁሉ ሲጠወልጉና ሲደርቁ የጥምባሆ (ሲጃራ) ቅጠል ለምልሞ ስለተገኘ ተወግዟል ይላሉ ። ይህ ግን በመጽሐፍም ሆነ በሊቃውንት ዘንድ የተደገፈ አይደለም ። እንዲሁም ሌሎች ደግሞ በአርዮስ ፈርስ ላይ የበቀለ ስለሆነ ነው የረከሰው ይላሉ ይህ ደግሞ ልዩ ክህደት ነው ። ምክንያቱም በዕለተ ሰሉሥ ያልተፈጠረ ሌላ ዕጽ በኋላ እንደ ተፈጠረ አድርጎ ማቅረብና ሌላ ፈጣሪ እንዳለ መናገር ስለሆነ ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው ።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጥምባሆም ሆነ ሌሎች ጐጂ ዕጽዋትን መውሰድ (መጠቀም) ለምን በቤተ ክርስቲያን ተከለከለ የሚለውን ጥያቄ እንዲህ ይመልሱታል ።

፩. ሰውነትን የሚጎዳ ማንኛውም ቅጠላ ቅጠል የተፈጥሮ ባሕሪያችንና የጤና አጠባበቅ ደንባችን እንዳንጠቀም ይከለክለናል ። ስለዚህ ትምባሆ ሲቃሙት ወይም አመድ ቀላቅለው ሲጐርሱት ግማቱና ክርፋቱ መልካም አለመሆኑን ይገልጻል ። ሲጋራ አድርገው ሲመገምጉት ደግሞ ከጢሱ

---

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 67



www.ethiopianorthodox.org

ጋር ተቀላቅሎ ልብንና ሳንባን እንዲሁም የአፍንጫ አስም ያለባቸውን ሰዎች እንደሚጐዳ አገር ያወቀው ጸሐይ የሞቀው እውነታ ስለሆነ ሰውነታችንን የሚጐዳ ነገር ደግሞ እንዳናደርግ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለታዘዝን ልንተወው ይገባል ።

፭. መዐዛው ከቤተ ክርስቲያን ጢስ (ዕጣን) ጋር አይስማማምና በቤተክርስቲያን ውስጥ ማጤስና መቃም አያስፈልግም ። ቤተክርስቲያን ስንል ደግሞ ህንጻውን ብቻ ማለታችን እንዳልሆነ ከሁላችን የተሰወረ አይደለም ። እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ስለሆነ ቤተክርስቲያን ነው ፣ (፩ኛ ቆሮ ፫ ፡ ፲፯ ፪ኛ ቆሮ. ፮ ፡ ፲፮) ። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ማደሪያ በግማት በክርፋት ልናጥነው አይገባንም እግዚአብሔር ንጹሐ ባህርይ አምላክ ስለሆነ ንጹህ ነገር ይሻል ።

፮. ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ የሚል መልእክት ጽፏል «ሌላው እናንተን አይቶ እንዳይስት ለራስህ የማትወደውን ለሌላ አታድርገው» ስለዚህ አንድ ክርስቲያን በዚህ ቃል መሠረት ወንድሙ ወይም ወዳጁ የማይወደው ጢስ የማይወደው ሽታ ስለሚሆን ስለወንድሙ ብሎ ይህን ጥሩ ሽታ የሌለውና ጐጂ የሆነን ነገር ይተወው ፤ (ሮሜ ፲፬ ፡ ፳—፳፩) ።

7. መጽሐፈ መክብብ ፱. ቍ. ፬—፮ ። ያልሞተ ውሻ ከሞት አንበሳ ይሻላልና ሰው ከሕያዋን ሁሉ ጋር በአንድነት ቢኖር ተስፋ አለው ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉና ሙታን ግን አንዳች አያውቁም መታሰቢያቸው ም ተረስቷልና ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም ፍቅራቸውና ጥላቸው ቅንዓታቸውም በአንድነት ጠፍቶአል ከጸሐይ በታችም በሚሠራው ነገር ለዘላለም እድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም»

ይኸን ጥቅስ በመጥቀስ የሞቱ ጻድቃንና ሰማዕታት ሊያማልዱ አይችሉም የሚሉና ጥቅሱ ለሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት የተጠቀሰ እንደሆነ አድርገው የሚናገሩ አሉ ።



ነገሩ «ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ » አይነት ነው ። በእነዚህ ክፍሎች አተረጳጐም የልሞተ ውሻ» በሕይወተ ሥጋ ያሉ ኃጢአተኞች ሲሆኑ የሞተ አንበሳ የተባሉት ደግሞ የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት ናቸው ። ይላሉ ሙታን አንዳች አያውቁም መታሰቢያቸውም ተረስቷልና ከዚያ በኋላ ዋጋ ያላቸውም የሚለውን ቃል ነቅሰው በማውጣት ጻድቃን ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ አንዳች አያውቁም መታሰብም የለባቸውም ከሞቱ በኋላ ዋጋ አይኖራቸውም ይላሉ ። ይኽ አባባል ግን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተያየት እጅግ የተሳሳተና ታላቅ ክህደት ሆኖ እናገኘዋለን ።

## ሙታን አንዳች አያውቁም ሲባል እንዴት ነው

ሰው ማለት የሰባት ነገሮች ውሕደት ማለት ነው ። እነዚህም አራቱ ባሕርያተ ሥጋና ሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ተብለው ይጠራሉ ። አራቱ ባሕርያተ ሥጋ የሚባሉት እሳት ፤ ነፋስ ፤ መሬት ፤ ውኃ ሲሆኑ ሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የሚባሉት ደግሞ ለባዊነት (ልብ ማድረግ ማወቅ ፤ (ነባቢነት (መናገር) ፤ ሕያውነት (ሕያው መሆን) ናቸው ።

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ሰው የሥጋና የነፍስ ውሕደት ነው ። በሕይወተ ሥጋ ሳለ ነፍስና ሥጋው በተዋሕዶ ሆነው ያንቀሳቅሱታል ዕለተ ሞቱ ደርሶ ወደ ላዕላዊው ፈራጅ ሲጠራ ተዋሕደው ይኖሩ የነበሩት ነፍስና ሥጋው በሞት አማካይነት ይለያያሉ ። ነፍስ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ባሕርይዋ ህያውነት ስለሆነ ለፍርድ ወደ ህያው አምላክ ስትሔድ ሥጋ ግን ወደ መቃብር ይወርዳል ። ወደ አፈርነቱ ይመለሳል ። ሕያዊት ነፍስ ተዋሕዳው በነበረ ጊዜ ይፈራ ይከበር ፤ ያውቅ የነበረው ሥጋ አሁን ግን ነፍስ በተለየችው ጊዜ አስከሬን ይሆናል ክብሩን ሁሉ ይገፈፋል እንደ ቆሻሻ ይቆጠራል ሬሳ ተብሎ እንደ እንስሳት ሬሳ ይጣላል ክብርም አይኖረውም ቀድሞ እንደ አንበሳ ግርማው ያስፈራ ያስደነግጥ የነበረው ከሞተ በኋላ ግን በሕይወተ ሥጋ ያሉ እንደ ውሻ የተናቁ ሰዎች በእግራቸው ይጠቀጥቁታል ። ይኸ ሁሉ ግን በአጠቃላይ ሰው ለተባለ ሁሉ የሥጋውን ፈራሽ በሰባሽነት ለማስረዳት የተነገረ እንጂ ለጻድቃን ሰማዕታት ተለይቶ የተነገረ አይደለም በአንጻሩ ደግሞ ሰው ሁሉ በሥጋው በኩል እንዲህ አይነት አነጋገር ቢነገርለትም በነፍስ በኩል ስላለው ሕያውነት ደግሞ በሰማይ በእግዚአብሔር ገነት ወይም በሲኦል



www.ethiopianorthodox.org

እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስገነዝበን ሀቅ ነው ። ሉቃ. ፳፫ ቁ. ፵፫ ። ራዕይ ፪. ቁ. ፲ ። ሉቃ. ፲፮. ቁ. ፲፱—፴፩ ።

ሙታን እንዳች አያውቁም የሚለው አባባል በሥጋቸው እንጂ በነፍሳቸው አለመሆኑን ልናውቅ ይገባናል ። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል «በቃለ እግዚአብሔር ሰላሙኑ ሕጉን ስለ ጠበቁ በሰማዕትነት የሞቱ ሰዎች ነፍሳቸውን ከመሠዊያ በታች አየሁ» ራእይ ፮. ቁ. ፱ ። ሥጋቸው በምድር ላይ በውስተ መቃብር ሲሆን ሕያዊት ነፍሳቸው ግን በእግዚአብሔር እጅ መሆንዋን ይነግረናል» የጻድቃን ነፍሳቸው በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነው» እንደተባለው ሁሉ ጻድቃን ሰማዕታት ነፍሳቸውን ለታመነው አምላካቸው ይሰጣሉና «ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጣራ ይወግሩት ነበር» ሐዋር. ሥራ ፯. ቁ. ፶፱ ። አምን በክርስቶስ ያመነ ሁሉ ነፍስ፡ በጌታ እጅ ውስጥ ነው የምትሆነው ።

ስለዚህ በሥጋ ቢሞቱም በነፍስ ግን ሕያዋን ናቸው ። «የሕያዋኑ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም» ማርቆስ ፲፪. ቁ. ፳፯ ። እንግዲህ አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ በሥጋ ሞተው መቃብራቸው የታወቀ ሲሆን ፤

ጌታ ግን የእነዚህን የሞቱ ጻድቃን ስም ጠርቶ ሕያዋን ናቸው ማለቱ የሞቱት በሥጋ እንጂ በነፍስ ሕያዋን መሆናቸውን ለማሳወቅ አይደለም ?

## ለሞቱ ጻድቃንና ሰማዕታት መታሰቢያ ማድረግ በረከት እንደሚያሰጥ.

መታሰቢያቸው ተረስቷልና የሚለውን በመጥቀስ የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታትን ማዘከር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ እንደሆነ አድርገው የሚናገሩ አሉ ዳሩ ግን ይኸ አባባል ስለ ክርስቶስ ወንጌል ሲሉ ሰውነታቸውን ለእሳት ለስለት አሳልፈው ለሰጡ ለወንጌል አርበኞች ለጻድቃን ሰማዕታት የተነገረ አለመሆኑን በሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች እናረጋግጣለን ፤



ታላቁ የጥበብ ሰው ሰሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ ም. ፲. ቁ. ፯ ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል «የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው የኃጥእን ስም ግን ይጠፋል» እንግዲህ ይኸን ቃል መነሻ አድርገው የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታትን መታሰቢያ የሚያደርጉ ሰዎች ከሞቱት ጻድቃን ሰማዕታት በረከትን ለመቋደስ መሆኑን መገንዘብ ያሻል ፤

ልበ አምላክ ዳዊት ደግሞ ጻድቃን ሰማዕታት እንደተቃዋሚ (ተጠራጣሪዎቹ) አባባል ሞተው ፈርሰው በስብሰው የቀሩና መታሰቢያቸውም በምድር ባሉ በክርስቶሳውያን ዘንድ የተዘነጋ ሳይሆን ለዘላለም እንደሚኖር ሲገልጽ «የጽድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል» ሲል ዘግቧል መዝ ፻፲፩/፻፲፪/ ቁ. ፯ ፤

ይኸው ነቢይ እግዚአብሔር ዳዊት እግዚአብሔር ለጻድቃን በሕይወተ ሥጋ እያሉ የገባላቸው ቃል ኪዳን ከሞቱ በኋላም እንደሚሠራ ሲገላጽ «ኪዳኑንም ለዘላለም ያስባል» ብሏል መዝ. ፻፲ (፻፲፩). ቁ. ፭ ።

ሌላው የእግዚአብሔር ነብይ የሆነው ኢሳይያስ ደግሞ እግዚአብሔር በእውነት ለሚያመልኩት ሰዎች የሰጠውን ጸጋ ሲያስገነዝብ ፤

እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና በቤቴና በቅጥሬ (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ» ኢሳይ ፶፮. ቁ. ፬—፭ ።

እንግዲህ ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱሳን በከፊል ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ የምትቀበል ስለሆነች ይኸን የእግዚአብሔርን ቃል በተግባር ላይ አውላዋለች ። ለዘሁም ሁነኛ ማስረጃዎች ለእግዚአብሔር ቃል ሲሉ በሰማዕትነት ባለፉት ጻድቃን ስም ቤተክርስቲያን ማሳነጽዋ ነው ። ቤተክርስቲያን ክቡርና ልዑል እግዚአብሔር የሚሠለስባት የሚቀደስባት ሥጋውና ደሙ የሚፈተትባት ሲሆን ዳሩ ግን ቅዱሳኑ ይታሰቡበታል ። ለዚሁም እንደ አብነት አድር



www.ethiopianorthodox.org

ግን በጳውሎስና በጴጥሮስ ስም የተሰየሙትን ቤተ ክርስቲያኖች ልንጠቅስ እንችላለን ።

እግዚአብሔር ለስሙ ፥ ለክብሩ ለአምልኮቱ ቀንተው በስማዕትነት ያለፉትም ሆኑ በሕጉ በትዕዛዙ ጸንተው የኖሩ ሰዎች የማይጠፉ የዘላለም ስም እንደሰጣቸው ገልጾአል በዚህ ምክንያት የተነሣ ኢሳይያስም ሆነ ዳዊት ከሞቱ ረዥም ጊዜ ቢሆናቸውም ዳሩ ግን ጌታ እግዚአብሔር ስማቸው እንደማይጠፋ ስለተናገረ እርሱን በሚያመልኩት ሰዎች ዘንድ ሁሉ ሲታሰቡ ይኖራሉ ።

ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ ወን. ም. ፲ ቍ. ፵፪ ላይ እንዲህ ሲል ተናግሯል «ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም» በማለት ዛሬ ክርስቲያኖች በሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት ስም የሚያደርጉትን ዝክር (መታሰቢያ) በእውነት ተቀብሎ ለአድራጊዎቹ ዋጋ እንደሚሰጣቸው በማይታበል ቃሉ ተናግሯል እንግዲህ ከጌታ የበለጠ ማን ሊያረጋግጥልን ይችላል ።

## ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም የሚለው አባባል ሰሞቱት ጻድቃን ሰማዕታት የሚስማማ አባባል ነው?

እንደ እውነቱ ከሆነ ጻድቃን ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ ዋጋ የላቸውም የሚለው አባባል በክርስቶስ አዳኝነት አምናለሁ ከሚል ክርስቲያን አፍ ይወጣል ተብሎ ሊታመን አይችልም ። ምክንያቱ እነዚያ ስለ እግዚአብሔር ቃል የተወደደ መሥዋዕት ሆነው ያለፉ ሰማዕታት ዋጋቸው ፈርሶ በስብሶ ሙቅረት ወይም ዋጋ ቢስ መሆን ከሆነ ዛሬ በ21ኛው ሙቶ ክፍለ ዘመን ያለን የክርስቶስ አማኞችስ ተስፋችን ምንድር ነው ? እነዚያ ስለተጋድሎአቸው ዋጋ ካልተሰጣቸውና ከሞቱ በኋላ ዋጋ የላቸውም ከተባለ እኛስ ምን ዓይነት ዋጋ ለማግኘት ከዚች ከፉ ዓለም ከሰይጣን ጋር እንታገላለን ።

በመሠረቱ ይኸ አባባል የእግዚአብሔር ቅዱሳንን መድፈር ብቻ ሳይሆን ዛሬም በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን ዘላለማዊ ዋጋ በተስፋ



የምንጠባበቀውን ሁሉ ተስፋ የሚያስቆርጥና ወደ ኃጢአት እንድንመራ ተስፋ መንግሥት ሰማይን እንዳናዘክር በሰይጣን በኩል የተጣለ የማሰናከያ መረብ ነው ።

እውነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነችው መድኅኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ስለሚያምኑ ሰዎች ተስፋ ሲናገር እጠቅሳለሁ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም» ዮሐ. ወን. ፲፩. ቍ. ፳፭ ።

እንግዲህ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ከሞት ወደ ሕይወት ከጉስቁልና ወደ ፍጹም ደስታ ከዋጋ ቢስነት ወደ ዋጋ ማግኘት መሸጋገሩን ገልጾልናል ። ታዲያ እውነተኛው ጌታ በእርሱ የሚያምኑ ዘላለማዊ ዋጋ እንደሚያገኙ እየተናገረ ጻድቃን ሰማዕታት ከሞተ በኋላ ዋጋ የላቸውም ብሎ መናገር አግባባዊነት አለው? የዚህ አይነት እምነት ያላቸው ሰዎች ቁጥራቸው ከክርስቶሳውያን ሳይሆን ከሰዱቃውያን መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል «ሰዱቃውያን ሰው ከሞተ በኋላ ዋጋ የለውም የሚሉ ናቸውና» ሐዋ/ሥራ ፳፫. ቍ. ፰ ።

ክርስቶሳውያን ግን መሪያቸውና ፈጣሪያቸው ልዑል ባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን መሠረት በማድረግ በእርሱ የሚያምን ሁሉ ዋጋ እንዳለውና ዋጋውም ዘላለማዊ ሕይወት መሆኑን ያምናሉ ያስተምራሉ ።

በመጽሐፈ ምሳሌ በም. ፲ በቍ. ፳፭ ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን «ዐውሎ ነፋስ ሲያልፍ ኃጥእ አይገኝም ጻድቅ ግን የዘላለም መሠረት ነው» ከዚህ አባባል የምንረዳው ቁም ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር ያመነ ሰው ዘላለማዊ ዋጋን በማግኘት ለዘላለም ከአምላኩ ጋር በፍስሐ እንደሚኖር ነው ።

የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት አስከሬን ዋጋ የለውም ተብሎ እንደ አልባሌ ነገር መታየት የለበትም ኃይለ እግዚአብሔር የሚገለጥበት ነውና ። ለዚሁም ዓቢይ ምሳሌነት የሚኖረው የኤልሳዕ አጥንት ነው ። ከሞተ እጅግ ብዙ ጊዜ የሆነው ነቢዩ ኤልሳዕ በአጽሙ የሞተ ሳው እንዳስነሳ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ም. ፲፫ በቍ. ፳፩ ላይ ሰፍሯል ።



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ የእግዚአብሔር ኃይሉ በሕይወተ ሥጋ ባለ ኃጥእ ሰው ላይ ሳይሆን በሞተው ጻድቅ ላይ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ስለገለጸልን የእግዚአብሔር ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ ዋጋ የላቸውም በሕይወተ ሥጋ ያለኃጥእ ይበልጣቸዋል ማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ የእግዚአብሔር ቅዱሳንን ለመሳደብ ተብሎ መሆኑን መረዳት አለብን ።

የሙክብብ አባባል ሰው ከሞተ በኋላ በሥጋው በኩል የሚገጥመውን ሁኔታ ለመናገር ፈልጐ እንጂ እንደተጠራጣሪዎች አባባል የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታት አያማልዱም ለማለትና ከሞቱ በኋላ የሚሆነውን ነገር አያውቁም ለማለት አይደለም ። በሕየወተ ሥጋ እያሉ ከሥጋ ጋር እየተሟገቱ ጸጋ እግዚአብሔር ከእነርሱ እንዳልተለያቸውና ልቡና ያሰበውን በስውር ሰዎች ያደርጉትን ድርጊት ያውቁ እንደነበረ በወንጌል ላይ የተገለጸ ነው ። ሐዋ. ሥራ. ፯ ቁ. ፶—፷ ።

በሕይወተ ሥጋ እያሉ ታላቅ ሙግት እንደሚኖር ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በላከው ክታቡ ላይ እንዲህ ሲል ገልጾታል «ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ ። ብልቶቻችሁ ዓመጻ ሊያደርጉ ለርኩስነትና ለዓመጻ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንደቀረባችሁ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ እንዲቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አቅርቡ» ሮሜ. ፮ ቁ. ፲፱ ። እንዲሁም» ሕግ መንፈሳዊ እንደሆነ እናውቃለንና እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ የማደርገውን አላውቅምና የምጠላውን ያን አድርጋለሁ ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደሆነ እመስክራለሁ እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ። በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና» ሮሜ ፯ ቁ. ፲፭—፳ ።

ከላይ ጳውሎስ የገለጸው ሥጋ ምን ያህል ለክርስቶስ ወንጌል እንዳንገዛ ተጽእኖ እንደሚያደርግብን ነው ። ግን ይኸን ሥጋችንን ተሟግተን ድል በማድረግ በእግዚአብሔር ጸጋ እንቃኛለን ዳሩ ግን ይኸ ሥጋ ሙግቱን አያቆምም ። አንዳንድ ጊዜ ለኃጢአት ሲያንበረክከን ይታያል በንስሐ ግን እንመለሳለን ።



እንግዲህ ምን እንላለን በሥጋችን የኃጢአት ባሪያ በምንሆንበት ጊዜ በእግዚአብሔር ጸጋ ከተጥለቀለቅን ሩጫችንን በድል አድራጊነት ከፈጸምን በኋላ ይኸን ጸጋ እግዚአብሔር ይቀነስብናል? እንግዲህ ካልተቀነሰብን በሕይ ወተ ሥጋ እያሉ ቅዱሳን በተሰጣቸው ጸጋ ያማልዱ እንደነበር ሁሉ ይኸን ጸጋቸው አሁንም ስላልተነጠቃቸው በእግዚአብሔር ዘንድ በአጸደነፍስ ሆነውም ስለ እኛ ማማለድ ይችላሉ አይችሉም የሚል ካለ ግን ለምን? ምን ያግዳቸዋል? የሚል ጥያቄ እናቀርባለን ።

ሞት ማለት ለቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ከመኖር ይልቅ እጅግ የሚሻል ጸጋ ከጌታቸው የሚያገኙበት ነውና «ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው» ፊልጵ ፩ ቁ. ፳፫ ። በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ መሆኑን ተናግሯል ፡

8. <u>፪ኛ ቆሮ. ፫. ቁ. ፯—፲፩</u> ። ያለው ማብራሪያ እንደሚከተለው ነው ። «ስለዚያ ስለተሻረው ስለ ፊቱ ክብር» የሚለውን በመጥቀስ ሕገ ኦሪት ተሽሯልና ዛሬ ሊፈጸም አይገባውም ስለ ዚህም ታቦትም ሆነ ቤተ መቅደስ አያስፈልግም የሚሉ አሉ ። ዳሩ ግን ጳውሎስ ሕገ ኦሪት ተሽራለችና ከእንግዲህ ወዲህ ሕግንና ነቢያትን መቀበል የለብንም ማለቱ አይደለም ሕግና ነቢያትማ ሊሻሩ እንደማይችሉ ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ ሕግና ነቢያትን ልሽር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ» ማቴ. ፭ ቁ. ፲፯ ። በማለት ሕገ ኦሪትን ፍጽምት ሕግ ሊያደርግ መምጣቱን ተናግሯል ።

ስለዚህ ጳውሎስ ጌታ ያልሻራትን ሕገ ኦሪት እርሱ ሊሽርና ሊያጠፋ አይችልም ጳውሎስ ለወንጌል ምሳሌ የሆነችው ኦሪት ክብር ይደረግላት እንደነበር ጠቅሶ ያቺ ለወንጌል ምሳሌ ጥላ ሆና የነበረችው ሕገ ኦሪት እንደዚያ አይነት ክብር ከተሰጣት አማናዊዋ ሕግ ሕገ ወንጌልማ ምን ያህል አትከብር ።እንዲሁም በሙሴ ፊት ላይ ዘላለማዊ ያልሆነ ጊዜያዊ ብርሃን (የተሻረ) ወይም ኃላፊ ብርሃን ስለተሣለባት



www.ethiopianorthodox.org

እስራኤል የሙሴን ፊት ማየት የማይቻላቸው እስኪኾኑ ድረስ ክብር ከተደረገለት/ሙሴ ፊትህን ሸፍንልን ብለውት ነበር ።

መንፈስ ቅዱስ ለጸፋት ሕግ (በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተቃኝተው የጻፋዋት በመሆንዋ ነው ። ) ለወንጌልማ ምን ያህል ክብር ይደረግ ላት ይኾን ሞትን ለምታስፈርድ ኃጢአትን ቆጥራ ቆጥራ ለምትናገር ለዚያች ለሕገ ኦሪት ብዙ ክብር ከተደረገላት ሕይወት የሚገኝባት ሕገ ጽድቅ ወንጌልማ (በኦሪት ሕግ የሰው ልጅ ፍጹም ድህነት አላ ገኘም በክርስቶስ ካሣ ግን ፍጹም ድህነት ተገኝቷል እግዚአብሔ ርና ሰውን ለይቶ የነበረው የኃጢአት ግድግዳ ፈርሷል የተዘጋችው ገነት ተከፍታለች ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በምላት ተሰጥቷል ለዚህ ነው ሕገ ጽድቅ የተባለችው ።

ምን ያህል ትከብር ይኾን በማለት ሕገ ወንጌልን ከሕገ ኦሪት እያነጻጸረ ነው የመጣው በዚህ ፍጹም ክብር ባነጻጸራት ጊዜ ከብራ የነበረች ሕገ ኦሪት እንዳልከበረች እስክትሆን ደረሰች ። ከወንጌል ጋር አነጻጽሮ የወንጌል ክብር ፍጹም መሆኑን ሲያሳይ እንጂ ኦሪት የከበረች አይደለችም ማለት አይደለም ።

እንግዲህ አለ ጳውሎስ በምሳሌነት (በጥላ) የነበረው የኦሪት ሕግ ክብር ካገኘ ባለማለፍ ጸንቶ የሚኖረው ሕገ ወንጌልማ ምን ያህል ይከበር ይኾን እንዲሁም ኃላፊ (ምሳሌ) የሆነውን ሕገ ኦሪትን የያዘ ክብር ካገኘ (ሙሴ) ባለማለፍ ጸንቶ የሚኖር ሕገ ወንጌልንማ የያዘ ምን ያህል ክብርን ያገኝ ይሆን በማለት በወንጌል በማመን የሚገኘውን ፍጹም ክብር ገለጸ እንጂ ሕግና ነብያትን አትቀበሉ አላለም ።

ስለሆነም ዛሬ ጥንታዊትና ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ሕግንና ነቢያትን ከሐዋርያት ትምህርት ጋር በማጣጣም ፍጹም የሆነውን የጌ ታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዝ ትፈጽማለች ። ሕግንና ኦሪትን ሊሽር የመጣ ሳይሆን ፍጹም ሊያደርግ የመጣውን አምላክ ከነቃሉ ተቀብላ ያመነች ናትና ።

9. ትንቢተ ኢሳይያስ ፩. ቍ. ፲፫ «...ምናምንቴውን ቁርባን ጨምራችሁ አታምጡ ዕጣን በእኔ ዘንድ አስጸያፊ ነው መባችሁንና ሰንበታችሁን በጉባኤም መሰብሰባችሁን አልወድድም» በኢሳይ



ያስ አድሮ ዕጣን በእርሱ ዘንድ አስጸያፊ መሆኑን ተናግሮ ሳለ በኦር ቶዶክስ ቤተክርስቲያን የዕጣን መስዋእት ለምን ይቀርባል የሚል ጥያቄ የሚጠይቁ አሉ ።

በመሠረቱ እግዚአብሔር በቤተ መቅደስ የዕጣን መስዋእት ጨርሶ አታቅርቡ አልወድም ያለበት ጊዜ የለም በኢሳይያስ አድሮ የተናገረውን በጥንቃቄና በጥሞና ስናስተውለው ሐሳቡ ተጠራጣሪ ዎች ከተረዱት ውጭ ሆኖ እናገኘዋለን ።

እሥራኤል የእግዚአብሔርን ሕግና ቃል ሳይፈጽሙ የሚቃጠል የአውራ በግ መሥዋዕትንና የፍሪዳን ስብ እንዲሁም የዕጣን መስዋ ዕት ይዘው በቤተ መቅደስ ያቀርቡ ነበር ዳሩ ግን የሠራዊት ጌታ እግ ዚአብሔር ከላይ የተጠቀሱትን መስዋእት ከማምጣታቸው በፊት መጀመሪያ የራሳቸውን ሕይወት መስዋዕት አድርገው ማቅረብ እንደ ሚገባቸው ልባቸው ከእግዚአብሔር ርቆ ገንዘባቸውን ወደ ቤተ መቅደስ ቢያመጡ እግዚአብሔር በመስዋዕታቸው ተደሳች እንዳል ሆነ ይገልጻል ። ይኽንንም ለማወቅ ቁጥር ፲፮ እና ፲፯ ብንመለከት «ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ የሥራችሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ ክፉ ማድረግን ተው መልካም መሥራትን ተማሩ ፍርድን ፈልጉ የተገፋውን አድኑ ለድሀ አደጉ ፍረዱለት ስለ መበለቲቱም ተሟገቱ» በማለት መስዋዕቱን ከማቅረባቸው በፊት ሊያደርጉ የሚ ገባቸውን ቅድመ ዝግጅት ገልጾላቸዋል ። እንግዲህ ከፍ ብሎ መነሻ ውን ዝቅ ብሎ መቋጫውን ሳይመለከቱ አንድ ሐረግ መዞ በማውጣት ወደ ስህተት ገደል ተወርውሮ ከመውደቅ ምዕራፉን በሙሉ ማንበቡ ይመረጣል ።

ደግሞም እግዚአብሔር በኃጢአት ሥራ ተሞልታችሁ ያመጣ ችሁልኝ ዕጣናችሁ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት የለውም አለ እንጂ ዕጣን የተመረጠ መሥዋዕት ነው አላለም ይኽም ይታወቅ ዘንድ በኦሪት ዘጸአት ም. ፴ ቍ. ፴፬—፴፰ ባለው ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ እን ዲህ ብሎታል «ጥሩም ዕጣን ውሰድ ... በጨው የተቀመመ ንጹሕና ቅዱስ አድርገው ... እንደእርሱ የተሠራ ዕጣን ለእናንተ አታድርጉ በእናንተም ዘንድ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን ሊያሸተተውም እንደ እርሱ የሚያደርግ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ ።

እግዚአብሔር የዕጣን መስዋዕት ለእርሱ የተቀደሰና የተመረጠ እንደሆነ መናገሩን ልብ አልን?



www.ethiopianorthodox.org

መልካም መዓዛ ያለው መስዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል «እግዚአብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ...» ኖኅ ያቀረበውን መስዋዕትና ልመናም ተቀበለ ። ዘፍ. ፰ ቊ. ፳፩ ።

በተጨማሪም በብሉይ ኪዳን የነበሩ አበው ለእግዚአብሔር መልካም ሽታ ያለውን የዕጣን መስዋዕት ያቀርቡ እንደነበር በተለያየ ሥፍራ እናገኛለን ዘሌ ፮. ቊ. ፲፫ ።

ይኸ ሥርዓት ባንድ ወቅት በተወሰነ ክልል ብቻ የሚደረግ ሣይሆን እግዚአብሔር በሚመለክበት ቦታ ሁሉ እንደሚሆን አስቀድሞ እግዚአብሔር በነቢዩ ሚልክያስ አንደበት አስነግሯል «ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ ። » ትን. ሚል ፩ ቊ. ፲፩ ።

የዕጣን ስጦታ (ገጸ በረከት) እግዚአብሔርን የሚያስደስተው መሆኑን የተረዱት የጥበብ ሰዎች ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ካመጡለት ገጸ በረከት አንዱ ዕጣን ነው ማቴ. ፪ ቊ. ፲፩ ። ይኸውም ዘላለማዊ ክህነቱን መለኮታዊ ማዕዛውን ለማመልከት ነው ።

የዕጣን መስዋዕት ማቅረብ መጽሐፍ ቅዱሳዊና እግዚአብሔርንም ፍጹም የሚያስደስተው መሆኑን ዮሐንስ በራእዩ የተመለከተው እውነታ ነው ። «በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው ። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር በመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ» ራእይ ፰. ቊ. ፬ ። ራእዩ ፭. ቊ. ፰ ።

ቤተ ክርስቲያናችን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ዕጣን የምታጥነው የቀረበው ጸሎት ልመና በእግዚአብሔር ፊት እንዲደርስ ነው ። ሕጉም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘ መሆኑን ከላይ ጠቅሰናል ።

አንዳንድ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን ዕጣን ቤታቸው ቡና አፍልተው በአምልኮት መልክ ሲያጨሱ ይታያሉ እነዚህ ሰዎች ፍጹም የተሣሣቱና ከእግዚአብሔር ሕግ የወጡ መሆናቸውን ሊያውቁ ይገባል ።



www.ethiopianorthodox.org